

የ‹‹የፍቅር ሕግ›› በቴዎድሮስ ካሣሁን ‹ማር እስከ ጧፍ› ዜማ!

በተረፈ ወርቁ

"የትግራይ ሕዝብ ዘላለማዊ ነው ሕወሓት ግን ዘላለማዊ ያልሆነ የአንድ ቡድን ስብስብ ነው!"

ብርጋዲየር ጄነራል ተፈራ ማሞ



የእስረኞቹ ‹አጋች ታጋች› ድራማ

መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን!

# ግዮን

ግዮን ቅጽ 1 ቁጥር 3 መጋቢት 2010 ዓ.ም

ዋጋ 14.99







## የፖለቲካ ሰዎች ስለ ዶክተር አብይ ምን አሉ?





## "ኢህአዴግ ፊት የለውም !" ዶክተር አብይን ለምን መረጠ ?

ግዮን

ቅጽ 1 ቁጥር 3 ቅዳሜ መጋቢት 22 2010 ዓ.ም



16 **"የትግራይ ሕዝብ ዘላለማዊ ነው ሕወሓት ግን ዘላለማዊ ያልሆነ የአንድ ቡድን ስብስብ ነው!"**

**ብርጋዲየር ጄነራል ተፈራማሞ**

**ቀጣይ ዕትም ቅዳሜ መጋቢት 29 ይጠብቁን!**




ቁጥር 2 ዕትም

14 የቀለም አብዮት እና ኢትዮጵያ
*በታምራት መርጊያ*

21 የ‹‹የፍቅር ሕግ›› በቴዎድሮስ ካሣሁን ‹ማር እስከ ጧፍ› ዜማ!
*በተረፈ ወርቁ*

24 የቅዠት ሰዎች ወረራና የዕልም ዛፎች ተጋድሎ
*ደረጀ መላኩ*

5 የፖለቲካ ሰዎች ስለ ዶክተር አብይ ምን አሉ?

5 ‹‹ለዶ/ር አብይ በቂ ጊዜ ልንሰጣቸው ይገባል››
*አቶ ልደቱ አያሌው*

6



**"ኢህአዴግ ፊት የለውም !"**
*ዶክተር አብይን ለምን መረጠ ?*

9 ዶክተር አብይ አህመድ እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር እና የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ
*ግርማ ሰይፉ ማሩ*

2 የእስረኞቹ ‹አጋች ታጋች› ድራማ



10 "የኢትዮጵያ እስር ቤቶች ትልቅ የስቃይ በታዎች ናቸው"

12 ፍትሐዊው መሪ
*ሁሴን ከድር*

13 ‹‹በጨለማ ውስጥ ያላችሁ ውጡ!››
**በኃይሉ ገ/እግዚአብሔር**

26 ‹‹ከመጋረጃ ጀርባ››
*ፍቃዱ ልመንህ*

29 ‹‹ዶክተር አብይ የህዝቡን ጥያቄ ካልመለሰ፤ የከፋ ችግር ይገጥመዋል››
*ዶ/ር መራራ ጉዲና*

30 ‹‹የተመረጠው ኢህአዴግ ነው፤ ምንም ለውጥ የለውም››
*አቶ ቡልቻ ደመቅሳ*

31 ‹‹ህዝቡንም ሊያሳምን የሚችል አካሄድ ይከተላሉ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ››
*አቶ ተመስገን ዘውዴ*

32 122 ዓመት ስንት ነው?

# የእስረኞቹ ‹አጋች ታጋች› ድራማ



እሁድ መጋቢት 16/2010 በፖሊስ ቁጥጥር ስር የዋሉት ጋዜጠኞች፣ የፖለቲካ ሰዎችና ጦማሪያኑ እስካሁን ድረስ (መፅሔታችን ለህትመት እስከ ገባችበት ሃሙስ ከሰአት በኋላ) አልተለቀቁም፤ ወደ ፍርድ ቤት ተወስደውም ጉዳያቸው አልታየም፡፡ ሁኔታው በምን መልኩ እስከ መቼ ድረስ እንደሚቀጥልም በግልፅ የታወቀ ነገር የለም፡፡ ለመሆኑ በእለቱ የነበረው ዝግጅትና በስተመጨረሻ የተጠቀሱትን ግለሰቦች ለእስር የዳረገው ጉዳይ ምን ይመስላል? የሚለውን በስፍራው ተገኝቶ ጉዳዩን ሲከታተል የነበረው የግየን ባልደረባ እንደሚከተለው አቅርቦታል፡፡

## “ክብር ለጀግኖች”

ጀሞ አንድ ኮንዶሚኒየም ግቢ ውስጥ የሚገኘው የጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ መኖሪያ ቤት የተገኘነው በቅርቡ (ከአንድ ወር በፊት) ከእስር የተፈቱት የተለያዩ ፖለቲካ ድርጅት አባላት፣ ጋዜጠኞችና ግለሰቦችን ‹‹እንኳን ደህና መጣችሁ፤ ከወዳጅ ዘመዶቻችሁ ጋርም እንኳን በሰላም አገናኛችሁ›› ለማለት በተዘጋጀው ፕሮገራም ላይ ለመታደም ነበር፡፡

እንደ ሚዲያ አካልነታችን ይህ መረጃ እንደደረሰን አስቀድመን በጥሪው ቦታ ብንገኝም በተያዘለት ሰአት ፕሮግራሙ አልተጀመረም፡፡ ለእዚህ ዋነኛ ምክንያቱ ደግሞ ለእስረኞች በጠቅላላ በእለቱ ሰማያዊ ፓርቲ 6 ሰአት ላይ ያዘጋጀው ‹‹እንኳን ደህና መጣችሁ›› የምሳ ፕሮግራም ሰፋ ያለ ሰዐት በመውሰዱ ነው፡፡

9፡30 አካባቢ የሰሚያዊ ግብዣን አጠናቀው የተመለሱት እንግዶች ጥሪ በተደረገላቸው ስፍራ ሲገኙ ታዳሚው ከመቀመጫው በመነሳት በፍቅርና በአክብሮት ተቀብሏቸዋል፡፡ ብ/ጀነራል ተፈራ ማሞ፣ አቶ በቀለ ገርባ፣ አቶ አንዱአለም አራጌ፣ ጋዜጠኛ እስክነድር ነጋ፣ ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ፣ አቶ ዘሪሁን ገ/እግዚአሄር፣ አቶ ተስፋ ሚካእል አበበ (አበበ ቀስቶ)፣ ወ/ሮ እማዋይሽ አለሙና አቶ ዮናታን ተስፋዬን ጨምሮ በርካታ ታሳሪዎች የዝግጅቱ ተጋባዥ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

ዘግየት ብሎ የተጀመረው ፕሮግራም የተከተፈው የአስተባባሪ ቡድኑ ተወካይ ለእንግዶች ይቅርታ በመጠየቅ ነበር፤ ከሰአታት በፊት በተደረገው ግብዣ ላይ ታሳሪዎች መገኘታቸው ተገቢ መሆኑን ያመነው ታዳሚ ይቅርታውንና የእንግዳቹን ማርፈድ በፀጋ ተቀበሎታል፡፡ ይህ ፕሮግራም በተሰማሩበት የሙያ መስክና በያዙት ጠንካራ አላማ ሰላማዊ ትግል ሲያደርጉ ለእስር የተዳረጉትን ሰዎች እንኳን ለቤታችሁ አበቃችሁ ለማለትና መስዋዕትነት ለከፈሉበት፣ በፅናት ለታገሉለት ስራቸው እውቅና ለመስጠት ታስቦ የተዘጋጀ እንደሆነ የገለፁት አስተባባሪዎች “ክብር ለጀግኖች ይገባልና ይህ ፕሮገራም በቀጣይነት በሌሎች ስፍራዎችም ለማካሄድ አቅማችን በፈቀደ መጠን ጥረት እናደርጋለን” ብለዋል፡፡

የፕሮግራሙን መከፈት እንዲያበስርና ለእንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር እንዲያደርግ የተጋበዘው ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ እሱና ሌሎች ታሳሪዎች ከተፈቱ በኋላ እየተዘጋጁ ያሉት መሰል ዝግጅቶች ህዝቡ የጣለባቸውን እምነትና የሰጣቸውን አደራ ያለ እረፍት ጭቆናን ሙሉ ለሙሉ ከሀገሪቱ ለማጥፋት እንዲሰሩ ጥሩ የሞራል ስንቅ እንደሚሆናቸው ገልፆ “ከሁላችሁም ጋር በእስር አብሬ ብከርምም አሁን ያለነው በሌላ መንገድ ላይ ነውና እንኳን ደህና መጣችሁ፣ እንኳን ለእዚህ አበቃችሁ” ሲል መልካም ምኞቱን ገልጿል፡፡

አስተባባሪዎቹ ሁላችሁም ክብር የሚገባችሁ ጀግኖቻችን ብትሆኑም ለአሁኑ ግን ለተወሰኑ እስረኞች መጠነኛ ስጦታ አዘጋጅተናል፤ በማለት አቶአንዱአለም አራጌ፣ አቶ ኤለባና ሌሊሳ፣ አቶ ተስፋ ሚካኤል፣አበበ (አበበ ቀስቶ)፣አቶ ናትናኤል፣ መኮንን፣አቶ ማሙሸት አማረ፣ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝና ጋዜጠኛ ውበሸት ታዬን ሙሉ የአገር ልበስ ከነጃኖው ያለበሱ ሲሆን ወ/ሮ እማዋይሽ አለሙን ባማረ የአገር ልብስ አስውበዋታል፡፡

የተፈቱት እስረኞች የተበረከተላቸውን ስጦታ ለብሰው በታዳሚው ፊት ሲቀርቡ የነበረው ልዩ ድባብ እጅግ ማራኪ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ለአገርና ለወገን መብትና ጥቅም ሰላማዊ ትግል በማድረጋቸው ለበርካታ አመታት ለእስርና ለዕንግልት ሲዳረጉ የከረሙት ‹‹ጀግኖች›› ፊት ላይ የሚነበበው እውነተኛ ፈገግታና እርካታ የሚያስተላልፈው መልዕክት ከህዝብ ፍቅርና አክብሮት በላይ ምንም ነገር እንደሌላ የሚያሳብቅ ነበር፡፡

ተሸላሚዎቹም ይህንኑ ነው፡፡ ‹‹የሰራነው ለመሸለም ወይም ለመመስገን ባይሆንም ይሄ ለእኛ ከምንም በላይ ነው፤ ሁሌም ህዝቡ ከጎናችን እንደሆነ እንዲሰማን አድርጎናል” ብለዋል፡፡ የእለቱ የክብር እንግዶች የሆኑት ብ/ጀነራል ተፈራ ማሞና አቶ በቀለ ገርባም ለዝግጅቱ የቀረበውን ድፎ ዳቦ በጋራ ቆርሰዋል፡፡

## “የባንዲራው ውዝግብ”

ስጦታ የተበረከተላቸው ታሳሪዎች ለታዳሚያኑ የሰጡት አስተያየት እንዳለቀና የፎቶ ፕሮግራም እየተገባደደ ባለበት ወቅት ነበር የጀሞ አካባቢ የፖሊስ አባላት የደረሱት፡፡ በጊዜው እነ አቶ በቀለ ገርባን ጨምሮ አብዛኛው እስረኞች ወደ መጡበት ተመልሰዋል፡፡ በበታው ላይ የነበሩ ጥቂት ታዳሚዎች ከአቶ አንዱ አለም አራጌና ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ጋር ፎቶ እየተነሱ ፤ ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝም ለ6ኛ ጊዜ የታተመው “የፈራ ይመለስ” የሚለውን መፅሃፉን ፊርማውን በማሳረፍ ለእንግዶች እያበረከተ ነበር፡፡

ወደ ግቢው የገቡት ፖሊሶች በቀጥታ የተሰቀለውን ባንዲራ ነትተው ሲያወርዱ

ተመልክተናል፤ ድርጊታቸው ሃይልና ንዴት የተቀላቀለበት በመሆኑ ከእንግዶቹ ጋር መጀመሪያ ላይ በሰከነ መንፈስ ለመነጋገር ከመሞከር ይልቅ ቁጣ ማስቀደም፣ ለበላይ አለቆቻቸው ሪፖርት ማድረግን ነው የመረጡት። በእለቱ አብዛኛው ጥሪ የተደረገለት እንግዳ ወደ መጣበት ተመልሷል፤ በሰአቱ የነበሩት ጥቂት ግለሰቦችና እድሜያቸው ገፋ ያለ የጎረቤት ሰዎች ብቻ መኖሆናቸው እየታወቀ ነገሮችን ማለዘብና በሰላማዊ መንገድ እዛው ቦታ ላይ መቋጨት እየተቻለ ፖሊሶቹ "ማንም ሰው ከግቢው እንዳይወጣ" በሚል ትዕዛዝ ተጨማሪ ሃይል ለመጥራት ተጣድፈዋል።

በእንግዶቹና በጋዜጠኞች በኩል ፖሊሶችን ረጋ ባለ ሁኔታ ለማነጋገር ተሞክሮ ነበር። የህግ አስፈጻሚ አካላቱም "ይሄ የሰቀላችሁት ባንዲራ ሳይሆን ጨርቅ ነው፤ ባንዲራ ሊያስብለው የሚችለው ኮከብ የለም" የሚል አስተያየት መስጠታቸው ረገብ ለማድረግ የተሞከረውን ውዝግብ ወደ ከፍተኛ ክርክር አሸጋግሮታል።

‹‹እኛ የምናውቀው የኢትዮጵያ ባንዲራ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ነው፤ይሄ እንዴት ጨርቅ ይባላል? የአፍሪካ ተምሳሌት የሆነው የአድዋ ድል ላይ የተውለበለበው፣አለም በነፃነታችን አርማ የሚያውቀው ይህን የማንነታችን መገለጫ ባንዲራ እንዴት ጨርቅ ነው በማለት ታቃልሉታላችሁ? ታድያ ጨርቅስ ከሆነ ለምን እኛን ያዛችሁን?›› የሚል ጥያቄ የቀረበላቸው ፖሊሶች አጥጋቢ ምላሽ ለመስጠት የባንዲራውን ልዩነትና ትርጉም በቅጡ ለመግለፅ ተቸግረው በተደጋጋሚ በመገናኛ ራዲዮናቸው መልዕክት ሲያስተላልፉ ታዝበናል።

## ‹‹የታሳሪዎች የአንድነት መንፈስ››

ዘግየት ብለው ፖሊሶች‹‹መጀመሪይ እኛ ልንፈታ የምንችለው ጉዳይ ነበረ፤ በአለመግባባት ወደ በላይ አካል ስለደረሰ ሁለት ሰው በተወካይነት ስጡንና እነሱን ይዘን ጉዳዮን ለሃላፊዎቻችን ያስረዱ›› የሚል ጥያቄ አቀረቡ። መጀመሪያ እኛ ልንፈታው እንችል ነበር ያሉት ፖሊሶች ለአለቆቻቸው ለመደወል የፈጠኑበት መንገድ ተዘንግቷቸው እንደሆነ ባናውቅም መጀመሪያም ለማሰር የጓጉ እንጂ ለመወያየት የፈለጉ እንደማይመስሉ ተመልክተናል።

ታጋች እንግዶች እየተካሄደ ያለው "የአጋች ታጋች ድራማ" ያስደነገጣቸው አልነበሩም፡ ሁሉም ሰው መቀመጫው ላይ ሆኖ ስለቀጣዩ የአገሪቱ እጣ ፈንታ ፣ስለሰብአዊ መብት ጥሰት፣ ስለዜጎች ነፃነት ማጣት በግልፅ እየተወያየ ነበር፤ ሁለት ሰው ወክሉና እንውሰድ ለሚለው ጥያቄም ‹‹የምንወክለው ሁለት ሰው የለም ፤ፕሮግራሙን ያዘጋጀነው በጋራ ነውና የምትወስዱን ከሆነ አንድ ላይ ሁላችንንንም ልትወስዱን ትችላላችሁ ፤ከዛ ውጪ በተናጠል የምንሰጠው ሰው የለንም ››የሚል ምለሽ የሰጡት ለበርካታ ደቂቃዎች ጀሞ ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ መኖሪያ ቤት ግቢ ውስጥ የታገቱት እስረኞች የአላማ ፅናትና የአንድነት መንፈስ ሊደነቅ የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል።

የፖሊስ አባላቱ ከአቶ አንዱ አለም አራጌ ጋር በተናጠል ስለጉዳዩ ሰፋ ላለ ደቂቃ ለመነጋገር ሞክረው ነበር። "እኛ ሁላችሁንም መውሰድ ፈፅሞ አንፈልግም ሪፖርት ያደረግንለት አካልም ከአዘጋጆች መሃል ሁለት ሰው ይዛችሁ ኑ ነውያለን፤ ሁላችሁም ከምትሄዱና ከምትጉላሉ ጉዳዮን ሊያስረዳ የሚችል ሰው ስጡን" የሚል ጥያቄ በተደጋጋሚ ቢያቀርቡለትም "እከሌና እከሌ ብለን አሳልፈን የምንሰጣችሁ፣ የምንወክለው ሰው የለም፤ ከወሰዳችሁ አንድ ላይ ውሰዱን፤የተለየ የአቋም ለውጥ አይኖርም›› ሲል አስረድቷቸዋል።

በተደጋጋሚና አሰልቺ በሆነ መልኩ ሃላፊነት የሚወስድ ጥቂት ግለሰቦችን ብቻ ለመውሰድ ሲጣጣሩ የነበሩት የፖሊስ አካላት ጋዜጠኞች፣ ጦማሪያኑን ጨምሮ ሌሎች ግለሰቦችን አግተው የሬድዮ ልውውጥ ሲያደርጉ ከቆዩ በኋላ የታጋቾች እስረኞች የአንድነት መንፈስ ፈፅሞ የማይሸረሸርና አቋማቸው የፀና መሆኑን ሲመለከቱ ተጨማሪ የፖሊስ ሃይል አባላትን በመጥራት አመሻሹ ላይ አንድ ላይ ተሰብስበው የነበሩትን ታጋቾች ጎተራ መንገድ ፔፕሲ የመጠጥ ፋብሪካ አጠገብ የሚገኘው ፖሊስ ጣቢያ ወስደዋቸዋል።

## "ያልታሰበው እስር"

በእለቱ ወደ ጣብያ ተወስደው እሰካሁን (ሃሙስ ከሰአት በኋላ) ድረስ በእስር ላይ የሚገኙት

1-ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ
2-ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ
3-አቶ አንዱ አለምአራጌ
4-አቶ አዲሱ ጌታነህ
5-ጦማሪ ዘላለም ወርቅአገኘሁ
6-ጦማሪ ማህሌት ፋንታሁን
7-ጦማሪና ጋዜጠኛ በፍቃዱ ሃይሉ
8-ወይንሸት ሞላ
9-አቶ ይድነቃቸው አዲስ
10-አቶ ስንታየው ቸኮል
11-አቶ ተፈራ ተስፋዬ ናቸው።

ከታሳሪዎች መሃል ብዙዎች ከእስር ከተፈቱ በኋላ የአንድ ወር እድሜ ነው ያስቆጠሩት። መንግስት በምህረት ለቅቂያቸዋለሁ ቢልም መልቀቃቸውን አስመልቶ በተዘጋጀ የእንኳን ደህና መጣችሁ ፕሮግራም ላይ በመገኘታቸው ተመልሰው ታስረዋል። እነ እስክንድር አሁን ያሉበት ሁኔታ ግራ የሚያጋባ ነው ማለት ይቻላል። መጀመሪያ ላይ ከሌሎች እስረኞች ጋር ተቀላቅለው እንዲታሰሩ ተደረገ፤ በማግስቱ ከሌሉች እስረኞች ተነጥለው ለብቻቸው እንዲሆኑ ተደረገ።እሮብ እለት በድጋሚ ከሌሎች እስረኞች ጋር ተቀላቅለው በተጨናነቀ ሁኔተ ውስጥ እንዲታሰሩ ሆነ።

በተለያዩ ቀናት የተለያዩ አካላት መጥተው እስረኞችን አነጋግረዋል፤ ግን እስካሁን ድረስ አንዳችም መፍትሔ አልተገኘላቸውም። "ያሰራቸው ኮማንድ ፓስቱ ነው" እየተባለ ነው፤ ግን የሚመለከተው አካል ጉዳያቸው በህግ የሚያስጠይቅ ቢሆን እንኳን ተገቢውን መንገድ ተከትሎ አንዳች እንቅስቃሴ ሲያደርግ አይታይም። ከእስር የወጡ ሰዎችን መልሶ ማሰር በቤተሰብና በማህበራዊ ጉድኝቶች ዙሪያ የሚፈጥረው ጫና በግልፅ እየታወቀ የጦማሪያኑና የጋዜጠኞች ጉዳይ ለቀናት በዝምታ መሰንበቱ "ምን ታስቦ ነው" የሚል ጥያቄ እንድናቀርብ አስገድዶናል።

ለጤና አስጊ በሆነ መልኩ በእስር ላይ የሚገኙት እነዚህ ግለሰቦች መጨረሻ ምንድነው? ሰላማዊ ትግል የሚያደርጉ ሰዎች በየጊዜው ለእስር የሚዳረጉበት አሰልቺ ሂደት መቼይቅር ይሆን? እነዚህና ሌሎች የብዙሃኑ ህብረተሰብ አንገብጋቢ ወቅታዊ ጥያቄዎች ምላሽ ከአዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ አብይ አህመድ በፍጥነት ይገኝለታል ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

# ህጋዊ ፓርቲ ለማቋቋም ሲንቀሳቀሱ የታሰሩት

በአማራ ክልል ባህርዳር ከተማ መጋቢት 15/2010ዓ.ም ከተለያዩ የአማራ አካባቢዎችና ከአዲስ አበባ የተውጣጡ 19 ምሁራን እና ባለሙያዎች ጣና ሀይቅ አካባቢ የቅድመ ምስረታ ሂደት ውይይታቸውን አጠናቀው ለእራት በተሰባሰቡበት ወቅት ለእስር ተዳርገዋል። ምርጫ ቦርድ ያውቀዋል የሚባለውን ህጋዊ የፖለቲካ ፓርቲ ለመመስረት ዝግጅት በሚያደርጉበት ወቅት ነው ባህርዳር ከተማ ላይ ወደ ቀበሌ 14 በሚገኘው 9ኛ ፖሊስ ጣቢያ ታፍሰው ተወስደዋል ።

የአማራ ክልልም ሆነ የባህርዳር ከተማ ፖሊስ ተቋማት በታሳሪዎቹ ጉዳይ እስከ ሐሙስ ዕለት ድረስ የሰጡት ምላሽ አልታወቀም።

# የዋልድባ መነኮሳት ተለዋጭ ቀጠሮ ተሰጣቸው

ለመጋቢት 18 ተቀጥረው የነበሩት አባ ገብረየሱስ ኪ/ማርያም እና አባ ገብረስላሴ ወ/ሃይማኖት በድጋሚ ለሌላ የአንድ ወር ቀጠሮ ተሰጥቷቸው እንዲመለሱ ተደርገዋል። በከፍተኛው ፍርድ ቤት 4ኛ ወንጀል ችሎት የቀረቡት የዋልድባ አባቶች ላይ አቃቤ ህግ ምስክሮች አልተሟልሉኝም የሚል ሰበብ በማቅረብ ተለዋጭ ቀጠሮ ለችሎቱ አቅርቧል። ዳኞቹም ጥያቄው ተገቢ እንዳልሆነና በቂ ጊዜ እንደነበረው በመጠቆም ለሚያዚያ 18/2010 ዓ.ም ምስክሮቹንና ማስረጃዎቹን አሟልቶ እንዲቀርብ አዘዋል።

የተከሳሾቹ ጠበቃ አመሃ በበኩላቸው ለአቃቢ ህግ በቂ ጊዜ ተሰጥቶታል ስለዚህ ተጨማሪ ቀነ ቀጠሮ መፍቀዱ ተገቢ አይደለም ብለው ቢከራከሩም ለትክክለኛ ፍትህ ሲባል አንድ ቀጠሮ ተገቢ ነው በማለት ዳኞቹ መነኮሳቱ ቀጣይ አንድ ወሩን በእስር ቤት እንዲያሳልፉ ወስነዋል።

# ፖሊስ የስዩም ተሾመ ጉዳይ በመደበኛ ፍርድ ቤት አይታይም አለ

በአምቦ ዩንቨርሲቲ ወሊሶ ካምፓስ መምህርና ጦማሪ ስዩም ተሾመ ከሳምንታት በፊት የካቲት 28 ቀን 2010 ዓ.ም በኮማንድ ፖስቱ ተይዞ ማዕከላዊ እስር ቤት ከገባ ጀምሮ እስካሁን ፍርድ ቤት አልቀረበም። ፍርድ ቤቱ የካቲት 30 ቀን 2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት ለመጋቢት 13 ቀን 2010 ዓ.ም የ14 ቀን ተለዋጭ ቀጠሮ ቢሰጠውም ፖሊስ ሊያቀርበው ፈቃደኛ አልሆነም።

ፍርድ ቤቱም በፌደራል ፖሊስ ጥያቄ መሰረት የጦማሪ ስዩም ተሾመን የጊዜያዊ ቀጠሮ መዝገብ እንዲዘጋ ወስኗል።

# መጋቢትን በታሪክ

እቴጌ መነን አስፋው መጋቢት 25/1883 ዓ.ም ተወለዱ፡፡

*መጋቢት አንድ ቀን 1884 ዓ.ም*

ከዛሬ 128 ዓመት በፊት፣ በኢትዮጵያውያንና በሱዳኖች መካከል መተማ ላይ መጋቢት አንድ ቀን ጠዋት ጦርነት ተጀመረ፡፡ የደርቡሽ ጦር በመጨረሻ ድል አድርጎ የአፄ ዮሐንስን አስክሬን ማረከ፡፡ አንገታቸውንም ቆርጠው በካርቱም ገበያ አዞሩት፡፡ አፄ ዮሐንስ አንገታቸውን የሰጡላት ኢትዮጵያ ግን በነፃነት እስከ አሁን ትኖራለች፡፡

*መጋቢት 13/1898 ዓ.ም*

ልዑል ራስ መኮንን ወልደ ሚካኤል ቁልቢ ላይ ሕይወታቸው አለፎ፣ ራሳቸው በተከሉት የቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ሐረር ከተማ ተቀበሩ፡፡

*መጋቢት 20/1900 ዓ.ም*

ዳግማዊ አፄ ምኒልክ የጠፉ እንስሳትን በተመለከተ የሚከተለውን አዋጅ አስነገሩ፡፡ "ከከተማ ዙሪያ የጠፋ ከብት የገባብህ ሰው የማታውን ለጠዋት፣ የጠዋቱን ለማታ እያገባህ፣ የሚገባህን ተቀበል ብዬ ሦስት አራት ጊዜ አዋጅ ነገርኩ፡፡ አንተ ግን የማትሰማ ሆንክ፡፡ የከተማው ከብት ሁሉ እየጠፋ የማይገኝ ሆነ፡፡ አሁንም የጠፋ ከብት የገባብህ ሰው በቶሎ አግባ፡፡ እንግዲህ ግን በቶሎ ጠቅለህ ያላገባህ እንደሆነ ከዚህ ከተማ የጠፋውን ከብት ሁሉ የጠፋበት ሰው ባወቀ እየገመተ፣ በከተማው ዙሪያ ያለህ ሰው ትከፍላለህ፡፡ የሌላውም አገር ሰው የጠፋ ከብት የገባብህ አታውል! አታሳድር! በቶሎ አግባ!!!"

*መጋቢት 25/1904 ዓ.ም*

ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር በመሆን አገራቸውን ያገለገሉት ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሐብተወልድ ከአለቃ ሀብተወልድ ካብትህ እና ከወይዘሮ ይደግድጉ ፊልፊሉ በቡልጋ ተወለዱ፡፡

*መጋቢት 16/1916 ዓ.ም*

አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ መኮንን "ስለ ባሮች አስተዳደርና ነፃነት የቆመ ደንብ" የሚል ርዕስ የተፃፈ ባለ አሥር ገጽ መመሪያ አሳተሙ፡፡ በሳምንቱ መጋቢት 22 ቀን 1916 ዓ.ም በአገሪቱ ባሪያ እንዳይሸጥ፣ እንዳይገዛም የሚከለክል አዋጅ እንዲታወጅ አደረጉ፡፡

*መጋቢት 21/1928 ዓ.ም*

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የኢትዮጵያ ጦር ጠቅላይ አዛዥ በመሆን ማይጨው ላይ ከኢጣልያን ጦር ጋር ተዋጉ፡፡ መጋቢት 28/1933 ዓ.ም ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ከአምስት ዓመት ስደት በኋላ በታላቋ ብሪታኒያ ጦር ዕርዳታና በኢትዮጵያ ዓርበኞች አይበገሬነት የጣሊያንን ጦር እየደመሰሱ በድል አድራጊነት ደብረማርቆስ ከተማ ገቡ፡፡ በዚያኑ ቀን በጀነራል ካኒኒንገሃም የተመራው የእንግሊዝ ጦር አዲስ አበባ ከተማን ከኢጣልያ ጦር አስለቀቀ፡፡

*መጋቢት 19/ 1953 ዓ.ም*

በታኅሣሥ ግርግር መፈንቅለ-መንግሥት ቀንደኛ ተዋናይ ናቸው የተባሉት ብርጋዲየር ጀነራል መንግሥቱ ነዋይ በስቅላት እንዲቀጡ ተፈረደ፡፡ ጀነራሉ ይግባኝ መጠየቅ መብታቸው እንደሆነ ሲነገራቸውም፡- "እናንተ ዳኞች የበየናችሁብኝን የሞት ፍርድ ያለ ይግባኝ ተቀብያለሁ፡፡ ይግባኝ ብዬ የሚመለከትልኝ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቢሆን ኖሮ ደስ ብሎኝ ይግባኝ ማለት በፈለኩ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ እንደማይሆን አውቃለሁና የአፄ ኃይለሥላሴን ፊት ለማየት አልፈቅድም፡፡ ከእናንተ ከዳኞችና የሞት ፍርድ እንድትበይኑብኝ ካዘዛችሁ ሰው ይልቅ ፍርዱን ተቀባዩ የዛሬው ወንጀለኛ እኔ፣ የነገ ባለታሪክ ነኝ" አሉ፡፡

*መጋቢት 20/1953 ዓ.ም*

ብርጋዲየር ጀነራል መንግሥቱ ነዋይ በአራዳ አደባባይ በስቅላት ተቀጡ፡፡ በዚሁ ዕለት ንጉሠ ነገሥቱ ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር አድርገው ሾሟቸው፡፡

*መጋቢት 4/1957 ዓ.ም*

"መሬት ለአራሹ የምትሹ፣ ተዋጉለት አትሽሹ!" የሚለውን መዝሙር፣ የዚያን ጊዜው የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ተማሪዎች በፓርላማው ፊት ለፊት አሰሙ፡፡

*መጋቢት 3/1961 ዓ.ም*

የኤርትራ ነፃነት ግንባር ጀበሀ የኢትዮጵያን አየር መንገድ ቦይንግ 707 አውሮፕላን በፍራንክፈርት አየር ማረፊያ በቦንብ አጋየ፡፡

*መጋቢት 5/1963 ዓ.ም*

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴና ልዑል አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን በደቡብ የእርሻ ልማት ሲጎበኙ የሄዱባት ሩሲያ ሰራሽዋ ኤም 60 ሄሊኮፕተር ድንገተኛ እክል አጋጥሟት ተከሰከሰች፡፡ በአደጋው ሦስት ሰዎች ሲሞቱ ንጉሠ ነገሥቱና አልጋ ወራሹ፣ ምንም ጉዳት አልደረሰባቸውም ነበር፡፡

*መጋቢት* 2/1965 ዓ.ም

ጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሀብተወልድ የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት፣ ከኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበራት ድርጅት ጋር ስምምነት ላይ መድረሱን አሳወቁ፡፡

*መጋቢት 11/1964 ዓ.ም*

የወንጂ ስኳር ፋብሪካ ተመርቆ ሥራ ጀመረ፡፡

*መጋቢት 21 ቀን 1992 ዓ.ም*

በኢትዮጵያ የሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ፋና ወጊ የሆኑት ባለ ሀብት አቶ በቀለ ሞላ አረፉ፡፡

*መጋቢት 16 ቀን 2003 ዓ.ም*

የህዳሴ ግድብ የመሠረት ድንጋይ ጉባ ላይ ተቀመጠ፡፡


**ጥቅምት 2010 ዓ.ም ተመሠረተ**
**ኢትዮ ሐበሻ ሕትመትና**
**ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር**
**በየ 15 ቀኑ ለሕትመት**
**የምትበቃ መጽሔት**

ማኔጂንግ ዳይሬክተር
ፍቃዱ ማ/ወርቅ

ዋናአዘጋጅ
ፍቅር ሠይድ
አድራሻ፡- አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 7
የቤት ቁጥር 314

አዘጋጆች
ሮቤል ምትኩ
ብሩክ መኮንን

አምደኞች
አበባው አያሌው
ቴዎድሮስ ተ/አረጋይ
ተረፈ ወርቁ
መስፍን ጌታቸው
ሁሴን ከድር
በሀይሉ ገ/እግዚአብሔር
ሠሎሞን ለማ

ክርኤቲብ ዲዛይን
መስፍን አድነው

የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ
አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09
የቤት ቁጥር 552/1
አምበቸው ህንፃ 5ተኛ
ፎቅ ቢሮ ቁ. 501
ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029
ስልክ : +251 911 227661
+251 912 165606
+251 118 951693
ኢ-ሜይል፡
Gihon2010meg@gmail.com
Facebook
Gihon meg

አታሚ
ሰለሞን፣ ከበደና ጓደኞቹ ኅትመትና
ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማ
አድራሻ
ክ/ከተማ ን/ስ/ላ፣ ወረዳ12
የቤት ቁጥር 1876
ስልክ ቁጥር 0911 77 15 56
0909 54 83 30

# የፖለቲካ ሰዎች ስለ ዶክተር አብይ ምን አሉ?

ኢህአዴግ በቀውስ ውስጥ መሰንበቱን ይፋ በሆነበትና የህዝብ አመፅ ከተለያየ አቅጣጫ በበረታበት ወቅት አቶ ኃይለማሪያም ደሳለኝ ለተፈጠረው ችግርና ለሚጠበቀው ለውጥ መፍትሔ አካል ለመሆን ራሴን ከሃላፊነት በፍቃዴ አንስቻለሁ ሲሉ በአገሪቱ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ አዲስ ምዕራፍ ተከፈተ የሚል ተስፋ በበርካታ ኢትዮጵያዊያን ዘንድ አሳድሯል፡፡

በርግጥ አቶ ሃ/ማሪያም ደሳለኝ የችግሩ ምንጭ አልነበሩም፡፡ ችግሩ የስርአቱ የተሳሳተ መንገድ እንጂ፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ እሳቸው ከስልጣን እንዲወርዱ አልጠቀየቀም፤ መፍትሄው እሱ ይሆናል ብሎ ስለማያምን ፡ ፡ነገር ግን ተተኪው ጠቅላይ ሚኒስትር ማን ይሆን? የሚለው ጉዳይ በተወሰነ መልኩም ቢሆን ህብረተሰቡን በጥልቀት አወያይቷል፡፡

ለበርካታ አመታት የታሰሩ የፖለቲካ ፓርቲ አባላት፣ ጋዜጠኞች፣ ጦማሪያንና የተለያዩ የፖለቲካ እስርኞች በምህረት መለቀቃቸው ደግሞ የበለጠ ለውጥን እንድንናፍቅ አድርጎናል፡፡ ‹‹ኢህአዴግ በችግሮቹና በህዝቡ ጥያቄዎች ላይ ጥልቅ ውይይት ለማድረግ ስበስባ ተቀምጫለሁ›› ብሎ በሰነበተ ሰሞን የሚሰነዘሩ አስተያየቶችም ቢሆኑ ወደ ስልጣን ማን ይመጣል የሚለው ጉዳይ ነበር፡፡

የአራቱን ድርጅቶች ጉዳይ ለመገምገም በዝግ ስበስባ በርካታ ቀናትን ያሳለፈው ኢህአዴግ እንዲሁ በደፈናው ‹‹ስህተታችንን ነቅሰን አውጥተናል፤ወደ ፊት የበለጠ ለመስራት ቃል ገብተናል›› የሚል መግለጫ ሰጥቶ ወደ ቀጣዩ መነጋገሪያ ርዕሱ ከተሸጋገረ ከቀናት በኋላ ማክሰኞ የግንባሩን አዲስ ሊቀመንበር መርጧል፡፡

ኢህአዴግ ለጠቅላይ ሚኒስትርነቱ ይመጥናሉ ያላቸው ዶክተር አብይ አህመድ እንደሚመረጡ አስቀድሞ ሲወራ ነበር፡፡ በተለይም በኦሮሚያ ክልል የተነሳውን አመፅ ተከትሎ ባለፈው አንድ አመት ጊዜ ውስጥ በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚሰጥዋቸው አስተያየቶች ግለሰቡ ቀጣዩ የኢህአዴግ ሊቀመንበር ሊሆኑ ይችላሉ የሚል ግምት እንድንይዝ አድርጎናል፡፡ የዝግ ስብሰባው መራዘም በመጨረሻ ያልታሰበ ሰው ተመርጦ ሊያሳየን ይችላል ጭምጭምታ አልፎ አልፎ በህዝቡ ዘንድ ቢያንፀባርቅም፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ ከመቼውም ጊዜ በላቀ መልኩ በንቃት ሲከታተለው የሰነበተውና ሲጠብቀው የቆየው የኢህአዴግ ማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ሲጠናቀቅ ዶ/ር አብይ አህመድ ዓሊን ቀጣዩ የድርጅቱ ሊቀመንበር አድርጎ መርጧቸዋል፡፡

ቀጣዩን የኢህአዴግ ሊቀመንበርና አዲሱን ጠቅላይ ሚኒስትር ለመምረጥ በተደገው ፉክክር ውስጥ የተካተቱት አቶ አብይ አህመድ፤ አቶ ሽፈራው ሽጉጤና አቶ ደብረጽዮን ገብረሚካኤል በመራጩ ዘንድ ያላቸው ሚናና ቅቡልነት በጉልህ ተለይቶ የታወቀበት ሆኖ አልፏል ማለት ይቻላል፤ በድምጽ ቆጠራው እንደታየው ከ169ዎቹ ድምጽ ሰጪዎች ወስጥ አንድ መቶ ስምነቱን ዶክተር አብይ አህመድ ዓሊ በመውሰድ ሲያሸንፉ፤ ቀሪውን 59 ድምፅ አቶ ሽፈራው ሽጉጤ፣ ሁለት ድምፅዶ ክተር ደብረጽዮን ገብረ ሚካኤል አግኝተዋል፡፡ ከ180 አባላት መሃል169 ሲገኙ አስራ አንዱ በተለያየ ምክንያት አልተገኙም፡፤

ምርጫውን አስመልክቶ የኢህአዴግ ጽ/ቤት ኃላፊ የሆኑት አቶ ሽፈራው ሽጉጤ ‹‹ምርጫው ፍትሐዊና ትክክለኛ ነበር›› ሲሉ በጋዜጣዊ መግለጫቸው ላይ ጠቅሰው በድርጅቱ ህግና ደንብ መሠረት የኢህአዴግ ሊቀመንበር ሆኖ የሚመረጠው ሠው የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ስለሚሆን በቅርቡ ይህ ሹመት ጉዳዩ በሚመለከተው የህዝብ ተወካዮች ምክርቤት ቀርቦ እንደሚፀድቅ ተናግረዋል፡፡

ኢህአዴግ በአቶ ኃይለማርም ደሳለኝ ኃላፊነት መልቀቅ የነበረው ክፍት ቦታ አንድ ብቻ በመሆኑ በጥቆማ በቀረቡት ግለሰቦች መሀል ምርጫ እንደተደረገ የሚናገሩት የጽ/ቤቱ ኃላፊ በሀገሪቱ በተፈጠረው ያለመረጋጋት ምክንያት ያልተካሄደው የድርጅቱ ጉባኤ በነሃሴ ወር መጀመሪያ እንደሚካሄድ በምክርቤቱ አባላት መወሰኑን ይፋ አድርገዋል፡፡

ጋዜጠኞች ለመግለጫ ተጠርተው ለስምንት ሰአታት ያህል እንዲቆዩ ያስገደደው የዶክተር አብይ አህመድ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር መሆን ይፋ ከሆነ በኋላ ግዮን መጽሔት ከፖለቲካና አገራዊ ፋይዳ አንፃር ቀጣይ ሙያቸው ምን መሆን አለበት? በሚሉና በሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ዙሪያ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ሰፊ ልምድ ያላቸው ዶክተር መራራ ጉዲና፣ አቶ ተመስገን ዘውዴ፣ አቶ ቡልቻ ደመቅሳና አቶ ልደቱ አያሌውን አነጋገረናቸዋል፡፡ ፖለቲከኞቹ የሰጡትን አስተያየት እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡

# ‹‹ለዶ/ር አብይ በቂ ጊዜ ልንሰጣቸው ይገባል››

## አቶ ልደቱ አያሌው

ግዮን፡- ዶክተር አብይ አሊ አዲሱ የኢህአዴግ ሊቀመንበር ሆነው ተመርጠዋል፡፡ ካላቸዉ ፖለቲካዊ ልምድ አንፃር የእሳቸውን ሹመት እንዴት አዩት?

አቶ ልደቱ፡- ሁልጊዜም እንደምንለው ኢህአዴግ በድርጅት ደረጃ የያዘውን አስተሳሰብ መስመሩን፣ አደረጃጀቱን የፖለቲካ ባህሉን ካልተቀየረ በስተቀር በአገር ደረጃ የሚመጣ መሠረታዊ ለውጥ ሊኖር አይችልም፡፡ አንድ መሪ ስለተቀየረ ብቻ የሚፈጠር ነገር አይኖርም፤ የድርጅቱ መቀየር ካልመጣ፡፡ ይሄ ማለት በአስተሳሰብ ፣ በአሰራር፣ በፖለቲካ ባህል ካልተለወጠ የአገሪቱ ወቅታዊ ሁኔታ ሊለወጥ ይችላል፡፡ እሱ ለውጥ ካልመጣና በተመሳሳይ መንገድ የሚቀጥል ከሆነ የዶክተር አብይ ሚና ከአቶ ኃይለማርያም የተለየ ሊሆን አይችልም፡፡ ነገር ግን ሰውን ከሰው መምረጥ ካለብን እኔ ዶክተር አብይ ይሆናሉ ብዬ አልጠበቅኩም ነበር፤ ግን በመረጣው በሁለት ምክንያት ደስተኛ ነኝ፡፡

አንደኛው ወጣት ናቸው፤ ይሄ የተበላሸ የፖለቲካ ባህል ያለው የመኢሶን፣ ኢህአፓ ትውልድ አባል አይደሉም፡፡ ላለፈው አንድ ዓመት በተለያዩ መድረክ ሲሰጡ የሰማነውን ንግግር እንደታዘብነው ለመግባባት፣ ለመቻቻል፣ ለውይይት፣ ለድርድር በሮች መከፈት አለባቸው የሚል አቋም የነበረው ነው፡፡ ይህን የራሳቸውን ባህል የድርጅት ባህል ለማድረግ ጥረት ካደረጉ የአገሪቱ ፖለቲካ ትልቅ አስተዎፅኦ ሊያበረክቱ ይችላሉ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

ሁለተኛው ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው መሰረታዊ የፖለቲካ ቅራኔ በብሔር ማንነት እና በኢትዮጵያ ጦርነት መካከል መሆኑን የጠበቀ አስተሳሰብ የማምጣት ጉዳይ ነው፡፡ በተለያዩ መድረኮች ያደረጉትን ንግግር እንዳየው በዚህ ረገድ ሁለቱን አስተሳሰቦች ሊያስታርቅ የሚችል ሚዛናዊ አመለካከት እንዳልታየ አይተናል፡፡ በአንድ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ አንድነት ምሉዕ ሆኖ መቀጠልና

ወደ ገጽ 28 ዞሯል

# “ኢህአዴግ ፊት የለውም !”

## ዶክተር አብይን ለምን መረጠ ?



ባለፉት ሳምንታት በዝግ ሲካሄድ የሰነበተው የኢህአዴግ ስራ አስፈጻሚ እና የምክር ቤቱ ስብሰባ የመጨረሻ ማጠቃለያው በጉጉት ሲጠበቅ ሰንብቷል። ኢህአዴግ በአቶ በረከትም ይሁን በጣልቃገብ መግለጫ በሰጡ ባለስልጣናቱ በኩል "የስብሰባዬ ዋና ግብ እስካሁን የተሰሩ ስራዎችን መገምገም እንጂ ጠቅላይ ሚኒስትር መምረጥ አይደለም" ቢልም ብዙኃኑ ግን ይህንን አባባል "ፈርቶ ዘራፍ እንደማለት ዓይነት ማስመሰል ነው" ሲሉ ተችተውታል። "ኢህአዴግ ጠቅላይ ሚኒስትር መምረጥ ጉዳዩ ካልነበረ ይህን ያህል ጊዜ በዝግ ስብሰባ ሲከራከርና ሲራኮት የከረመው ታዲያ በየትኛው አገራዊ ጉዳይ ውሳኔ ለማሳለፍ ነበር?" ሲሉ ጠይቀዋል።

ለማንኛውም "ኢህአዴግ በ27 ዓመታት የአገዛዝ ዘመኑ ባካሄዳቸው ስብሰባዎች ህዝብ ህዝብ የሚሸት ውሳኔ አሳልፎ አላየንም " ብለው የሚተቹ ጦማሪያን እና ተቃዋሚዎች በበኩላቸው "የኢህአዴግ ያለፉት ሳምንታት ስብሰባ የብዙኃኑን ትኩረት የሳበው ፓርቲው የህዝብ ድምጽ ሰምቶ ዶክተር አብይን ሊቀመንበሩና የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር አድርጎ ይሾማል? ወይስ እንደለመደው በግትርነቱ ይዘልቃል' የሚለው ጥያቄ የሚመለስበት አጋጣሚ ስለነበር ነው" ይላሉ።

በአገር ውስጥም ይሁን በመላው ዓለም የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ዜጎችንና የኢህአዴግ ፖለቲካ ተቃዋሚ ወገኖችን እንዲሁም ዓለም አቀፍ ታዛቢዎችን ቀልብ ጭምር ይዞ የከረመው የአዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ማንነት ጉዳይ ማክሰኞ መጋቢት 18 እኩለ ሌሊት መዳረሻ የኢህአዴግ ስብሰባ የመጨረሻ ማጠቃለያን አስመልክቶ በተሰጠ ይፋዊ መግለጫ ታውቋል። ፓርቲው በመጨረሻ ዶክተር አብይ አህመድን ሊቀመንበሩ አድርጎ መሾሙን አሳውቋል። የፓርቲው ሊቀመንበር የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር መሆኑ የተለመደ አካሄድ በመሆኑም (በፓርቲው አቅራቢነት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ማጽደቁ እንደተጠበቀ ሆኖ ) በሌላ ቋንቋ ዶክተሩ የኢትዮጵያ የቀጣዮቹ ሁለት ዓመታት ጠቅላይ ሚኒስትር መሆናቸው ተረጋግጧል።

ከፓርቲው ደጋፊዎች ወገን "ኢህአዴግ ደጋግሞ እንደተናገረው በጥልቅ ታድሷል፣ ህዝብን ማዳመጥ ጀምሯል፣ ባህሪውንም ለውጧል" የሚሉ አስተያየቶች እየተሰነዘሩ ቢሆንም በተቃራኒው "ፓርቲው ዶክተሩን የመረጠው የህዝብ ድምጽን በማክበር ሳይሆን ገፍቶ የመጣውንና በከባድ አደጋ ጫፍ ላይ የደረሰውን ህዝባዊ ተቃውሞ ለማርገብ እንዲሁም ለረጅም ዘመን አገዛዝ እቅዱ እዚህም እዚያም የተደቀኑበትን እንቅፋቶች ለመበጣጠስ ጊዜ መግዛት አስቦ ነው" የሚሉ የጥርጣሬ ድምጾችም ጎልተው እየተሰሙ ነው።

## በእርግጥ ኢህአዴግ ዶክተር አብይን ለምን መረጠ?

በፓርቲ አባልነት ግለሰባዊ ስብዕና መገንባት ርካሽ ተወዳጅነትን ከማትረፍ እኩል የሚፈረጀው ኢህአዴግ ዛሬ ህዝብ የካባቸውን ሰው ወደስልጣን ለማምጣት ምን አስገደደው ? ...ግዮን መጽሔት እነዚህንና መሰል ጥያቄዎችን ከነባራዊ እውነቶች አንጻር በመመዘን በጥቂቱ ለመዳደስ ትሞክራለች።

## የኢህአዴግ 'ፊት አልባ ፓርቲነት' ውጤቶች

"ኢህአዴግ ፊት የለውም !" የሚለው መርህ ከትጥቅ ትግል ጀምሮ ዛሬ ድረስ ለዘመናት የኖረ የፓርቲው መለያ ሆኖ ቆይቷል። ጎምቱ ባለስልጣናቱ በተለያዩ መድረኮች እንደመሰከሩት፣ የፓርቲው የ27 ዓመታት ባህሪም በግልጽ እንደሚያመላክተው ኢህአዴግ "ምስጢራዊ የፖለቲካ ድርጅት" ነው። "ፓርቲው መታወቅ ካለበት እንደ ፓርቲ በኢህአዴግነቱ እንጂ በግለሰብ ስምና ሰብዕና ላይ ተንተርሶ አይደለም" የሚል ጽኑ እምነት ይዞም ኖሯል። ኢህአዴግ የሚከተለው ውስጠ ፓርቲ አሠራር ዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት ላይ የተመረኮዘ እንደመሆኑ ግለሰባዊ ልዕልናን ሳይሆን ቡድናዊ አሠራርን የሚያገዝፍ ሂደት ይከተላል። በዚህም ሳቢያ በመርህ ደረጃ የአባላቱ ግላዊ አሳብ የቡድን ተቀባይነትን ካላገኘ በቀር የፓርቲው አጀንዳ ሊሆን የሚችልበት ዕድል የለም። ብዙዎች እንደሚተቹት ይህ አካሄድ ደግሞ ከፓርቲው አካሄድ የተለየ አቋም የያዙ አባላቱ የሚኖራቸውን ጠቃሚ ሀሳብ የፓርቲው አሰራር ውስጥ ለማስረጽ እድል ነፍጓቸው ቆይቷል። በውጤቱም ፓርቲው ለለውጥ አራማጅ አስተሳሰብ በሩን የዘጋና አዳዲስ ሀሳቦች የማይፈልቁበት ድርጅት ሆኖ እንዲቀጥል አድርጎታል ።

ፓርቲው በዚህ አካሄዱ ኢህአዴግነታቸውን ሳይለቁ ፓርቲያቸው ከሚከተለው ግትር ፖለቲካ ፈቀቅ ብለው ወደ ህዝብ ቀረብ ያሉ አባላቱን ሲኮረኩምና "ርካሽ ተወዳጅነትን ለማትረፍ የሚሮጡ" ብሎ ሲገመግም ኖሯል። በምርጫ 97 ሠሞን አቶ አርከበ ዕቁባይ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ በነበሩበት ወቅት ወደ ህዝብ በጣም የቀረበ አካሄድ በመከተላቸው ብቻ ሳይሆን አንጻራዊ በሆነ መልኩም ቢሆን በወቅቱ ፓርቲው የሌለው አይነት የህዝብ ድጋፍ በማግኘታቸው ፣ ከዚያም አልፎ "አርከበ ኢህአዴግ ባይሆን እንመርጠው ነበር" የሚል ድምጽ መሰማት በመጀመሩ መለስ ዜናዊ "ሶስት ቦታ ጥዳ አንዱም እንደማይበስልላት ሴት..." በማለት ሰውየውን እንዴት በአደባባይ ዘልፈው ከቦታቸው እንዳነሷቸውና በሚኒስትር ዲኤታ ስልጣን ወደ ሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር እንደወሰዷቸው አይዘነጋም።

በተቃራኒው ደግሞ መለስ ዜናዊ በቃል "ድርጅቴ በመደበኝ ቦታ እሰራለሁ….ያዘዘኝን የምፈጽም ወታደር ነኝ ፣ የራሴ ስልጣን የለኝም" ይበሉ እንጂ በተግባር ግን ከፕሬዚዳንትነት እስከ ጠቅላይ ሚኒስትርነት በኖሩበት የሁለት አስርተ ዓመታት የስልጣን ዘመን ግን "የኢህአዴግ ብቸኛ ፊት" ሆነው ቆይተዋል የሚሉም አሉ። መለስ ስልጣን ጠቅልለው ከመያዛቸውና የድርጅቱ ደምና ደምስር ሆነው ከመኖራቸው ጋር በተያያዘ ኢህአዴግ ሲታሰብ በሁሉም ህሊና የመለስ ፊት ገዝፎ እንዲታወስ ያደረገ አካሄድ ሲከውኑ ኖረዋል ተብለውም ይተቻሉ።

የሆነው ሆኖ "ኢህአዴግ ፊት አልባ ነው !" የሚለው መርህ ከፓርቲው ስራና ስኬት ይልቅ የአባላቱ ስምና ዝና ገዝፎ እንዳይታይ ለማድረግ ሲባል የተወጠነ አሰራር ይሁን እንጂ በቆይታ ኢህአዴግን ውስጠ ድፍን እና ግዑዝ ምስጢራዊ አካል አድርጎ ከህዝብ አራርቆ አቆይቶታል። እንደ ድርጅት ከህዝብ ርቆ የተሰቀለውና አመራሮቹም ሰውኛ ባህሪ የሌላቸው፤ ኢህአዴግ በዚህ መርሁ ወደ ተራው ዜጋ የተጠጋ ስብዕና የፈጠረ አባል አለማፍራቱ ዋጋ አስከፍሎታል የሚሉ ወገኖች አሉ። እንደነዚህ ወገኖች ትንተና አንድ ፓርቲ በሕዝብ የሚወደድ አባል መፍጠር ከቻለ በመልካም ጊዜም ሆነ በፈተና ወቅት ፓርቲውን በህዝብ ግንኙነት ስራ በማገዝ ከህዝብ ዘንድ የሚነሳበትን ተቃውሞ ማብረድ ብቻ የፓርቲውን የተቃውሞና ድጋፍ ሚዛን ሊጠብቅለትም ይችላል።

ያም ሆኖ በኢህአዴግ "ፊት አልባ ፓርቲ" መርህ ግን አባላቱ ወይም ባለስልጣናቱ በአስተሳሰብ ጎልቶ መውጣት ይቅርና ግላዊ ህይወታቸው እንኳን ለብዙዎች ምስጢር ስለሆነ ተመሪው ህዝብ እንዳያውቃቸውና እንዳያምንባቸው እንዲሁም እንዳይቀበላቸው ምክንያት ሆኗል። በአጠቃላይ ድምዳሜ ፓርቲው በኖረበት አሠራር ሳቢያ በችግር ቀን ከአባላቱ መካከል ወደ ህዝብ የሚያቀርበው የተገነባ ሰብዕና ባለመፍጠሩ ከሚመራው ህዝብ ጋር የሚገናኝበትን መስመር በቀላሉ የሚቆረጥ እንዲሆን አድርጎታል።

## ኢህአዴግ 'በአዲስ ፊት'

ዶክተር አብይ የኢህአዴግ ሊቀመንበር ሆነው ከመመረጣቸው ጋር ተያይዞ የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር የመሆናቸው እውነት ሳይታለም የተፈታ ሆኗል። ዶክተር አብይ የአዲሱ ትውልድ የኢህአዴግ አባል ናቸው። ኢህአዴግ አዲስ አበባን ከተቆጣጠረ በኋላ ባለው ጊዜ በብሔራዊ ድርጅታቸው ኦህዴድ በኩል ኢህአዴግን የተቀላቀሉ፣ በተለያዩ የፖለቲካ እና የሙያ ኃላፊነት ቦታዎች ላይ ተመድበው በመስራት በኃላፊነት ዘመናቸው ሁሉ በቀላሉ ሰው የሚቀበላቸው ቅቡዕ መሪ (charismatic leader) መሆናቸውን ያስመሰከሩ ሰው እንደሆኑ ይነገራል። በፓርቲው ውስጥ በቁልፍ የኃላፊነት ቦታዎች ተመድበው የሠሩትን የዶክተር አብይ ስብዕና ከፓርቲያቸው ሰዎች ባለፈ በመረጃና ደኅንነት መረብ ኤጀንሲ እንዲሁም በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የስራ ባልደረቦቻቸው ያውቁ ካልሆነ በቀር እምብዛም በብዙኃኑ ህዝብ ዘንድ የፖለቲካ ሰብዕናቸው የሚታወቅ አልነበሩም።

በኦሮሚያና በአማራ ክልሎች ኢፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል እና የመልካም አስተዳደር ዕጦት እንዲሁም የሥልጣን ውክልና ጥያቄዎች ያስነሱትን ከፍተኛ ህዝባዊ ተቃውሞ ተከትሎ ከኦህዴድ ወገን ወደ መድረኩ ብቅ ያሉት አቶ ለማ መገርሳ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ቦግ እልም እያሉ ወደ አደገኛ አዘማሚያ ሲጓዙ የከረሙትን ብሔር ተኮር የጠባብ ፖለቲካ አዘማሚያዎች ለመመከት ኢትዮጵያዊነትን በተለየ መልክ ማቀንቀን ጀመሩ። ይህም በህዝቡ ዘንድ ተቀባይነት አግኝቶ መልዕክቱ መስተጋባት ሲጀምር በብዙኃኑ ዘንድ ተስፋ የተቆረጠበት የመሠለው የአገሪቱ ፖለቲካ አዲስ ብርሃን ወደ መፈንጠቁ መጣ። የብዙኃኑ ድጋፍ በዚህ ዙሪያ ሲሰባሰብም ፓርቲው በምክንያትም ይሁን በቸልተኝነት ዘንግቶት የኖረውን ኢትዮጵያዊነት ከወደቀበት አቧራውን አራግፎ አዲስ አጀንዳ አደረገው። ይህን ተከትሎ ነው እንግዲህ የዶክተር አብይ ጉልህ ሚና መታየት የጀመረው።

ዶክተር አብይ ብዙኃኑ እንደሚስማሙበትና ከዚህ ቀደም በተለያዩ አጋጣሚዎች ያደረጓቸው ንግግሮች እንደሚመሰክሩላቸው ኢትዮጵያዊነት ከፓርቲ ተልዕኮ አንጻር ሳይሆን ከራሳቸው ጽኑ ፍላጎትና እምነት ጋር የተቆራኘ ጉዳይ ስለነበር አንድም ይህንኑ አጠናክሮ አገሪቱን ከመከፋፈል የቁልቁለት መንገድ ለማዳን፣ በሌላ በኩልም ሁሉንም አስተሳሰብ ወደ አንድ ማምጣት ባይቻል እንኳን በኢትዮጵያዊነት ጥላ ስር ለማሰባሰብ የለውጥ ጅማሮ ንቁ ተዋናይ ሆነው ወደ መድረኩ ብቅ አሉ። በዚህም ያልተጠበቀ እና ተስፋ የተጣለበት የህዝብ ድጋፍ አገኙ። ኢህአዴግን አምርሮ የሚቃወመው የኦሮሞ እና የአማራ ልሂቃን እንዲሁም አራማጆች ጎራ እንኳን በነዚህ 'አዳዲስ ኢህአዴጎች' ላይ ያለውን ተስፋ በአደባባይ መግለጽ ጀመረ።

እነዚህ ሁለት የኦህዴድ ሰዎች የኢህአዴግ ፊቶች ሆነው 'ፊትአልባውን ፓርቲ' መልክ ሊሰጡት ሲነሱ እንዳለፈው ዘመን ከፓርቲው ወገን ያለው የቆየ አስተሳሰብ በቀላሉ አልተዋቸውም። እነአቶ አርከበን የገመገመበትን "ርካሽ ተወዳጅነት" (cheap popularity) የሚል ቃል "ህዝበኛ" (populist) በሚል ተተክቶ ከኢህአዴግ አሰራር ያፈነገጠ አካሄድ ተከትለዋል በሚል በፓርቲው ተገምግመዋል።

ያም ሆኖ አዲሱ አስተሳሰብ ስር ሰድዶ ኢህአዴግ ተከናንቦት የኖረ ካባውን ሲያስገልጠው፣ ወዲህም በግራና ቀኝ የተነሳውን →

ተቃውሞ ለመቆጣጠር ከማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሶ አገሪቱን በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ማስተዳደር ሲጀምር የህዝብን ቀልብ የሚይዝ አስተሳሰብ ማራመድ የሚችል ሰው ከመካከሉ መፈለጉ አልቀረም:: በተለይም የአቶ ኃይለማርያም ከስልጣን መልቀቅ ጥያቄ ፣ በኢህአዴግ ለውጥ የማይታሰብ ነው በሚል ተስፋ መቁረጥ ውስጥ የኖረው አብዛኛው ህዝብ፣ እንዲሁም ፓርቲው ከኖረበት አስተሳሰብ ዘመኑ ወደ 'ሚጠይቀው አሳታፊና ግልጽ አሠራር እንዲሸጋገር ይፈልጉ በነበሩ የገዛ አባላቱ ያደረጉት ግፊት ፍሬ አፍርቶ የአዲስ አስተሳሰብ ለውጥ ንፋሶች እንዲነፍሱ በማድረጉ እነ ዶክተር አብይ ወደፊት መጥተው ህዝቡም በአዲሶቹ ፊቶች እንዲስማማ አደረገው::

ከዚህ በኋላ የነበረው ጉዳይ ኦህዴድ ከሁለት የህዝብ ፍላጎት ከሆኑ አባላቱ አንዱን በአገሪቱ ህግ መሰረት መስፈርቱን አሟልቶ ለጠቅላይ ሚኒስትርነት ማጨት ብቻ ነበር::

ከዚህ በኋላ የተካሄደውን የጠቅላይ ሚኒስትርነት ምርጫ ዶክተር አብይ በከባድ የአሸናፊነት ግምት ቢመሩትም በፓርቲው አባል ድርጅቶች ዘንድ ከባድ ሽኩቻ ማስተናገዱ አልቀረም:: በተለይም በሕወሓት ወገን ዶክተር አብይ ወደ ሥልጣን እንዲመጡ አልተፈለገም የሚል ወሬ መናፈሱ፣ ደኢህዴን አክሮባት ሰርቶ ዶክተር ሽፈራው ሽጉጤን ሊቀመንበሩ አድርጎ መምረጡና ዕጩ ማድረጉ፣ ሕወሓት እጩ እንደማያቀርብ ተገልጾ ሳለ በስተመጨረሻ ዶክተር ደብረጽዮንን ማቅረቡ፣ ብአዴን በመጨረሻው ሰዓት በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርነት ስልጣኑ ላይ ለመቀመጥ በመፈለግ በጠቅላይ ሚኒስትር ውድድር ውስጥ ራሱን አለማካተቱ፣ በመጨረሻም ዶክተር አብይ በሰፊ ልዩነት ተፎካካሪዎቻቸውን ጥለው ወደፓርቲው ሊቀመንበርነት መምጣታቸው ራሱን የቻለ ትርክት ሆኖ በመጨረሻ የዶክተር አብይ ወደቦታው መምጣት ለሁሉም እፎይታ ሆኗል:: ወትሮም ፊታቸው በብዙኃኑ ህሊና የሠረጹ ዛሬ ደግሞ የኢህአዴግ አዲሱ ፊት ሆነው ብቅ ብለዋል::

## ኢህአዴግ ዶክተር አብይን ለምን መረጠ?

በብዙዎች ዘንድ ለጠቅላይ ሚኒስትርነቱ ቦታ ቅድመ ግምት የተሰጣቸው ዶክተር አብይ በመጨረሻ ከተሰጠው 180 ድምጽ ውስጥ 108 በማግኘት የሊቀመንበርነቱን ስፍራ ተቆናጠዋል:: ብአዴን ባለበት ምክትል ሊቀመንበርነት በመርጋቱ ለሊቀመንበርነት ብቻ በተሰጠው ድምጽ አቶ ሽፈራው ሽጉጤ 59 የሕወሓቱ ዶክተር ደብረጽዮን ደግሞ 2 ድምጽ ብቻ በማግኘት ምርጫውን አጠናቀዋል::

እንደሚታወቀው የኢህአዴግ ምክር ቤት 180 አባላት ያሉት ሲሆን በስብሰባው ላይ የተገኙት ከተሰናበቱና በሞት ከተለዩት ውጪ 170 ናቸው:: በስሌቱ መሠረት ዶ/ር አብይ ካገኙት 108 ድምጽ ውስጥ ከ60 ፐርሰንት በላይ ድምጽ ያገኙት ከኦህዴድ ፓርቲ ውጭ ካሉ የኢህአዴግ አባል ፓርቲዎች መሆኑን ቁጥሩ ያመላክታል:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ብአዴን እና ኦህዴድ የአንድ ፓርቲ የበላይነት (የሕወሓት) አለ የሚል አስተሳሰብ ማራመድ ከመጀመራቸው ጋር በተያያዘ ይህንኑ ተጽዖኖ ለመቀልበስ የትብብር መንፈስ ሲያሳዩ ተስተውሏል:: ይፋ የሆነው የምርጫ ውጤትም የብአዴን ተጽዕኖ ከፍተኛ እንደነበር የሚጠቁሙ መረጃዎች ወጥተዋል:: ለምሳሌም የአማራ ክልል የኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽሕፈት ቤት ኃላፊ የሆኑ አቶ ንጉሱ ጥላሁን ምርጫውን በሚመለከት በፌስቡክ ገጻቸው ባሰፈሩት መልዕክት የሚከተለውን ጽፈዋል::

"የኢህአዴግ ምክር ቤት ዛሬ ስብሰባውን ሲያጠናቅቅ ዶክተር አብይ አህመድን ሊቀመንበር አድርጎ መርጧል:: ቀደም ብሎም የአቶ ኃይለማርያምን አርአያነት ያለው የመልቀቂያ ጥያቄ ተቀብሎ አፅድቋል:: በሂደቱ ብአዴን ለድርጅቱ ብቁ መሪ ለመምረጥ የበኩሉን ሚና ተጫውቷል:: መላው የኢህአዴግ አባላት እና የኢትዮጵያውያን ሁሉንም ሂደት ትዕግስት እና አስተዋይነት በተሞላበት ሁኔታ በመከታተል ለነበራቸው አስተዋፅኦ ክብር ይገባቸዋል::"

ጉዳዩ ይህ ከሆነ ዘንዳ ኢህአዴግ በየትኛውም መንገድ ይሁን መጨረሻ ላይ በደረሰበት አጠቃላይ ስምምነት ዶክተር አብይን ለምን መረጠ የሚለው ጥያቄ እዚህ ላይ መነሳቱ አይቀሬ ነው:: ቀዳሚው ምክንያት ዶክተሩ አስቀድመው በገነቡት ስብዕናና በአንደበተ ርቱዕ አቀራረባቸው በውስጣቸው ከያዙት ኢትዮጵያዊነት ስሜት ጋር ተዳምሮ በድጋፍም ይሁን በቅሬታ ውስጥ ተስፋ መፍጠራቸውና የብዙኃኑ ፍላጎት ሆነው መምጣታቸው ነው:: በተለይም በብአዴን ዘንድ እንደሚነገረው ራሱም በግለሂስ በተቀበለው መሠረት የአማራውን ህዝብ ውክልና በአግባቡ አለመወጣት ጉዳይ ጋር ተያይዞ የገጠመው ተቃውሞ ቅቡልነት እንዳያሳጣው በመስጋት አሁን ካለበት የምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርነት ስልጣን ወደ ጠቅላይ ሚኒስትርነት ለመሸጋገር አለመፈለጉ፣ ድምጹንም ሙሉ በሙሉ ለዶክተር አብይ መስጠቱ ለዶክተሩ መመረጥ ትልቁን ድርሻ መጫወቱ ይነገራል::

ከዚህ ጋር ተያይዞ ኢህአዴግ እንደ ፓርቲ በኦሮሚያ የተፈጠረውንና በመላው አገሪቱ ተስፋፍቶ ወደ ከባድ ደረጃ እየተሸጋገረ የነበረውን የህዝብ አመጽ ለማረጋጋት ከኦህዴድ ወገን ሰው ከመምረጥና ስልጣኑንም ለዚሁ ድርጅት ከመስጠት የተሻለ አማራጭ አለማግኘቱ ሌላው ተጠቃሽ ምክንያት ሲሆን ይህንኑም ቢያንስ ሁለቱ ፓርቲዎች (ኦህዴድ እና ብአዴን ) የተስማሙበት መሆኑ ለዶክተሩ መመረጥ ምክንያት እንደ አንድ መላምት ተደርጎ ሊጠቀስ ይችላል::

በሌላ በኩል ዶክተሩ የአሜሪካ ፍላጎት መሆናቸው ወደዚህ ስልጣን ለመምጣታቸው አንዱ ምክንያት ተደርጎ ይወሰዳል:: ከኢትዮጵያ ፖለቲካ ጋር በተያያዘ ስማቸው ቀድሞ የሚነሳው የአሜሪካ ምክትል የውጭ ጉዳይ ኃላፊ የነበሩት ኸርማን ኮኸን የዶ/ር አብይን ጠቅላይ ሚኒስትር መሆን ቀደም ብለው ከተናገሩ "ተንታኞች" ግንባር ቀደሙ መሆናቸው አይዘነጋም:: ይኸም ዶክተር አብይ አሜሪካ ሄደው ከመመለሳቸውና ከኸርማን ኮኸን ጋር መገናኘታቸው ፣ አምባሳደሩም ለአሜሪካ ድምጽ የዶክተሩን መመረጥ እንደሚደግፉ መግለጫ ከመስጠታቸው ጋር ተያይዞ የሚነሳ ጉዳይ ነው::

ያም ሆኖ ኢህአዴግ ዶክተሩን ሲመርጣቸው በብዙሃን ዘንድ እንደሚታመንበት በፓርቲው ፖለቲካ ውስጥ ለውጥ ያመጣሉ ብሎ በማመን አይደለም:: ኢህአዴግ ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው (በመለስ ዜናዊ ላይ የሰራ ባይሆንም) በመርህ ደረጃ በግለሰብ ለውጥ ይመጣል ብሎ የሚያምን ፓርቲ አይደለም:: ይህ ደግሞ ግለሰቦች ያሏቸውን የለውጥ አዳዲስ መንገዶች ተቀብሎ ከመተግባር በእጅጉ የሚያርቀው ነው::

ኢህአዴግ ዶክተር አብይን የመረጠው የህዝብን ቁጣ ከመቀነስ ባሻገር ከፈተና አስተዳደር (crisis management) ፋታ ለማግኘት እና ራሱን ገምግሞ የተጋረጠበትን የመበታተን አደጋ በማስወገድ ወደ አንድ ሃሳብ ለመምጣት ለሚያደርገው ጉዞ በቂ ጊዜ ለመሸመት ነው የሚሉም አልታጡም::

## የጉልቻ መለዋወጥ ተስፋ በድጋፍና ቅሬታ ውስጥ

የዶ/ር አብይን በገኘው ፓርቲ ሊቀመንበርነት መመረጥ በብዙዎች ዘንድ አሁን ካለው የአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ አንጻር በአወንታዊ ዓይን ታይቷል:: ቢያንስ ብዙኃኑ የሚፈልጉትን ሠላም ዶክተሩ እንደሚያረጋግጡላቸው እምነት አላቸው:: በሌላ በኩል ይህንን የዶክተሩን ምርጫ በአወንታዊ መልኩ የሚያዩ ኢትዮጵያውያን የመኖራቸውን ያህል፤ መዋቅራዊ እና ርዕዮተ-ዓለማዊ ለውጥ በሌለበት ሁኔታ የዶ/ር አብይ መመረጥ ጉልቻ ከመለዋወጥ ባለፈ የገኘውን ፓርቲ ፕሮግራም ከማስፈጸም የዘለለ ርባና የለውም የሚሉም ወገኖች አልታጡም:: የሆነው ሆኖ ግን በሁለቱም ዘንድ የዶክተር አብይ መመረጥ ለአገሪቱ ጊዜያዊ ችግሮች ሕክምና ሲባል አማራጭ የሌለው ሂደት እንደነበር ይታመንበታል:: በተለይ የሁሉም ነገር መሠረት የሆነው ሠላምና መረጋጋት ላይ ዶክተር አብይ የሚጫወቱት ሚና የላቀ እንደሚሆን የሁለቱም ወገኖች እምነት ነው::

## የዶክተሩ መጻኢ ፈተናዎች

ብዙኃኑ ኢትዮጵያዊ በዶክተር አብይ ላይ ዕምነቱን ጥሏል:: ሀገሪቱ በረጅም ዘመን የኢኮኖሚ ታሪኳ አስተናግዳው ከማታውቀው ከፍተኛ የዋጋ ንረት እና የኑሮ ውድነት ጋር ተጋፍጣለች:: የሸቀጦች ዋጋ አንዳንድ ጊዜ ከመቶ ፐርሰንት በላይ ጨምሯል:: የብዙኃኑ ህዝብ የመግዛት ዐቅም እና የገበያው ዋጋ አልተመጣጠነም:: ዶክተሩ እነዚህንና ሌሎችም የኢኮኖሚ ጥያቄዎች አፋጣኝ የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ወደ ተረጋጋ ደረጃ እንደሚያደርሱት ይጠብቃል:: በተመሳሳይ የአገሪቱን ሠላምና መረጋጋት እንደ ቀድሞው በመመለስ የብሔር ቁርቋሶ እና ጥላቻን መሠረት ያደረጉ ችግሮች እንዳይፈጠሩ ህዝቡ በዶክተሩ ሙሉ እምነቱን ጥሏል:: ያለፉትን "በመደበኛ የህግ ስርዓት ሂደት ሊፈቱ የማይችሉ" የተባሉ የህዝብ አመጽና ቁጣዎችን

**....አገሪቱን ከመከፋፈል የቁልቁለት መንገድ ለማዳን፣ በሌላ በኩልም ሁሉንም አስተሳሰብ ወደ አንድ ማምጣት ባይቻል እንኳን በኢትዮጵያዊነት ጥላ ስር ለማሰባሰብ የለውጥ ጅማሮ ንቁ ተዋናይ ሆነው ወደ መድረኩ ብቅ አሉ...**

መሠረት በማድረግ በአገሪቱ ላይ የተጣለው አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ተነስቶ ህዝቡም በሠላም ገብቶ የመውጣት መብቱ እንዲረጋገጥለት ይፈልጋል:: በተለይም በኦሮሚያ ክልል አስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ተገን በማድረግ የተወሰዱ እምርጃዎች እንዲቆሙና በወታደሮች የተካሄዱ ግድያዎችም ተመርምረው አጥፊዎች ለፍርድ እንዲቀርቡ ይፈልጋል:: ከዚህ ጋር ተያይዞ የታሰሩ የፖለቲካ እስረኞች ሁሉ እንዲፈቱም የህዝቡ ጽኑ ፍላጎት ነው:: ዶክተር አብይ እነዚህን አስቸኳይ ምላሽ የሚሹ የህዝብ ፍላጎቶች የማስፈጸም ተስፋ ተጥሎባቸዋል::

በረጅም ጊዜ ውጤትም ዶክተሩ እያዘቀዘቀ የመጣውን የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ወደ ጅምሩ የእድገት ጉዞ ለመመለስ፣ አሳታፊ የፖለቲካ ስርዓት እንዲሰፍን የማድረግ፣ ኢህአዴግን እንደ ግንባር ከአንድ ብሔራዊ ፓርቲ የበላይነት እንዲላቀቅ ማስቻልና በብሔራዊ ድርጅቶች መካከል እኩል ተሰሚነትና የህዝብ ውክልና እንዲኖር ማድረግ፣ መከላከያና ደኅንነትን ከአንድ ብሔራዊ ፓርቲ እዝ ስር አላቅቆ የብዙኃን ተሳትፎ ወደ ታከለበት አሠራር ማሸጋገር፣ ዴሞክራሲና ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት እንዲከበር ማድረግ፣ ከተቃዋሚ እና የለውጥ ኃይሎች ጋር ለአንድ አገር ዕድገት ተባብሮ የመሥራት፣ ከምንም በላይ የኢትዮጵያዊነት መንፈስ እንዲያብብ መጣር የዶክተር አብይ ቀጣይ የቤት ሥራዎች ናቸው:: ቁምነገሩ ኢህአዴግ ለዘመናት ሲጠየቅባቸውና ሲወቀስባቸው የኖረባቸውን እነዚህን የለውጥ ጥያቄዎች ዶክተር አብይ በግለሠብ ደረጃ ታግለው ለማስፈጸም ምህዳሩን ያመቻችላቸዋል ወይ የሚለው ጥያቄ ነው:: ይህ ጥያቄ የዶክተሩ ፈተና ሆኖ እንደሚቀጥል ብዙዎች ከወዲሁ ይገምታሉ::



ግርማ ሰይፉ ማሩ

# ዶክተር አብይ አህመድ እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር እና የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ

ባለፈው አቶ ኃይለማሪያም ደሳለኝ በወንበር ገፍ ሥልጣን ሲይዙ "ማዋከብ ሳይሆን ማገዝ አለብን" ብዬ ስሟገት ነበር። ይህን በማለቴ ከፓርቲዬ (ነብሱን ይማርና አንድነት ድንክ ሳይሆን) ጭምር ከፍተኛ ውግዘት ደርሶብኛል። አይቼ አይቼ ሲበቃኝ ደግሞ ከሁለት ዓመት በፊት መሆኑ ነው፤ እባኮትን ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ሥልጣን ይልቀቁ ብዬ ፃፍኩ። ሁለቱም ጊዜ ልክ ነበርኩ። በእርግጥ ከእኔ በተቃራኒ የቆሙትም ቢሆኑ በራሳቸው መለኪያ ልክ ናቸው ብለን ነበር ይኸው ለውጥ የሚባል ነገር አላመጡም፣ ብለው ሊሟገቱ ይችላሉ። ልዩነቱ የእኔ ብጤዎች ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን በተስፋ ዳቦ ኖረናል። በእኔ እምነት አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ላይ ተስፋ እንድጥል ያደረጉኝ ነገሮች ሁሉ ተስፋ ለማድረግ ከበቂ በላይ ነበሩ። እሳቸው ይህን ሊጠቀሙበት አልቻሉም። ይህ በወርቅ ሳሕን ታሪክ የተሰጣቸውን እድል ባለመጠቀማቸው ጥፋቱ የእርሳቸው እንጂ የእኔ እና የእኔ ቢጤ ተስፈኞች ሊሆን አይችልም።

ዶክተር አብይ አህመድ ለኢህአዴግ ሊቀመንበርነት ሲመረጡ በፌስ ቡክ ገፄ ላይ እንዲህ ብዬ ከትቤ ነበር። "ለታሪክ የተፃፈን ሰው ከታሪክ መዝገብ መፋቅ አይቻልም። ከአሁን በኋላ አብይ አህመድ በታሪክ መዝገብ ተፅፏል በደግ ይሁን በክፉ ወሳኙ እርሱና እርሱ ብቻ ናቸው።"

በዚህ መነሻ ዶክተር አብይ በመጪው ለምክር ቤቱ ወይም ደግሞ ለመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ በሚያደርጉት ንግግር በምንም መመዘኛ ዝም ብሎ ለሕዝብ ግንኙነት ፍጆታ ተብሎ የሚደረግ የፖለቲካ ቃላት ድሪቶ መሆን የለበትም። የጠቅላይ ሚኒስትሩ ንግግር ኢህአዴግን እንደ ፓርቲ ከዘመኑ ጋር ሊያቀራርቡት መስራት እንደሚፈልጉ ሊነግሩን ሙከራ ባያደርጉ እመክራለሁ። ይህ የድርጅት የቤት ሥራቸው ስለሚሆን የሚያደርጉት ንግግር በሙሉ መቃኘት የሚኖርበት በጠቅላይ ሚኒስትርነት እና የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ በመሆናቸው የሚያደርጉት ንግግር መሆን ይኖርበታል። ይህን ካልተረዱት የውድቀታቸው መጀመሪያ ይሆናል። ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማሪያም መውደቅ የጀመሩት "የመለስን ራዕይ አስቀጥላለሁ"፣ "ዘላለማዊ ክብርና ሞገስ ለታላቁ መሪ"፣ ወዘተ ማለት ሲጀምሩ ነው። ተስፋ ሳንቆርጥ አሻራዎን ያኑሩ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ብንልም አልሰሙን። መጨረሻቸው ይህ ሊሆን።

ዶክተር አብይ ኢህአዴግን ለሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን የሚሆን ፓርቲ ማድረግ ለእኔ እና ለእኔ መሠል ዜጎች አንድም የሚፈይደው ነገር እንደሌለው መረዳት አለባቸው። ይህ ለፓርቲ አባሎቻቸው ማድረግ የሚገባቸው ንግግር ነው። እኛ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር በንግግራቸው ውስጥ እንዲያካትቱት የምንፈልጋቸው ነገሮች አሉ። ዋና ዋናዎቹን በመጠቆም ኃላፊነቴን ለመወጣት እሞክራለሁ።

የኢትዮጵያ አገራችን ፖለቲካ በመንግስት ሚዲያ ሠላም፣ ሠላም በሚሉ ዘፈኖች፤ እንዲሁም በቴሌቪዥን በሚበሩ ነጫጭ ወፎች የሚገኝ አይደለም። የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፈውስ የሚያገኘው፣ ሁሉም ዜጋ በአገሬ ጉዳይ ያገባኛል ብሎ በመረጠው መስመር መደራጀት እና ሀሣቡን በነፃነት ለህዝብ ማቅረብ ሲችል። ሀሣቡን የሚያቀርብበት መድረክ ደግሞ ክፍት እንዲሆን ማድረግ የመንግስት ሃላፊነት ነው። ባለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት ይህ ሊሆን ባለመቻሉ በነፍጥ ያሸነፉት ቤተ-መንግሥት በገቡ ማግስት ሌሎች ደግሞ ጥራኝ ጫካው፣ ጥራኝ ዱሩ ብለው ነፍጥ አንስተዋል። ይህ ሁኔታ ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ እንዲቀለበስ በማንኛውም ሁኔታ ነፍጥ አንስተው ሥርዓቱን ለመጣል የተሰለፉትን ቡድኖች ወደ ሠላማዊ መድረኩ እንዲመጡ ከልብ የመነጨ ከፖለቲካ ብልጣብልጥነት የፀዳ ጥሪ መደረግ ይኖርበታል። የሂደቱን ታማኝነት ለማረጋገጥ ደግሞ ገለልተኛ የሆኑ አካላት እንዲሳተፉበት ማድረግ ክብር ያሰጣል እንጂ ውርደት ሊሆን የሚችልበት አንድም ምክንያት አይኖርም። ይህን ጉዳይ መምራት የክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ኃላፊነት ነው። በሴራ የተካኑ የቀድሞ ፖለቲከኞች በፍፁም ከዚህ ተግባር ለአገር ፖለቲካ ድህነት ሲባል መራቅ ይኖርባቸዋል። ቢቻል በፈቃዳቸው ገለል በማለት ሥራቸውን እንዲያቀሉላቸው ጥሪዬን አቀርባለሁ።

በአገር ውስጥ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኙ የፖለቲካ ኃይሎችም ሆኖ ሌሎች ለመንቀሳቀስ ፍላጎት ያላቸው ሁሉ በአገር ውስጥ መንቀሳቀስ እንዲችሉ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠር የግድ መሆኑን ያህል፤ በግል ጥቅም (ሥልጣን፣ ገንዘብ ወይም ሌላ ሊሆን ይችላል) ተነሳስተው ሕዝብን አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል እንቅስቃሴ ለማድረግ ፍላጎት ያላቸውን ኃይሎች ለመቆጣጠር እና ለማጋለጥ የሚያስችል ጠንካራ የሲቪል ማኅበራትና የሚዲያ ተቋማት ሚናቸውን ማሳደግ ያስፈልጋል። አሁን የተጫነባቸው የፍርሃት ቆፈን በጠቅላይ ሚኒስትሩ ንግግር ተስፋ እንዲጫርባቸው ያስፈልጋል። ሲቭል ማኅበራትም ሕዝቡ አማራጮችን ገምግሞ እንዲወስን ውሣኔውን ደግሞ መቼና እንዴት እንደሚያደርግ ማስተማር እንዲችሉ ድጋፍ ማድረግ የግድ ነው።

ዜጎች የተሳሳተ አማራጭም ቢሆን የመምረጥ መብት አላቸው። ይህ መብታቸው ሊከበር ይገባል። በተጨማሪ፤ የክልል መንግስታት ነፃነት ሊከበር እና ፌዴራል መንግስቱ ደግሞ በጥብቅ የሰብዐዊ መብት አያያዛቸውን ሊከታተል እንደሚገባ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ማስገንዘብ ይኖርባቸዋል። የክልል መንግስታት የፖለቲካ ነፃነት ለአካባቢያቸው ዕድገት ብቻ ሳይሆን ለሠላማችን ጭምር ወሳኝ ግብዓት ነው። የፌዴራል መንግስቱ ከማገዝ የዘለለ ሚና ሊኖረው አይችልም። የመድበለ ፓርቲ ሥርዓት የሚወለደው በክልሎች እንደሆነ በግሌ ይሰማኛል።

ከላይ ከተገለፁት አጭር ፖለቲካዊ ጉዳዮች በተጨማሪ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዲያነሷቸው የሚጠበቀው፤ ምን አልባት በተሻለ ያስቀምጡታል ብዬ የማስበው ኢትዮጵያዊያን ያለን ማኅበራዊ ግንኙነት በዘርና ብሔር መከፋፈል እንደሌለበት ይህም ከከፍታችን ያወርደን እንደሆነ እንጂ የሚጨምርልን ነገር አለመኖሩን፣ ሁሉም ዜጋ አገሩ የጋራ መሆኑን አፅዕኖት ይሰጡታል ብዬ አምናለሁ። ኢትዮጵያዊነታችን የሚደምቀው በማኅበራዊ ግንኙነታችን ውስጥ እንጂ ባለን የፖለቲካ ልዮነት ወይም አስተሳሰብ ሊሆን አይገባም።

ከሁሉም በላይ በአገራችን ኢትዮጵያ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ዕድገት ተመዝግቧል እየተባለ፤ አንዱ በፎቅ ላይ ፎቅ ሲደርብ ሌላው ለምፅዋት እጁን የሚዘረጋበት የኢኮኖሚ ሥርዓት መፍረሱን ማብሰር አለባቸው። ፍትሓዊ ተጠቃሚነት ሲባል፣ ዜጎች በኢኮኖሚ ደረጃ መለያየት መኖሩን ማስወገድ የማይቻል ቢሆንም ልዩነቱ ግን በጥረት የሚመጣ እንጂ ከባለሥልጣን ጋር በመሻረክ እና የእገሌ ዘር በመሆን እንደሌለበት መሰመር ያለበት እና ሁሉም ኢትዮጵያዊ ለሥራ ታጥቆ እንዲነሳ ሊያበረታቱት ይገባል። ፍትሓዊ ያልሆነ ተጠቃሚነት ምንጩ የፖለቲካ ሥርዓት በመሆኑ ይህ ደግሞ ቀድሞ ማኅበራዊ ግንኙነታችንን ቀጥሎም ደግሞ ሥርዓቱን እንደሚገረሰሰው ፍንትው ብሎ ታይቷል። መቼም ይህ ያልተገለፀለት የኢህአዴግ አባል ካለ ችግር ላይ መሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል።

ባለፈው ሶስት ዓመታት በአገራችን በፖለቲካው ውጥንቅጥ መንስዔ ማህበራዊ እሴቶቻችን እንዲሁም የኢኮኖሚ መሠረቶቻችን አደጋ ላይ ወድቀዋል። ስለዚህ ፖለቲካውን በማከም አገራችንን ከውድቀት ልንጠብቃት የግድ ይለናል። ማንኛውም ዜጋ ደህንነቱ የሚረጋገጠው ኢትዮጵያዊ መንግሰት ሲኖር መሆኑን በማመን የእኔ ብሔር መከላከያ፣ የእኔ ብሔር ደህንነት ካልሆነ አደጋ ላይ እወድቃለሁ ከሚል ስጋት ነፃ እንዲሆን ማድረግ የመጪው ጠቅላይ ሚኒስትር ትልቁ ሥራ ነው። የመከላከያ እና የደህንነት እንዲሁም የፖሊስ ተቋማት በሙሉ ለዜጎችና ለአገር ደህንነት እንጂ ለአንድ ቡድን ታዛዥ የሚሆኑበት ሥርዓት ማክተም ይኖርበታል። የዜጎችን ሃሣብ የሚሰልል ተቋም አያስፈልገንም። ዜጎችን ከውጭ ጠላት የሚጠብቀን ሠራዊት ያስፈልገናል። በአገልግሎታችሁ እንኮራለን የምንላቸው የሠራዊት አባላት ይናፍቁናል። በትምህርት ቤት የሠራዊት ቀን ተብሎ ዩኒፎርም ለብሰው ልጆቻችን ፎቶ ሲነሱ ለማየት ይናፍቀናል። የኢትዮጵያ መለዮ ለባሾች ልብስ ዜጎችን ማስፈራሪያ መሆኑ ማብቃት ይኖርበታል።

መልካም የሥራ ዘመን ክበር ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ

# “የኢትዮጵያ እስር ቤቶች ትልቅ የስቃይ  ቦታዎች ናቸው”

## ወጣት ዮናታን ተስፋዬ



ዮናታን ተስፋዬ በቅርብ አመታት ውስጥ ብቅ ካሉ ወጣት ፖለቲከኞች መሃል አንዱ ነው። በ1990ዎቹ መጨረሻ የነበረውን የቅንጅትና የህብረት እንቅስቃሴ በትኩረት ሲከታተል ከቆየ በኋላ በ2005 ዓ.ም በኢ/ር ይልቃል የሚመራውን ሰማያዊ ፓርቲን ተቀላቀለ።

“በወቅቱ የነበረው የፓርቲው ራዕይ ጥርት ያለና የኢትዮጵያን ፖለቲካ አንድ እርምጃ የሚያራምድ ነበር” የሚለው ወጣት ዮናታን በጊዜ ሂደት ከፓርቲው አንዳንድ መርሆችና እንቅስቃሴዎች ጋር የእሱ እሳቤ ባለ መግጠሙ ዘግየት ብሎ ራሱን ለማግለል ቢዳረግም የሰማያዊ ፓርቲ የህዝብ ግንኙነት ሃላፊ በመሆን ሰርተዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ በልዩ ስሙ ፈረንሳይ ለጋሲዮን ተብሎ የሚጠራው አካባቢ ተወልዶ ያደገው  ዮናታን ተስፋዬ ከሶስት አመት እስር በኋላ (የተፈረደበትን እስር ለመጨረስ 48 ቀን ብቻ ሲቀረው) በቅርቡ እንዲፈታ ተደርጓል። ወጣቱ ፖለቲከኛ የእስር ቤት ቆይታውንና አጠቃላይ የህይወት ተሞክሮው ምን እንደሚመስል አእንዲህ ባለ መልኩ **አቅርበነዋል።**

**ግዮን፡- በህግ አካላት የተያዝከው መቼና በምን አይነት አጋጣሚ ነበር?**

ዮናታን፡- የተያዝኩት ካዛንቺስ አካባቢ ነው። በማደርገው የፖለቲካ እንቅስቃሴ ቀደም ብለው ሲከታተሉኝ ሰንብተዋል። ምሽት 12 ሰአት ላይ በሰብአዊ መብት ጥሰት ዙሪያ ውጭ ከነበረ አንድ አካል ጋር መረጃ ስለዋወጥ ነው የያዙኝ። በዛ ሰአት ሰውን ማሰር የሚቻል አይመስለኝም ከህግ አኳያ፤ እኔ በተያዝኩበት ወቅት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ህግ አልነበረም።

**ግዮን፡- ተመሳሳይ በሆነ ሁኔታ በተያዝክ ማግስት ምሽት ላይ ነበር ፍርድ ቤት የቀረብከው?**

ዮናታን፡- ትክክል። በ18 ተይዤ በ19 ምሽት 12 ሰአት ካለፈ በኋላ ነው ፍርድ ቤት የቀረብኩት። ይሄ አካሄድ የነበረውን የእኛን ክስ ሰው እንዳያውቅ ተብሎ የተደረገ ይመስለኛል፤ እነሱ ሌላ የራሳቸው ምክንያት ሊኖራቸው ይችላል።

**ግዮን፡- ፍርድ ቤት ስትቀርቡ የተነበበላችሁ ክስ ምን ነበር?**

ዮናታን፡- እሱ ነው አስቂኙ ነገር፤ የመጀመሪያው ክስ ሲመጣ የግንቦት ሰባት አባል በመሆን፣ጎንደር አካባቢ ሴሎችን በማዋቀር፤ ከዚህ ከአዲስ አበባ በዛ በኩል ልጆች እየመለመልክ ትልካለህ  የሚል ነበር። በዚህ ምክንያት  ለአራት ጊዜ የ28  ቀን ቀጠሮ እየተጠየቀብኝ ተመላልሻለሁ፤ ከአራት ወር ስምንት ቀን የማዕከላዊ ቆይታ በኋላ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ስቀርብ ሌላ ክስ ተቀየረ፤ አዲሱ ክስ ደግሞ ‹‹ኦነግ በኦሮሚያ ዙሪያ ያስነሳውን የሽብር እንቅስቃሴ ተልዕኮ ለማስፈፀም፤ አመፅና ብጥብጡን ሲያስቀጥልና ሲያበረታታ፣ ሲመራ የነበረ ነው›› ተብሎ መጣ።

የምርመራ ሂደቱ ላይ ምንም አይነት ማስረጃ ሊያገኙብኝ ስላልቻሉና ክሱ የፈጠራ እንደሆነ ስለሚያውቁ ፤መጨረሻ ላይ በግልፅ በአደባባይ የፃፍኳቸው  በጊዜው ወጣቶች ተቃውሞአቸውን በምን መልኩ ማድረግ እንዳለባቸው የሚገልፀውን፤ ብሎም በማስተር ፕላኑ ሂደትና በአጠቃላይ ስርአቱ እያረጀ መሆኑን የገለፅኩበት ፅሁፍ በዝርዝር የክስ ማስረጃ ወይም ክስ ሆኖ ነው የቀረበው።

**ግዮን፡- በምራመር ወቅት ማዕከላዊ የነበረው ሂደት ምን ይመስላል? በተለይ እዛ በዙሪያህ የነበሩ እስረኞች ላይ የታዘብከውስ ነገ ምን ነበር?**

ዮናታን፡- ማዕከላዊ ከባድ የፈተና ቦታ ነው። እንዲሁ በግርድፉ ምስሉን ለመስጠት ያህል በዛ ቦታ ሰው ሲሞት፣ ሰው አካሉ ሲጎድል፣ዘሩ ሲመክን፣ ቤተሰቡ ሲበተን አይተናል። ኢብራሂም የሚባል የሐረርጌ ልጅ ራቁቱን ቆሞ እየተመረመረ ስፖርት ሲያሰሩት ከኋላው በኩል ብልቱን ስበው ጥለውት መክኗል። ፖሊስ ሆስፒታል ሄዶ ተመርምሮ ብልቱ የማይሰራ ሆኖ ወጥቷል። ከድብደባ ብዛት በኩላሊቱ በኩል ተጎድቶ ሽንት የሚሸና ልጅ ነበር፤ እንዲህ አይነቱ ግፍ ሲፈፅም እኔም ሆንኩ ሌሎች አብረውኝ የነበሩ ታሳሪዎች አይተናል።

በጊዜው ይሄንን ነገር በማየታችን ብሎም ከቤተሰብ እንዳንገናኝ በመደረጉ 28 ቀን እንደቆየን በጊዜው የረሃብ አድማ አደረግን። 15 ሰው በሚይዝ ቤት ውስጥ 25 ሆነን ነው የታሰርነው፤ ይሄ ሲከሰት እኔና አቶ በቀለ ገርባን ጣውላ ቤት አስቀመጡን፤ መጀመሪያ ሳይቤሪያ የሚባለው ቦታ ነበር የነበርነው። በጊዜው እነሱ ሌላ ምክንያቶች ቢሰጡንም ዋናው ነገር ግን በዜጎች ላይ  የሚደርሰውን በደልና ስቃይ እንዳናይ ነበር።

ያስገቡን ጣውላ ክፍል ከላይ የምርመራ ቤት ስለነበር ሰው በእለት ተዕለት ሲደበደብ፣ ሲወድቅ፣ ሲነሳ እንሰማለን። የካቲት 30 ቀን እንዲህ ባለ ሁኔታ ነው የሰው ህይወት ያለፈው።

**ግዮን፡- ባልከው ቀን የሞተውን ሰው ታውቁታላችሁ…? ህይወቱ ማለፉንስ በምን እርግጠኞች ሆናችሁ?**

ዮናታን፡- ጥሩ ጥያቄ ነው። የሞተውን ሰው ማንነት አናውቅም። ሰዎች ለምራመራ የሚያልፉት እኛ ባለንበት  በኩል ነው። በእለቱ ሰውየው በዛ በኩል ነው ወጥቶ ወደ መርመራ ክፍል የገባው፤ ከምሽቱ 2፣30 እራት ስንበላ የተጀመረው ድብደባ እስከ ሌሊቱ ስድስት ሰአት ነው የቀጠለው። ይጮሀል፣ ይወድቃል፣ ያጓራል፣ ይነሳል፣ ይወድቃል ይሄንን ታዝበናል። ሌላ ጊዜ ምርመራው ሲያልቅ መልሰው እየጎተቱ ወደ ነበረበት የሚመልሱት በእኛ በኩል ነው፤ከላይ ጣውላ ስለሆነ ሁሉም ነገር ይሰማናል። እኛ መጀመሪያ ላይ ፌንት ያደረገባቸው መስሎን ነበር፤ ረጅም ሰአት ጠበቅን አልነቃም፤ ቢነቃ ኖሮ

እኛ ባለንበት በኩል ነበር የሚያልፈው፤እንቅልፍ ሳንተኛ ቁጭ ብለን ስንከታተል ነው ያደርነው፤ ይሄንን ጉዳይ ስናነጋግራቸው ‹‹እንዲህ ሊደረግ አይችልም፤ እናጣራለን.. የምናውቀው ነገር የለም›› ከማለት ውጪ የተደረገ ነገር የለም፤ እንደውም ይሄን በማለታችን በድጋሚ ቦታ ቀየሩን፡፡

በዚህ መልኩ ብዙ ነገሮችን ታዝበናል፤ አንዲት ለረጅም ጊዜ ማህጸኗን በእጇ ደግፋ በከዘራ የምትራመድ ከሻሸመኔ የመጣች ልጅ ነበረች፡፡ ልጅቷ ተደብድባለች፤ ይሄ ሳያንስ መደፈሯ ያስታውቃል፡፡ ያለችበትን ሳይኮሎጂካሊ ሁኔታ በግልጽ ታየዋለህ፡፡ እኛ የታሰርንበት ጣውላ ቤት ሴቶች ከታሰሩበት ቤት አጠገብ ስለነበረ ውጪ ሲንቀሳቀሱ በደንብ እንከታተላቸው ነበር፤ ከዚህ ውጭ አቶ በቀለ ገርባ የህክምና ባክ ግራውንድ ያለው በመሆኑ ነገሮችን ታዝበን ለመረዳት አይቸግረንም፡፡

የውስጥ እግራቸው ተገርፎ ጠባሳው ያለቀቃቸው ሰዎች ነበሩ፤በሲባጎ እጃቸው ታስሮ ውስጡ ተሰርስሮ ጠባሳው እስካሁን ድረስ ያለ ልጆች ብዙ ናቸው፤ ካቴና የለም ተብሎ ቁርጭምጭሚታቸው የተሰበሩ ልጆች አሉ፤ ብዙ ግፍ ነው በቦታው የሚፈመው፤ ግን ይሄ ሁሉ ለነፃነት የሚከፈል ዋጋ ነው ፤ይሄ ሁሉ ለሰብአዊ መብት፣ ለእኩልነት የሚከፈል ዋጋ ነው፡፡

**ግዮን፡- እሰቲ የፍርድ ሂደቱን ወደ ኋላ መለስ ብለህ አጫውተን?**

ዮናታን፡- እኔ ላይ የቀረበው ማስረጃ በህገ ወጥ መንገድ የተገኘ ነው፤አንደኛ ግለሰቡ ቃል መስጠት ካልፈለገ አልፈለገም ነው፤ እጅግ አሰልቺና አታካች የሆነ ጭቅጭቅ እኔ ላይ ተካሂዷል፡፡ ሌሎች በድብደባ ጭምር ነው የተመረመሩት ፤በሆነ መንገድ ነው ቃላችንን እንድንሰጥ የተገፋነው፤ ከፌስቡክ ኢንቦክስ ውስጥ፣ ከኢሜሌ ውስጥ ያሉ ነገሮችን ነው እንደ ማስረጃ ለፍርድ ቤት ያቀረቡት፤ አንዳንዶቹን በማስረጃነት ባይቀበላቸዉም፡፡ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሳያሳዩ ያለ ፍቃዴ ነው ከኢሜሌ ያወጡት፡፡ ፓስ ወርድህን ሲቀበሉህ በጉልበት ነው፤ እኔን እንዲህ ባለ መልኩ ባይቀበሉኝም ኢሜሌ ውስጥ ግን እንዴት እንደገቡ አላውቅም፡፡ የፍርድ ሂደቱ መጀመሪያ ላይ ስድስት አመት ከስድስት ወር ነው ያስወሰነብኝ፤ በኋላ ይግባኝ ብዬ ወደ ሶስት አመት ከሶስት ወር ዝቅ ብሏል፡፡

**ግዮን፡- ወደ ቂሊንጦ የተዘዋወርከው መቼ ነበር? እዛስ ከሰአብአዊ መብት አንፃር ምን ገጠመህ?**

ዮናታን፡- ቂሊንጦ ግንቦት 28/2008 ዓ.ም ነው የገባሁት፡፡ እዛ አንድ አመት ነው የቆየሁት፤መጀመሪያ ዞን ሁለት የሚባል ግቢ ነበር የገባሁት፡፡ እዛ ከተለያየ አካባቢ የሚመጡ ሰዎች አሉ፡፡ ከእነሱ ጋር ታወራለህ ትጨዋወታለህ፤ ያ ደስ አላላቸውም መሰል ልዩ ጥበቃ የሚባል ቤት ወሰዱኝ፡፡ ጨለማ ቤት ነው የሚባለው፤ ምንም አይነት ፋሲሊቲ አልነበረውም፡፡ ከዞን ሁለትና አንድ በአጠቃላይ አስር ሰዎችን 75 በ15 ሴንቲ ሜትር የሆነች ጠባብ ቤት ውስጥ አስገቡን፡፡ እነ በቀለ ገርባም እዛው ነበሩ፤ አንድ አመት የተቀመጥነው እዛ ቤት ውስጥ ነው፡፡ በብዙ ጭቅጨቃ ቤተሰብ እንዲጠይቀንና ሌሎች ነገሮች እንዲገቡልን የተደረገው ራሳችን ላይ ወስነን ለዘጠኝ ቀን የረሃብ አድማ ካደረግን በኋላ ነው፡፡

ከዚህ ክርክር በኋላ ነገሮች ሲስተካከሉልን ነሐሴ 28 የእሳት ቃጠሎው ተነሳ፡፡ በጊዜው አተት ተከስቶ ነበር፤ የማረሚያ ቤት ሃላፊዎች በዚህ የተነሳ ‹‹የቤተሰብ ምግብ አትቀበሉም፣መንግስት ለእናንተ በቂ ምግብ ያዘጋጃል›› አሉ፤ እነሱ ይሄን ያሉት ለእኛ አስበው ሳይሆን በአጋጣሚው ከቤተሰብ ጋር እንዳንገናኝ አመቺ አጋጣሚ ስለነበር ነው፡፡ ይሄንን ውሳኔ ደግሞ አብዛኛው እስረኛ አልተቀበለውም፤ በመጀመሪያ ቀን መግባባት ስላልተቻለ ሃላፊዎች ዝም ብለው ሄዱ፡፡ በሁለተኛው ቀን ውይይትም እስረኛው ሃሳቡን አልተቀበለም፤ያኔ አስተዳደሩ “ምንም አታመጡም፤ውሳኔውን መቀበል ግዴታ ነው” አሉ፡፡ ታራሚው ደግሞ “ለጤናችን ጠንቅ የሆነ ደረጃውን ያልጠበቀ ምግብ አንበላም” ብሎ ምግብ አቆመ፤ ያን ቀን ጠዋት ቁርስ ተመለሰ፡፡ ሰው በዚህ መልክ ይጮሃል “አንበላም አናግሩን” ይላል፤ አስተዳደሮች ያኔ በሩን ዘግተው “ይጩሁ፣ ምንም አያመጡም” የሚል አቋም ነው የያዙት፡፡

ከአዳራሽ ውጪ ያሉ ካፍቴሪያዎች የተነሳ እሳት ወደ አዳራሹ ተያይዞ ነው ዞን ሁለትና ዞን ሶስትን ለውድመት የዳረገው፡፡ ዞን 3፣ዞን2፣ ዞን1 ውስጥ ከዛ እሳት ለማምለጥ ይሞክሩ የነበሩ ሰዎች በጥይት እየተመቱ ወድቀዋል፤ በጊዜው ይሄ ነገር በስፋት ተነግሯል፡፡ እነሱ 23 ሰው ሞቷል አሉ እንጂ የሞተው ከዛ ይበልጣል፡፡ የነበረው ተኩስ በጣም ያስፈራል፤ቀለሃዎች ሲረግፉ ይሰማናል፡፡ በኋላ ላይ አስለቃሽ ጭስ ተተኮሰ፤ የሚገርመው በእኛም በኩል ተተኩሷል፤ ለምን እንደተኮሱት ባይገባኝም፡፡ ከፊት ለፊታችን የነበረው ዞን አንድ ቤት እሳቱ አልደረሰም፤ እሱ ቤት ተቃጥሎ ቢሆን ኖሮ እኛ በህይወት መትረፋችንን አላውቅም፡፡ ብዙዎቻችን በህይወት የቆየነው በእግዚአብሄር ፍቃድ ነው፡፡

**ግዮን፡- ከእነ በቀለ ገርባ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በቂሊንጦ ድብደባ ተፈፅሞብህ እንደ ነበር በጊዜው ተነግሯል፤ ምክንያቱ ምን ነበር?**

ዮናታን፡- ጥቅምት 2009 ዓ/ም ነው፤ በወቅቱ እነ አቶ በቀለ ፍርድ ቤት ይሄዱ ነበር እነሱ ደግሞ “ፍርድ ቤቱ ጉዳያችንን ያለ አግባብ ይዞብናል፤ ፍትህ ሊሰጠን አይችልም፡፡ ስለዚህ ወደ ፍርድ ቤት አንሄድም” የሚል አቋም ይዘዋል፡፡ ይሄ መብታቸው ነው፤ ይሄ ኢ-ፍትሃዊነትን የምትቃወምበት አንዱ መንገድ ነው፤ ይሄን ሲያደርጉ ወታደሮች እያንገላቱና ሰአብዊ መብታቸውን እየጣሱ መሬት ለመሬት እየጎተቱ ካቴና አጠለቁላቸው፡፡ በዛ መሃል ዱላ መማታት ጀመሩ፡፡ በተለይ አዲሱ ቡላላን አንዱ ከኋላው በዱላ ይመታዋል፤‹‹ለምን ትመታዋለህ? ምን አደረገ?” ብዬ ስጠይቅ እነሱን አስወጡና ሁሉም ዱላውን ወደ እኔ አዞረ፡፡

እግረ መንገድ ቂማቸውን፣ በቀላቸውን፣ ቁጭታቸውን ነው የተወጡብኝ፡፡ በካቴና ታስሬ ቁጭ ያልኩኝ ነኝ፤ አፍሪካ ውስጥ ነው ያለነው ብለህ አስበህ ቅጣት ነው ቢባል እንኳ አንድና ሁለት ሰው እኔን ለመደብደብ በቂ ነበር፡፡ ከሀያ በላይ የሚሆኑ ሰዎች መልኩ እኔ ላይ ጥቃት መፈፀሙ በጣም የሚያሳዝን ነገር ነው፡፡ እኔ ግን ይሄ ሁሉ ነገር ደርሶብኝ የበደሉኝን ሰዎች በይቅርታ ነው ያለፍኩት፡፡ አጠቃላይ ስርአቱ እንዲለወጥ፣ እንዲህ አይነት ነገር ዳግም በሌሎች ላይ እንዳይፈጸም የምታገል በመሆኑ በደሌ መማሪያ ከሆናቸው በይቅርታ ነው ማለፍ ያለብኝ፤ ምንም እንዳልተፈጠረ አድርጌ ትቼዋለሁ፡፡

**ሰዎች ለምራመራ የሚያልፉት እኛ ባለንበት በኩል ነው፡፡ በእለቱ ሰውየው በዛ በኩል ነው ወጥቶ ወደ መርመራ ክፍል የገባው፤ ከምሽቱ 2፤30 እራት ስንበላ የተጀመረው ድብደባ እስከ ሌሊቱ ስድስት ሰአት ነው የቀጠለው፡፡ ይጨሀል፣ ይወድቃል፣ ያጓራል፣ ይነሳል፣ ይወድቃል**

**ግዮን፡- በወጣትነት እድሜህ ፖለቲካ ውሰጥ ጉልህ ሚና እያበረከተክ ነው ያለኸው፤ በተደጋጋሚ በመንግስት የሚዲያ ተቋማት ተደጋግሞ ‹‹ወጣቶች ሰከን በሉ›› እየተባለ ነው፤ አንተ ካለህበት ሁኔታ አንፃር ወጣትነትና ፖለቲካን እንዴት ትገልፀዋለህ?**

ዮናታን፡- አሁን መንግስት አካባቢ የሚሰራው ፕሮፓጋንዳ ወጣቱን እንደ አንዳች ስሜታዊ ሃይል ብቻ የመቁጠር ሁኔታ ነው የሚታየው፤በርግጥ ፖለቲካ ያለ ስሜት አይሰራም፡፡ ግን ዝም ብሎ ማንም እየተነሳ የሚነዳው፣ ማሰብ የማይችል አድርገው የሚስሉት ነገር አለ፡፡ ወጣት በአለም ደረጃ የለውጥ ሃይል ነው፡፡

መለስ ዜናዊና ጓደኞቻቸው በረሃ ሲወጡ ወጣቶች ነበሩ፤ዛሬ ከስርአቱ ጋር አርጅተው አገሪቱን አንለቅም ያሉት ሰዎች በወጣትነት እድሜያቸው ነው ደርግን በትጥቅ ትግል ፊትነውና ጥለው ስልጣን ላይ የወጡት፡፡ ከ20 አመት በላይ ወጣቱ እንዳይነቃ፣ በዩኒቨርሲቲ አካባቢዎች የነበሩ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች እንዲዳከሙ ሲደክሙ የነበረበት መንገድ እየከሸፈ መጥቷል፡፡ አሁን ያንን ነገር ለማዳፈንና ወጣቶች ነገርን በዝምታ እንዲያልፉ ለማድረግ ነው እየሞከሩ ያሉት፤ ግን ይሄ የሚሆን ነገር አይደለም፡፡

ወጣቱም ሆነ ቀሪው የህብረተሰቡ ክፍል ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በአገሩ ጉዳይ ንቁ ሆኖ ያገባኛል እያለ ነው፤ በስርአቱ ወላጆች ሳይቀሩ ተማረዋል፡፡ እንኳን ልጆቻቸውን ተው ብለው ሊመክሩ ‹‹በርቱ፣ወደ ፊት ግፋ›› ነው የሚሉት ፤በተለያዩ ጊዜ እኔን ሊጠይቁ ከመጡ ትላልቅ ሰዎችም የተመለከትኩት ይሄንን ነው፡፡ ስለዚህ የተሻለች ኢትዮጵያን እንድናይ ሰፋ ያለ አስተሳሰብ፣ የይቅርታ ልብ ይዞ ወደ ፊት ሊያራምድ የሚችል ሰላማዊ የሆነ ትግል ወጣቱ እንዲከተል ነው የምመክረው፡፡

**ግዮን፡- ከቂሊንጦ ወደ ዝዋይ ከተዘዋወርክ በኋላ ያለው የእስር ቤት ጊዜህ ምን ይመስላል? ከቤተሰብ ራቅ ስትል ሁሉ ነገር ያስቸግራልና ያ ጊዜ እንዴት አለፈ?**

ዮናታን፡- ዝዋይ ከቂሊንጦ የተለየ ነገር የለውም፤ እዛም እዚም ያሉት ሰዎች የአስተሳሰብ ቀለማቸው አንድ ነው፡፡ ዝዋይን ከቂሊንጦ ለየት የሚያደርገው ለቤተሰብ እጅግ በጣም ፈታኝ መሆኑ ነው፡፡ ቦታው ይርቃል፣ በርሀ ነው፣ መንገዱ አይመችም፡፡ የመኪና አደጋ በየቀኑ የሚደርስበት ሁኔታ ስለነበር ቤተሰብ ጠይቆን እስኪመለስና ደህና መግባቱን እስክናረጋግጥ ድረስ እረፍት አልነበረንም፡፡ ይሄ ትንሽ የሚከብድ ነገር ነው፤ እንደ አጠቃላይ ግን ኢትዮጵያ ውሰጥ ያሉ እስር ቤቶች ዝዋይም ይሁን ሸዋሮቢት፣ ቂሊንጦም ይሁን ቃሊቲ ህግ የሌለባቸው ቦታዎች ናቸው፡፡ እንደ ተፈለገ ልትደረግ የምትችልባቸው ቦታዎች፤ መጠየቅ ለምን ? ማለት የማትችልባቸው የስቃይ ቦታዎች ናቸው፤ ይሄ እንዲለወጥ ከመስራት ውጭ ምንም አማራጭ የለንም፡፡

በሌላ መልኩ እስር ቤት የተማርንበት ቦታ ነው ማለት እችላለሁ፡፡ በሰብአዊ መብት ጥሰት ዙሪያ ውጪ ሆነን ስንጮህ የነበረበትን ጉዳይ እዛው እስር ቤት ውስጥ በተግባር ደርሶብን በፊት ለፊት ለመታዘብ ችለናል፡፡ አሁን ከዚህ በኋላ በልበ ሙሉነት ልናወራበት ልንናገረው የምንችለው ጉዳይ እንደሆነ በአጋጣሚው ለመመልከት በቅተናል፡፡ እስር ቤት የምታየው ነገር በጣም አስከፊ ቢሆንም ለምታደርገው ትግል የቤት ስራ የሚሰጥህ፣ ጉልበት የሚሆንህ መልካም ገፅታም እንዳለው መገንዘብ ችያለሁ፡፡

# ፍትሐዊው መሪ



**ሁሴን ከድር**

በቀድሞው መሪ ኑዛዜ መሠረት ነበር መንበረ ሥልጣኑ ላይ እንዲቀመጥ የተደረገው። ለሥልጣን ቅንጣት ጉጉት የለውም። መንበረ ሥልጣኑ ላይ እንደተቀመጠ ሚስቱን ጠርቶ ምርጫ ሰጣት ‹‹እዚህ ቤተ-መንግሥት ውስጥ ተቀምጬ ሕዝቤን ቁልቁል እያየሁ መምራት አልፈልግም። በአንጡራ ሐብቴ በገዛኋት መሬት ላይ የጭቃ ቤት ሠርተን እንድንኖር ፈቃድሽ ከሆነ አብረን እንኑር አ... ይይ ካልሽ ደግሞ መንገዱን ጨርቅ ያርግልሽ። አንቺ ድሎትን የለመድሽ የንጉስ ልጅ ነበርሽ። አባትሽ አሁን ስልጣኑን ለኔ አስተላልፎ ሞቷል። እኔ ደግሞ ሥልጣንን አባትሽ በያዘበት መንገድ አልይዝም። ...ምን ትያለሽ?›› አላት።

‹‹ምን ልታደርግ አስበህ ነው?››

‹‹በዚህ ቤተ-መንግሥት ሥልጣንን ተገን አድርገው በቀድሞው ንጉስ ወቅት የራሳቸውን ጥቅም ሲያካብቱ የነበሩ ልዑላንና ከፍተኛ ሹማምንት በሙሉ ያለአግባብ የሰበሰቡትን ገንዘብ አስመልሳለሁ። አንቺም ብትሆኚ የወሰድሽው ትመልሻለሽ። እርምጃውን ከራሴ ነው የምጀምረው። አባትሽ ባሰራው የተንጣለለ ቤተ-መንግሥት ውስጥ መኖር አልፈልግም። ለባለሥልጣናት ትርፍ ደሞዝ አልሰጥም። የኔንም ደሞዝ የሚበቃኝን ብቻ ነው የምወስደው......

‹‹እስካዛሬ ሳውቅህ ከነበረው የተለየ ነገር አላየሁም። በሃሳብህ እስማማለሁ። ከጎንህ ነኝ›› አለችው።

የቀድሞው መሪ የቀብር ሥነ,ሥርዓቱ እንደተፈጸመ ለዚህ ወራሴ መንግሥት በጌጣጌጥ ያሸበረቀ ፈረስ ከነአጀቡ አቀረቡለት። ‹‹ይህ ምንድነው?››

‹‹ንጉስ ሆይ ከዚህ በኋላ መሪያችን ነህ ክብርህን የሚመጥን መጓጓዣ ያስፈልገሃል›› አሉት።

‹‹አልፈልግም። እኔ በዚህ አልሄድም›› በማለት የራሱን ፈረስ ካሰረበት ፈትቶ ጋለበ። ወደ ቤተ-መንግሥቱ በመሄድም በውስጡ የነበሩ ውብና ውድ ቁሳቁሶችን ከቤተ,መንግሥት በማስጋዝ ግምጃ ቤት ተመዝግቦ እንዲገባ አስደረገ። እጅግ በርካታ ሃብት ከቤተ-መንግሥቱ ወጣ። ከፋርስ ፣ከሮም የተገዙ ልብሶች፣የፈርጥ ቀለበት ምንጣፎች ፣የቅንጦት እቃዎች ፣መመገብያ ውድ ሳህኖች.... በሙሉ ከቤተ-መንግሥቱ ተወገዱ። የንጉሱ ልጆች ሥልጣኑን ቢመኙትም አባታቸው ለሴት ልጁ ባል በማውረሱ ለወዲያው ምንም ማድረግ አልቻሉም። በእጃቸው የሚገኙ ውድ ሃብቶች እንዲያስረክቡ ተጠየቁ።

አዲሱ ንጉስ ውደሥልጣን ከመምጣቱ በፊት በወር ይከፈለው የነበረው አርባ ሺ ዲናር ብሎም ያጠራቀም የነበረውን ገንዘብ በሙሉ ለግምጃ ቤት አስረከበ። የሚስቱ ውድ እቃዎች ፣የወርቅ ቀለበቶች የአባቷ ሥጦታ ሳይቀር ግምጃቤት አስጋዘ። ንጉስ ሆኖ የአመት ደሞዙ አራት መቶ ዲናር ብቻ እንዲሆን አስወሰነ። በዘረፋ፣ የተሰበሰበ የቀድሞው ንጉስ ሹማምንት፣ወይም የንጉሱ ልጆች ሃብት መውረስ ብቻ ሳይሆን ‹‹ንብረት ተወርሶብኛል የምትል በግዛቴ ሥር ያለህ ሕዝብ ሆይ አለኝ የምትለውን ንብረት መጥተህ ውሰድ። ›› ብሎ በአዋጅ አስነገረ።

ሃብት ንብረታቸው በግፍ የተወረሱ በሙሉ አቤት በማለታቸው በማስረጃ አለኝ የሚሉትን ንብረት አስመልሷል። ቅንጦት የለመዱ፣የሰው ሃብት ማጋበስ፣መዝረፍ፣መንቦጣረር የሚመኙ ሁሉ ሽብር ቤታቸው ገባ። የሚይዙ የሚጨብጡትን አሳጣቸው። ዘመዶቹን እየፈለጉ ሽምግልና ላኩበት። ሆኖም ማንም ከዘራፊዎች የተሰበሰበን ሃብት መልስ ብሎ የሚያሸማግል ቤቱ እንዳይመጣ ብሎ መለሳቸው። ሕዝቡን ሰብስቦም ‹‹የቀደሙት መሪዎች ሥልጣን አስረክበውኛል። ወሊድም ሱለይማንም ንብረታቸውን ሃገር እንዳስተዳድርበት በቤተ-መንግሠት ውስጥ አኑረውልኛል። የነሱን ሃብት አልፈልግም። ሁሉንም ወደግምጃቤት አስገባለሁ ፣እቅዴ ሕዝብን በፍትህ ማስተዳደር ነው። ለዚህ እንድትተባበሩኝ እፈልጋለሁ። የሰው ንብረት የወሰዳችሁ አሁንም መልሱ። የሚገባችሁንም ንብረት ብቻ ያዙ።›› አለ። ከዚህ ዓለም ጥቅማጥቅም ራሱን አገለለ።

ግምጃቤት የተከማቸውን ሃብት ለተራቡ ድሆች፣ለአልጋ ቁራኛ በሽተኞች፣ ለታረዙ ሰዎች፣ቀለብ ላጠራቸው የሙት ልጆች፣ባሏ ለሞተባት፣ ከሃገሩ ለተሰደደ፣ ለተገፋ፣ ለአቅመ ደካማ፣ የቤተሰቦቹን ጉሮሮ መሸፈን ላልቻለ ለባለብዙ ቤተሰብ አባላት ላሉት አባወራ....፣ እየተፈለገ ይሰጥ ጀመር። ድሃ በሃብታም ቤት ሃቅ አለውና ሃቁን እንዲወስድ አመቻቸ። ይህ ተረት አይደለም፣ይህ የፈጠራ ታሪክ አይደለም፣ይህ የምኞት ታሪክ አይደለም በትናትናዋ ሂጃዝ ከተማ የተፈጠረ እውነተኛ ታሪክ ነው።

የመሸንገያ ስጦታዎችን፣ጉቦ የሚመስሉ ማማለያዎችን አልቀበልም አለ። ሌላው ቀርቶ ዑመር በሚመገበው ምግብ ላይ አቋም ወሰደ። ምግቡ ክብርና ሞገሱን በሚያስይ ደረጃ የሚዘጋጅ ከሆነ ላለመብላት ወሰነ። ከቶም በሃገሪቱ በድህነት ደረጃ ላይ የሚገኙ ሰዎች የሚመገቡት ምግብን ሆነ የሚመርጠው። የዚህን ሰው ታሪክ በሚያሳይ አንድ ፊልም ላይ ከቶም ደረቅ ቂጣ በውሃ እያራሰ ሲመገብ ያሳያል። ኢራቅ፣ግብጽ፣ሶርያ በአጠቃላይ የአረብ ልሳነ ምድር በሱ የአስተዳደር እዝ ሥር የነበሩ ሀገራት ናቸው። ከዛሬ 1300 ዓመታት በፊት የነበረ ንጉስ ነው።

ሥልጣን ኃላፊነት እንጂ ክብርና የሃብት ማጋበሻ ሥልት እንዳልሆነ ለዓለም ሕዝብ ያስመሰከረ ሰው ነበር። ይህ ሰው ነብይ አይደለም ወይም በነብይ ዘመን የኖረ ሃዋርያ አይደለም፣ራዕይ የተገለጸለት ቅዱስ ሰው አይደለም። ሕዝብን በፍትህ ላስተዳድር ያለ ቤተሰቦቹ በንግስና ወንበር ላይ የነበሩ የድሆች ብሶት የመዲና ከንቲባ በነበረበት ዘመን ጀምሮ የተረዳ አንድ ግለሰብ ነው። አያት ቅድመ አያቱ ንግሥናን ያጣጣሙ፣ አጎቱ ከልጆቹ አስበልጦ ሀገራትን እንዲያስተዳድር ቁልፉን ተናዞለት የሞተ ድንቅ ሰው ነበር። ይህ ዓለም ዛሬም ድረስ ዝናውን የሚዘክረለት መሪ ዑመር ኢብኑ አብዱልአዚዝ ይባላል። ቅድመ አያቱ ሁለተኛው ከሊፋ ዑመር ኢብኑል ኸጣብ ነበር።

ዑመር ሁለተኛ የነበረውን ደረጃ የተመለከቱ የታሪክ ምሁራን አምስተኛው ከሊፋ እስከማለት ደርሰው ነበር። ይህን ሰው ለዘመናት ስመኝ ኖርያለሁ። ምናልባት ላቲን አሜሪካ ውስጥ በቅርቡ ያየናቸው መሪ ካልሆኑ በቀር በዓለም ታሪክ እሱን የሚያክሉ ሌሎች መሪዎችን አላየንም። ወይም አልሰማንም። የ21ኛው ክፍለዘመን ቅዥት ትሉኝ ይሆናል። ግን በሕዝብ ጫንቃ ላይ የተሾመ መሪ ተምሳሌቱ የህዝብን ደም እየመጠጡ ጫንቃቸውን ያደለቡ መሪዎች ሳይሆኑ ለፍትህ የቆሙ፣ ሕዝብን በእኩልነት ያስ ተዳደሩ፣ከራሳቸው፣ከቤተሰባቸው፣ከጎጣቸው፣ከዘ ራቸው ይልቅ ለሃገራቸው፣ለሕዝባቸው ብሎም ለሰው ልጅና ለዓለም ደህንነት የሚተጉ ሆነው እንድናያቸው ነው ምኞታችን።

እንዳለመታደል ሆኖ እስካሬ በሃገራችን ታሪክ ለግልና ለወገናቸው ጥቅም ያልቆሙ የምንላቸው መሪዎች እምብዛም አላገኘንም። የኢትዮጵያን ሕዝብና የሀገራቸውን ታሪክ ለመለወጥ የተፍጨረጨሩ አልነበሩም ለማለት ሳይሆን በኔ መረዳት ተጠልፈው የወደቁ ብዙ ነበሩ። ይህ ታሪክ እንዲቀየር እንፈልጋለን።

መሪዎች ሥልጣን ላይ እንደተንጠለጠሉ ‹ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል› የሚለውን አሉታዊ ይትበሃል ከመዝገባ ቃላቸው ካልፋቁ በቀር የመሪነት ሞገስን ሳይሆን የሌብነት ውርደትን ነው የሚጭኑት። በሥልጣን መንቀዝ ማለት የግድ የወረቀት ገንዘብን ማካበት አሊያም ጥሬ ሃብትን ማግበስበስ ብቻ ላይሆን ይችላል። አቅም ባለው ሰው ሀገሪቷ እንድትተዳደር ከማድረግ ይልቅ ለ‹እከክልኝ ልከክልህ› ወዳጅ ዘመድን፣ወገን ጎጥን፣ያገር ልጅ....እየተባለ ዙርያን ማጠር የሚመጣ ከሆነ ከንቅዘትም በላይ ንቅዘት ነው።

ሀገር ልትመራ የሚገባው በየሙያ ዘርፉ ትክክለኛ በሚባል ሰው እንጂ በኮታ በወር ተራ ተጠብቆ ‹‹እስካሁን እኔ ቦጥቡጫለሁና ተራህን ዝረፍ›› ሊሆን አይገባውም ማለት ተራ ወሬ ሊመስል ይችላል። ግን 27 ዓመታት የተጓዝነው በዚህ የኮታ ድልድል ነበር። ዛሬ ይህ መሆኑ ኢትዮጵያን ወደኋላ እንጂ አንድ ጋት ወደፊት ሊያራምዳት አይችልም።

ሥልጣን እያንዳንዱ ግለሰብ አምሮቱን የሚጠረቃበት ማዕድ አይደለም። በየትኛውም መንገድ ቢሆን ለየትኛውም ኃላፊነት ላይ የሚቀመጥ ሀገርን ከፊቱ ሊያኖር ይገባዋል። አሁን አገራችን በአዲስ የመንግሥት መዋቅር ሥር አርፋለች። ህዝብ የትኛውንም መሪ በጥርጣሬ ነው የሚያየው። ሁሉም የራሱን አጀንዳ የሚያስፈጽምለትን እንጂ ‹ከኔ እከሌ ይባልጣልና የወንድሜ ችግር ከተፈታ የኔ እንደተፈታ እቆጥረዋለሁ› የሚል እምብዛም አይገኝም። መሪም ሁሉንም ለማስደሰት አይሮጥም 50 በመቶ ከተስተካከለ እሰየው ነው፡፡ ኢህአዴግ ዛሬም የሕዝብን ጥቅም ወደጎን ብሎ የድርጅቱን ሃብት ማካበጫ እና የሹማምንቱን ከርስ መሙያ የሥልጣን መደላድል ካመቻቸ ወደቀደመው ጸባችን መግባታችን አይቀርም። ከምንም በፊት ሕዝብ ይቅደም ከምንም በፊት ሀገር ትቅደም። መኩሪያ መከበሪያችን ሀገራችን እንጂ ጎጣችን፣ዘራችን፣ ዘመዳችን አይደለም። ሀገራችንን በዓለም አደባባይ ከፍ እንድትል እንድተሰሩ እንጠይቃለን። ቦርጫችሁ እንዲገፋ ኪሳችሁ እንዲወፍር ማጀታችሁ እንዲሞላ ከሆነ ወንበሩ ላይ ተቀመጣችሁት ለሌላ ዙር መረበሽ ራሳችሁን እያዘጋጃችሁ እንደሆነ አትርሱ። የህዝብ ብሶት ይብቃ። ሀገራችን ትለምልም።

ሰላም በምድራችን ላይ ይስፈን።



በኃይሉ ገ/እግዚአብሔር

# «በጨለማ ውስጥ ያላችሁ ውጡ!»

‹‹የፈረንሳይ መንገድ ጉቦ ተበላበት፤
የኮተቤም መንገድ ጉቦ ተበላበት፤
የአስኮውም መንገድ ጉቦ ተበላበት፤
ያደግንበት መንደር ጉቦ ተበላበት፤
ባንተ መበዝበዜን ለማን ልበል አቤት!?››

…እግዚሃር ይይለትና ሳልወድ በግድ አንድ አጠገቤ ተቀምጦ የነበረ ጠጪ እንገሩጉሮውን አጋብቶብኝ ሄደ፡፡ …ሲያናድድ! እህ ቢሉት እኮ አዲስ አበባን ጨርሶ፣ የክልሎቹን አውራ መንገዶች አዳርሶ ድልድይና ግድቦችን ሲጠቃቅስ ያመሽ ነበር፡፡ …ነገረኛ!

‹‹ጉቦ ያልተበላበትን መንደርና መንገድ ብትጠቅስ አይሻልም!?›› ብሎ ያ ሰውዬ ኩም ባያደርገው ኖሮ ጅቡቲ ይደርስ ነበር፤ … ይኼ ወሽካታ!

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ መሰብሰብን የማይከለክልባቸው ሥፍራዎች ቢኖሩ መጠጥ ቤቶች ብቻ ናቸውና ዛሬም መጠጥ ቤት ውስጥ ነኝ፡፡ የቀበሌ 23 ‹ማደግ በጥረት› የሸማቾች የኅብረት ሥራ ማኅበር›› ድራፍት ቤት ውስጥ፡፡ … ሦስተኛ ጃንቦዬን አጨብጭቤ ከማዘዜ… አንድ አዕምሮውን የአንዳንድ ኃይሎች መጠቀሚያ ያደረገ ሰው እንዲህ አለ፡-

‹‹ይህ ቀበሌ የጠቀመኝ ድራፍት ቤቱ ብቻ ነው!››

ባለማመን ‹‹እ!?›› አልኩት፤ እ!? ብቻ፡፡ የ‹‹እ!?›› ትርጓሜም፣ ‹‹ምን እያልክ ነው አንተ ፖለቲከኛ!?›› የሚል ነበር፡፡

‹‹እደግመዋለሁ፤ ይህ ቀበሌ የጠቀመኝ ድራፍት ቤቱ ብቻ ነው!›› አለ ሰውየው ፊቱን ወደኔ መልሶ፡፡ ብስጭቴ በረታ፡፡ በብስጭት ለመናገር ግን ያጎደልኩት ሦስተኛ ጃንቦ በቂ አልነበረምና እላዩ ላይ ሁለት ካከልኩበት በኋላ እንዲህ አልኩ፡- ‹‹ማን ነህ አንተ ይህ ቀበሌ የጠቀመኝ ድራፍት ቤቱ ብቻ ነው ያልክ!?›› ጥያቄዬ የሆነ የቀበሌ ሹም ቅላፄ ነበረው፡፡

‹‹አቤት!›› አለ ተናጋሪው ሳያፍር ከተቀመጠበት እየተነሳ፡፡

እግዚኦ! ይህን የሚያህል ቁመቱን የት ከቶት ኑሯል ጎበዝ!? ‹‹ለምድን ነው እንደሱ ያልከው?›› አልኩ በተቻለ መጠን እንዲፈራኝ ድምፄን አስፈሪ ለማድረግ እየጣርኩ፡፡

‹‹ስለሆነ ነዋ!››

‹‹ምኑ?››

‹‹ይህ ቀበሌ የጠቀመኝ ድራፍት ቤቱ ብቻ ነው!››

ተናደድኩ፡፡ ቀድሞ ከመናገሩ፣ መድገሙ አበሳጨኝ፡፡ ፈራሁም፡፡ ድምፄን ከሹምነት፣ አንደበቱን ስካር ወዳሰረው ጠጪ ቀይሬ ‹‹ነውር ነው፤ እንደሱ አይባልም!›› አልኩ፡፡

‹‹ቀበሌ ሌላ ምን አገልግሎት ይሰጣል?›› ይባስ ብሎ በጥያቄ አፋጠጠኝ፡፡ ሰውየው የሚለቀኝ አልሆነም፡፡

‹‹ሲጀመር ወረዳ እንጂ ቀበሌ የሚባል የለም!›› አልኩ አሁን ደግሞ ስካር ካሰረው አንደበት ወደ ትሁት የበታች አገልጋይ ድምፄን ቀይሬ፡፡

‹‹ወረዳም በለው ቀበሌ ምን እንደሚሠራ እኔ አላውቅም፤ አንተ የምታውቀው ካለ ተናገር!›› ይባስ ብሎ ትከሻውን በግዴለሽነት እያማታ ዐይኑን አፈጠጠብኝ፡፡

‹‹ቢያንስ ቢያንስ በራሱ ተነሳሽነት ልደት እና ሞት ይመዘግባል!›› አልኩ አንደበቴ ያመጣልኝን ተናግሬ ለመገላገል ያህል፤ (ከገባው የወሳኝ ኩነት ምዝገባን ማለቴ ነበር)

‹‹ልደቱስ እሺ፤ ሞቱን ማን አመጣው?››

ኸረ ጉድ መጣ፤ እዩልኝ ዓሣ ጎርጓሪ ዘንዶ ሲያወጣ፤ ‹‹ይሄ ሰውዬ የፖለቲካ እሥረኞች ተፈቱ ሲባል፣ ሌላ እሥረኛ የማይገባ መሰለው እንዴ!?›› አልኩ ድፍረቱ ያለቅጥ ቢገርመኝ፡፡ ‹‹ስማ! እዛው እሥር ቤት ቁጭ ብለህ ብቻህን እንደ ቀውስ ታወራታለህ እንጂ መግባትህ አይቀርም!›› ልለው አስቤ ከአፌ መለስኩት፤ ይህቺን ዓይነቷን ድፍረት የማመጣው አሁን ከጠጣኋት ስድስት ጃንቦ ላይ ሁለት ሳክልባት ነው፡፡ ወዲያው እንደ ሃይማኖት አባት አንገቴን ወደ እሱ ሰብሬ፣ ‹‹ወንድሜ ትሰማለህ!?›› አልኩት፤

‹‹አቤት!›› አለ አሁንም በልበ ሙሉነት፡፡

‹‹ልደትን የፈጠረ ፈጣሪ፣ ሞትን እንደፈጠረ አታምንም? … ስለምን በፈጣሪ ላይ ትዘባበታለህ?›› አልኩት፡፡

‹‹በምድሩ ጌታ ተለማምዳችሁ፣ ከላይኛውም ጋር ልታቃቅሩን ነው!?›› አለኝ ውስጡ እልህ ይሁን ስካር ባመጣው ቁጡነት፡፡

ተዚህ በላይ መነጋገር አልፈቀድኩም፡፡ ‹‹ማነህ እዚህ ጋ!›› አጨበጨብኩ፡፡ አስተናጋጁ መጣ፡፡

‹‹ሒሳብ ስንት ነው!?›› እጄን ወደ ደረት ኪሴ እየከተትኩ ጠየቅኩ፡፡

ድምፄን የሹም ባስመስል አልተፈራሁም፤ ትሁት የበታች አገልጋይ ባስመስል አልተፈራሁም፤ የሃይማኖት አባት ባስመስል አልተፈራሁም፤ ሹምም ሞገስ በሌለው አገር፤ የበታች አገልጋይም ሞገስ በሌለው አገር፤ የሃይማኖት አባቶችም ሞገስ በሌላቸው አገር በከንቱ መድከሜ በእርግጥም እኔ ነበርኩ ጥፋተኛው፡፡

‹‹ስማ!›› አለኝ አንዱ እግሬ ከመጠጥ ቤቱ ደጃፍ መውጣት ሲጀምር፤

‹‹አቤት!››

‹‹ልደት እና ሞት የምትመዘግቡት ቁስለኛውን ለማን ትታችሁት ነው?››

‹‹በሕግ አምላክ!›› አልኩ በንግግሩ ማዘኔን ለመግለፅ ያህል፡፡

‹‹ሰውዬ! ሕግ እንኳን መጠጥ ቤት መንበሯ ላይም የለች!›› አለ የአንድ አሺፊ ጠጪ ድምፅ፡፡ ተናጋሪውን ዘወር ብዬ አየሁት፡፡ ያለቅጥ ጥውልግ ድቅቅ ያለ ሰውዬ ነው፡፡ የሆነ የድሮ ፍራንክ የሚመስል ነገር፡፡ የሆነ እንደ ጉንዳን ጭንቅላቱ ብቻ የሚታይ ዓይነት፡፡ ሰው እንዴት ደፋር ሁኗል?!

‹‹ስማ!›› አልኩት እኔ፤

‹‹አቤት!›› አለ ሰውየው እንደመሳቅ እየከጀለው፤

‹‹ኋላ ነግሬሃለሁ፤ ወህኒ ለመውረድ ዕድሜ እንጂ ኪሎ አይጠየቅም፤ …ዋ!››

‹‹እንዴ! አሁንስ ያለሁት የት ነው?›› አለ ዐይኑን ቁልቁል የተጎሳቆለ የራሱ ሰውነት ላይ እያመላለሰ፡፡ …በለው ድፍረት! በለው ፖለቲከኛነት! ‹‹እንዴ! አሁንስ ያለሁት የት ነው?

… በዚያ መከረኛ ወቅት የሆነ ነው አሉ፡፡ የአዲስ አበባ ሰው ሁሉ በየቤቱ በተከተተበት አስፈሪ ምሽት ጥንቅቅ ብሎ የሰከረ አንድ የእኔ ቢጤ ጅብራሬ መሀሉን የመኪና መንገድ ይዞ እያቀራራ፣ እያንጎራጎረ፣ እየጮኸ፣ ቆላና ደጋ እየረገጠ ይሄዳል አሉ፡፡ በዚህ መሀል ሁለት የፀጥታ ኃይሎች አገኙት፡፡ እንኳን ሌሊት ሆኖ በቀንም የሰዉ እንቅስቃሴ የተገታበት ጊዜ ነበርና ፀጥታ ኃይሎቹ ተናደውበታል፡፡ ከተማዋ እንዲህ ባለ ጭንቅ ተይዛ እሱ ሰክሮ በመለፋደዱ በግነዋል፡፡

‹‹ና አንተ!›› ጠራው አንደኛው፡፡

‹‹አቤት!›› አለ ሰውየው ቀብረር ብሎ ስካር ያዝ ባደረገው አንደበት፡፡

‹‹ለምንድነው አካባቢ የምትረብሸው? ፀጥ ብለህ አትሄድም?››

‹‹ምን ጎደለብኝና ፀጥ እላለሁ?›› አለ ትከሻውን በትዕቢት እያማታ፡፡

‹‹ነው?›› አለና በጥፊ አጮለው፡፡

‹‹አባል እኮ ነኝ!›› አለ መታወቂያውን ለማውጣት እጁን ወደ ኪሱ እየሰደደ፡፡

‹‹የምን?››

‹‹የፓርቲ ነዋ!››

‹‹እና ብትሆንስ!?›› አለና ሁለተኛው በጠረባ ዘረረው፡፡ ሰውየው መሬት ላይ እንደተነጠፈ እንዲህ አለ አሉ፤

‹‹ኸረ ጉድ ነው፤ ሳንሰማ መንግሥት ተቀየረ እንዴ!?››

… ይህ ደቃቃ ሰውዬም፡- ‹‹ሕግ እንኳን መጠጥ ቤት መንበሯ ላይ የለችም!›› ባለ ጊዜ አዕምሮዬ ደጃፍ ላይ መጥቶ የተገተረው ሐሳብ ይኸው ነው፤ ‹‹ኸረ ጉድ ነው! ሳልሰማ መንግሥት ተቀየረ እንዴ!?››

… ከዚህ ነገረኛና ተናግሮ አናጋሪ ከሞላበት መጠጥ ቤት ወጣሁ፡፡ የራሴን መከፋት እና ማዘን እያሰላሰልኩ የምተክዝበት ሥፍራ ስፈልግ ከፊት ለፊቴ ያለው ቤተ- ክርስቲያን ትዝ አለኝ፡፡ ሔድኩ፤ ተሳልሜ ገባሁ፡፡

‹‹በጨለማ ውስጥ ያላችሁ ውጡ!›› እያለ ሰባኪው ይሰብካል፡፡ ከንፈሬን በሐዘን እየመጠጥኩ፣ አንገቴን እንደ ቫዮሊን ተጫዋች ወደ ጎን ሰብሬ፣ ቀልቤን ሰብስቤ ስብከቱን እያዳመጥኩ ነው፡፡

‹‹እነሆ በጨለማው ዓለም ያላችሁ ወገኖቼ ሆይ ውጡ! እውነት እውነት እላችኋለሁ እናንተ በጨለማ ግዛት ውስጥ ያላችሁ ወገኖቼ ሆይ ውጡ!››

በዚህ መሀል ከጎኔ ያለ አንድ አማኒ ወደ ጆሮዬ ተጠግቶ፡- ‹‹አዬ! ቪዛ ቢገኝማ አሁኑኑ ነበር ጥርግ ማለት!›› ብሎኝ እርፍ፡፡ ከዚህ በላይ ጆሮዬን ለዚህ ሰውዬ ማዋስ አልፈለኩም፡፡ ቤተ- ክርስቲያኒቱን ከነስብከቷ ጥዬ ውልቅ!

‹‹የፈረንሳይ መንገድ ጉቦ ተበላበት…›› ኦኦይ! ያ ሰካራም እግዚሃር ይይለት አቦ! ይኼን የማይረባ የሙስና ሪፖርት፣ ግጥም ብሎ ካፌ ጋር ሰፋው፡፡ እንዴት ልገላገለው!? እህ!

‹‹የኮተቤም መንገድ ጉቦ ተበላበት፤
የአስኮውም መንገድ ጉቦ ተበላበት፤
ያደግንበት መንደር ጉቦ ተበላበት፤
ባንተ መበዝበዜን ለማን ልበል አቤት!?››



በታምራት መርጊያ

# የቀለም አብዮት እና ኢትዮጵያ

እንደየአገራቱ ዘዬና ወግ ስሙን እያበጃጁ ይጠሩታል። የቀድሞዋ ዩጎዝላቪያ ፌዴራላዊት ሪፐብሊክ ዜጎች እ.ኤ.አ በ2000 ያካሔዱትን ሕዝባዊ የተቃውሞ እንቅስቃሴ "የቡልዶዘር አብዮት" የሚል ስያሜ ሰጥተውታል፤ ጆርጅያዎች ደግሞ በ2003 "የፅጌረዳ አብዮት"፤ ዩክሬኖችም በፊናቸው በ2004 "ብርቱካናማው አብዮት" ሲሉ ጠርተውታል። ሌሎችም ደግሞ እንዲሁ እንደየአገራቸው ዘዬና ወግ ስያሜ እየሰጡ ያሻቸውን ይሉታል። ይህ ሁሉ እንግዲህ በአሁኑ ወቅት በአገራችን ኢትዮጵያ እየታየ ነው ተብሎ በመንግሥት የተነገረለትን "የቀለም አብዮት" ለመግለፅ ነው።

የቀለም አብዮት ጉዳይ ግድ የሚላቸውና በቅርበት የሚከታተሉት፣ እንደነ ጀስቲን ራይሞንዶ እና ሚካኤል ሊንድ የመሳሰሉ የምዕራቡ ዓለም የፖለቲካ ልኂቃን እንደሚገልፁት ከሆነ፣ የቀለም አብዮት እንቅስቃሴ ንድፈ ሐሳብ የተፀነሰውና አስቀድሞ የታየው እንደ ጎርጎሮሳዊያኑ የዘመን ቀመር በ1986 በደቡብ ምሥራቅ ኤዥያዋ ሐገር ፊሊፒንስ "ቢጫ አብዮት" (the Yellow Revolution) በሚል ስያሜ እንደነበር ይገልፃሉ።

በአንፃሩ የተለያዩ የምዕራብ ዓለም ታዋቂ የመገናኛ አውታሮች እንደሚገልፁት ከሆነ ደግሞ፥ የቀለም አብዮት በቀድሞዋ የሶቪየት ኅብረት አካላት በነበሩ እንደነ ዩጎዝላቪያ፣ ጆርጅያ እና ዩክሬን የመሳሰሉ አገራትና የባልካን አገራት ተብሎ በሚጠራው የምስራቅ አውሮፓ ክፍለ ግዛት የሚገኙ አገራት ውስጥ እ.ኤ.አ ከ2000 ጀምሮ እንደመነጨ በስፋት ይገለፃል።

የዚህ ዓይነት ሕዝባዊ የተቃውሞ ማዕበል ተሳታፊዎች የትግል ስልት በዋነኝነት በንብረትም ሆነ በሰው ሕይወት ላይ ጉዳት ሊያስከትል በማይችልና ጥፋት አልባ የሆነ ሕዝባዊ የተቃውሞና የእምቢተኝነት (non-violent resistance) እንቅስቃሴን በመተግበር፤ ሙሰኛና ጠቅላይ (authoritarian) ነው ብለው ባመኑትን መንግሥትና የፖለቲካ ሥርዓት ላይ ከባድ ፖለቲካዊ ጫና ማሳረፍ፣ ብሎም የሥርዓት ለውጥ ለማምጣትና ዴሞክራሲን ለማስፈን የሚደረግ ሕዝባዊ የትግል ስልት እንደሆነ ይገለፃል።

በተለምዶ የቀለም አብዮት በተካሔደባቸው ሐገሮች እንደተስተዋለው ከሆነ ደግሞ የተለያዩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (NGOs) እና የተማሪ የመብት ተሟጋች ቡድኖች (student activists) የቀለም አብዮት እንቅስቃሴን በማደራጀትና በማስተባበር ረገድ የሚኖራቸው ከፍተኛ ሚናና አበርክቶ የአንበሳውን ድርሻ የሚይዝ ሆኖ እናገኘዋለን።

የቀለም አብዮት ነገር ፈፅሞ ምቾት ከማይሰጣቸው አገራት ውስጥ የቭላድሚር ፑቲኗ ራሺያ፤ ግምባር ቀደም ተጠቃሽ ናት። በአንድ ወቅት ፕሬዚዳንት ፑቲን የቀለም አብዮትን አስመልክቶ ሲናገሩ "በአገሬ ራሺያ የቀለም አብዮት ይሉት ነገር፣ ከቶውንም ደብዛው እንኳን እንዳይታይ በፅናት እከላከላለሁ" በማለት ተናግረው እንደነበር እናስታውሳለን። ፑቲን ምክንያታቸውን ሲያስረዱ እንደተናገሩት፤ በዚህ የቀለም አብዮት የተባለ ከንቱና ጠንቀኛ ነገር መዘዝ፣ በተለያዩ የቀለም አብዮት የተካሄደባቸው አገራት የተከሰቱን አሳዛኝ እውነታዎች በምክንያትነት ይጠቅሳሉ። በተመሳሳይም የመከላከያ ሚኒስትራቸው ሰርጌሾጉ እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ሰርጌላቭሮቭም፣ "የቀለም አብዮት ማለት፣ አዲስ መልክ ያለው በአገር ላይ የሚቃጣ የጦርነት ስልት ነው፤" በማለት የፑቲንን ሐሳብ ያጠናክራሉ። በርግጥም ሩሲያዊያን እንደአገር እንዲህ ያለ ጠንካራ የፀረ-ቀለም አብዮት አቋም ለማራመድና አፀፋዊ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችላቸው ከበቂ በላይ ርዕዮተ-ዓለማዊና ፖለቲካዊ ምክንያቶች አሉዋቸው። ይኸውም አገሪቱ ከምዕራቡ ዓለም ጋር ያላት የፖለቲካና ዓለም አቀፋዊ የኃይል ሚዛንን የመጨበጥ የቆየ ፍትጊያና ቁርሾ ነዉ። በዚህ መነሻም የራሺያ ባለሥልጣናት የቀለም አብዮት፣ የምዕራብ ዓለም አገራት ሕዝባዊ የተቃውሞ እንቅስቃሴን በማፋፋም ለንቅናቄው አካላት ቀለብ እየሰፈሩ በፋይናንስ ጭምር በመደገፍ የርዕዮተ-ዓለምና የፖለቲካ ፍትጊያው አሸናፊ ሆነው ለመውጣት ከመጋረጃ ጀርባ ሆነው የሚዘውሩት የእጅ አዙር እንቅስቃሴ እንደሆነ በፅኑ ያምናሉ።

በአንጻሩ ከዚህ በተቃራኒ ፅንፍ የቆሙ የምዕራብ አለም የቀለም አብዮት ደጋፊና አራማጅ ልኂቃን እንደሚገልፁት ከሆነ ደግሞ፣ የቀለም አብዮት ከሕዝቦቻቸው ጥቅም ይልቅ፣ የግል ጥቅማቸውን በማስቀደም፣ የራሳቸውን ምቾት በሚጠብቁ (kleptocrati cgovernment)፣ በምርጫ ስም የሕዝብ ድምፅ የሚያጭበረብሩና በሙስና የተጨማለቁ ወዘተ. መንግሥታት ላይ በሕዝቦች የሚካሔድ፤ ለውጥን እና ታሐድሶን ግቡ ያደረገ፤ ሰላማዊ የለውጥ እንቅስቃሴ እንደሆነ አበክረው ሲከራከሩ ይደመጣል።

## ኢትዮጵያና የቀለም አብዮት

የኢትዮጵያ መንግሥት የቀለም አብዮት እንቅስቃሴ ጉዳይ ከሚያሳስባቸው መንግሥታት መካከል አንዱ እንደሆነ በተለያዩ ጊዜያት ሲገልፅ መቆየቱ ይታወቃል። ይህንንም የሚያረጋግጥልን በተለያዩ ወቅቶች፣ በተለይም በአገሪቱ ውስጥ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች በሚካሄድበት ጊዜ፣ መንግሥት እራሱ በሚቆጣጠራቸው የተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን አውታሮች ላይ ቀለም አብዮት ካርድን እየመዘዘ ሰፊ ሽፋን በመስጠት ረዘም ላለ ጊዜ የቀለም አብዮት ሊያስከትል የሚችለውን አገራዊ አሉታዊ ውጤቶች የቀለም አብዮት የተካሔደባቸውን የተለያዩ የአለም ሐገራትን አሉታዊ ኩነቶችና መዘዞች በተምሳሌትነት በማጣቀስ ሲያንፀባርቅ እንደነበር መመልከት ይቻላል።

"የፈሩት ይደርሳል፣ ያመኑት ያወርሳ" እንዲሉ አበው፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ይህ የረዥም ጌዜ ስጋቱ፣ ከስጋትነት አልፎ ወደተጨባጭ እውነታነት ማደጉን እንዳመነ በሚያንፀባርቅ መልኩ፣ በአሁኑ ወቅት በሐገሪቱ የተለያዮ ክልሎች ውስጥ ከሚካሔደው ሕዝባዊ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ መግለጫ የሰጡት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ኮማንድ ፖስት ሴክረተሪያትና የመከላከያ ሚኒስትሩ አቶ ሲራጅ ፊጌሳ "በኢትዮጵያ ውስት እየተካሔደ የሚገኘው ሕዝባዊ የተቃውሞ እንቅስቃሴ፣ የቀለም አብዮት መልክ እየያዘ መጥቷል፤" በማለት መግለፃቸው እንደ ማሳያነት ሊወሰድ የሚችል ጉዳይ ነው።

የሆነው ሆኖ በዚህእ ረገድ አጽንዖት ተሰጥቶት መታየት የሚገባው ዐብይ ጉዳይ፣ በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ ውስጥ የሚታየው ሕዝባዊ የተቃውሞ እንቅስቃሴ በመንግሥት እንደተገለፀው የቀለም አብዮት እንቅስቃሴነው ወይ?? የሚለው አንኳር ጉዳይ ይሆናል።

በዚህ ረገድ ሁለት ፅንፍ የያዙ አመለካከቶችን መመልከት ይቻላል። አንደኞቹ የመንግሥትን ሐሳብ በመደገፍ፥ የቀለም አብዮት መልክ ያለው እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ እየታየነው የሚል አመለካከት የሚያንፀባርቁ ሲሆኑ፣ ሌሎቹ ደግሞ ፈፅሞ በዚህ ሐሳብ የማይስማሙ ሆነው እናገኛቸዋለን። የቀዳሚዎቹን የአመለካከት መሠረትና አመክንዮ፣ በአሁኑ ወቅት በሐገሪቱ ውስጥ እየተከሰተየሚገኘው እንደ ኤርትራ እና ግብፅ ያሉ በኢትዮጵያ ላይ የተለየ ፍላጎት ያላቸው የውጭ ሐይሎች በሽብርተኝነት ከተፈረጁና ነፍጥ ካነሱ መንግሥትን በሐይል ለመጣል የሚንቀሳቀሱ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች በጋራ ተቀናጅተው የሚዘዋወሩት የተቃውሞ እንቅስቃሴ እንደሆነ በማመንና በዚህ አመክንዮ መነሻም በአሁኑወቅት በኢትዮጵያ የሚካሄደው የሕዝባዊ ተቃውሞ እንቅስቃሴ የቀለሞ አብዮት መልክ እንዳለው ይገልፃሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ በዚህ ሐሳብ ፈፅሞ የማይስማሙ ወገኖች፣ አሁን በአገሪቱ ውስጥ ለተከሰተው የፖለቲካው ጥረትና እየተወሳሰበ ችግር እንዲሁም ሕዝቡን ለተቃውሞና ለአመፅ እንዲዳረግ ያበቃው ዋነኛው ተጠያቂውና ሐላፊነቱን መውሰድ የሚገባው አገሪቱን

በመምራት ላይ የሚገኘው መንግሥትና የፖለቲካ ሥርዓቱ እንደሆነና የችግሮቹ መንስኤም ራሱ መንግሥት የፈጠረው ችግር እንደሆነ አበክረው ይገልፃሉ። ይህንን ሐሳባቸውን ለማጠናከርም የኢሐዴግ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በታኅሣሥ ወር 2010 ዓ.ም ያካሔደውን የ17 ቀናትን ድርጅታዊ ግምገማ ተከትሎ ይህንን ማመኑን በድርጅቱ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ መግለጫ ላይ የተጠቀሱ ነጥቦችን በአስረጂነት ያነሳሉ።

እንደሚታወሰው በዚህ መግለጫው ላይ የኢሕአዴግ ሥራ አስፈጻሚ የሕዝባዊ ተቀውሞ እንቅስቃሴውን መንስኤና የተከተለውን አገራዊ ችግር አስመልክቶ ሲገልፅ፡-

"…በተራዘመ ትግል የተገነባችውን አገር ለአደጋ ማጋለጥ የጀመሩት ጉድለቶች በዋነኛነት የኢሕአዴግ ከፍተኛ አመራር በተለይም የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ድክመቶች ናቸው፡ ፡ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላቱና የድርጅትና የመንግስት ከፍተኛ ኃላፊዎች በተናጠልና በጋራ፣ ስትራቴጂያዊና ታክቲካዊ አመራር የመስጠት ኃላፊነታቸውን ባለመወጣታቸው የተፈጠረ ችግር ነው። በዚህ ግምገማ የኢሕአዴግ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴና የመንግሥት የበላይ አመራሮች ወቅቱ የሚጠይቀውን ስትራቴጂያዊ አመራር የመስጠት ጉድለታቸው ሰፊ እንደሆነ ታይቷል። ከፍተኛ አመራሩ ችግር አስቀድሞ የመለየት፣ ተንትኖ የማወቅ፣ የመፍቻ መንገዶች የመተለምና በዚሁ መሠረት የመፍታት ብቃቱ ወቅቱና መድረኩ ከሚጠይቀው ደረጃ ጋር አብሮ ባለማደጉ የተወሳሰበውን አገራዊ መድረክ በብቃት የመምራት ጉድለት እንደነበረበት የጋራ አቋም ተይዟል። በመሆኑም ለተፈፀመው ስህተትና ለደረሰው ጉዳት ከፍተኛ አመራሩ ኃላፊነቱን እንደሚወስድ ስምምነት ላይ ተደርሷል። ከዚህ በመነሳት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው መላ የአገራችን ሕዝቦች በከባድ ተጋድሏቸው ያስመዘገቧቸውን ድሎች ጠብቆና አስፍቶ ለማስቀጠል ባለመቻሉ፤ እንዲሁም በድርጅታችን ውስጥም ሆነ በአገራችን ውስጥ የሚታዩ ልዩ ልዩ ችግሮችን በጊዜና በከፍተኛ የኃላፊነት መንፈስ ለመፍታት ባለመቻሉ ለደረሰው ጉዳት ሙሉ ኃላፊነቱን ከመውሰድ በተጨማሪ ለመላ የአገራችን ሕዝቦችና የድርጅታችን አባላትና ደጋፊዎችን ልባዊ ይቅርታ ይጠይቃል።…." ነበር ያለው።

ታዲያ እውነታው ይህ ከሆነ፣ መንግሥት የቀለም አብዮትን ጉዳይ አሁን ላይ ማንሳቱ ለምን አስፈለገው? ለሚለው ጥያቄ መልስ የቀለም አብዮት በአገሪቱ ውስጥ አልታየም የሚል ሐሳብ የሚያራምዱ ምሁራን፣ አዲስ ትርክት ለመፍጠር (new narrative creation) ነው የሚል ሐሳብ እንዳላቸው በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ሲገልፁ ተሰምቷል።

በዚህ ረገድ እነኚው ምሁራኑ ሐሳባቸውን ሲያብራሩ እንደሚገልፁት መንግሥት የችግሮቹ ምንጭ እኔ ነኝ ሲል አስቀድሞ በይፋ ያመነውና የገለፀው ትርክት ፖለቲካዊ ኪሳራ ሊያመጣበት እንደሚችል ግምገማ በማድረግና በመጀመሪያው ትርክት መሠረት መጓዙ በተግባር የሚጠይቀውን የተሐድሶ ማሻሻያ ለመተግበር በሚችልበት ቁመና ላይ አለመገኘቱና ፍላጎት ማጣቱ ሌላ አዲስ ትርክት እንዲፈጥር እንዳደረገውና የትርክት ለውጥ እዲያደርግ አስገድዶታል ብለው እንደሚያምኑ ሲገልፁ አናስተውለናል።

የሆነው ሆኖ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ የሚታየውን የሕዝባዊ ተቃውሞ እንቅስቃሴ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ መቃኘትና መተንተን ለጉዳዩ ተገቢና ምክንያታዊ ፍረጃ ለመስጠት እንደሚያግዝ አያጠያይቅም።

## የቀለም አብዮት ተቋማዊ ይዘቶችና መዋቅሮች

በዚህ ረገድ እንደ Center For Syncretic Studies የተባለው ተቋም ጥናት አገላለፅ በአጠቃላይ በአንድ አገር ውስጥ የቀለም አብዮት እንቅስቃሴ መኖሩን ለመረዳት የተለያዩ ውስብስብ ነገሮች (factors) ጥምረትና ቅንጅትታዊ እንቅስቃሴዎች መታይት ይኖርባቸዋል። ይሁንና እደተቋሙ ጥናት አገላለፅ እነኚህ ሁሉ ነገሮች በሚከተሉት ንዑስ መመዘኛዎች ተጠቃለው ሊቀመጡ ይችላሉ፡-

## ርዕዮተ-ዓለማዊ መሠረት (Ideology)

ርዕዮተ-ዓለም የለውጥ እንቅስቃሴ መሪ የሐሳብ ማዕከልና የአብዮቱን ተሳታፊዎች ለተቃውሞ በማነሳሳት ረገድም ግንባር ቀደም ገፊ ምክንያት እንደሆነ ይኸው ጥናት ያመለክታል። ከታች የተገለፁት ቀሪዎቹ የቀለም አብዮት ክፍሎች የዚህ ሐሳብ ተከታዮች ናቸው። በተጨማሪም ያለ ርዕዮተ-ዓለም ቀሪዎቹ ንዑስ ክፍሎች ትርጉምና ግብ አልባ ናቸው። የቀለም አብዩት ርዕዩተ-ዓለም ማጠንጠኛ ግብ የምዕራቡ ዓለም የሚከተለው የሊብራል ዴሞክራሲ ርዕዮት እንደሆነ በጥናት ተመልክቷል።

## ፋይናንስ

ጥናቱ እንደሚያመለክተው ከሆነ ሕዝባዊ ተቀባይነትና ድጋፍ ለማግኘት ማንኛውም ርዕዮተ-ዓለማዊ እንቅስቃሴ የፋይናንስ ምንጭ (financial infrastructure) ሊኖረው እንደሚገባ ያመለክታል። ጥናቱ አክሎ እንደሚገልፀው ገንዘብ በሕብረተሰቡ ላይ ርዕዮተ-ዓለማዊ ተፅዕኖ ለመፍጠር አጋዥ ኃይል ነው። ለርዕዮተ-ዓለም በአንድ አገር ውስጥ ሰርጎ ለመግባትና ለመስረፅ ዋነኛው የሆነው ኃይል የሆነው መነሻ የገንዘብ ምንጭ የሚመጣው ከውጭ ሐይሎች እንደሆነም ይኸው ጥናት ይገልፃል።

**…የመንግሥትን ሐሳብ በመደገፍ፥ የቀለም አብዮት መልክ ያለው እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ እየታየነው የሚል አመለካከት የሚያንፀባርቁ ሲሆኑ፣ ሌሎቹ ደግሞ ፈፅሞ በዚህ ሐሳብ የማይስማሙ ሆነው እናገኛቸዋለን…**

## ማኅበራዊ መሠረት

በቀለም አብዮት ንቅናቄ ውስጥ ማኅበረሰብ በንቅናቄው የሚሳተፉ ሕዝቦችን የሚያካትትና ለንቅናቄው ማኅበራዊ መሠረት የሚሰጠው የአብዩቱ ታህታይ መዋቅር ነው። ማኅበረሰብ በቀለም አብዮት ውስጥ በሦት ዋና ዋና ማኅበራዊ ፈርጆች ተከፋፍሎ ይዋቀራል። ይኸውም፣ ግምባር ቀደም (Core/ Vanguard)፣ የሠራተኛ መደብ (Cohorts/ Workers) እና መደበኛው ነዋሪ (Civilians/Sympathizers) በመባል ይታወቃል። ግምባር ቀደም ወይም (Core/Vanguard) በሚለው ፈርጅ ውስጥ የሚመደበው የማኅረሰብ ክፍል የቀለም አብዮቱን በማደራጀት፣ በማቀናጀትና በመምራት የአብዮቱ ዋነኛ ዘዋሪ በመሆን ያገለግላል።

የሠራተኛ መደብ (Cohorts/Workers) በመባል የሚታወቀው የማኅበረሰብ ፈርጅ ደግሞ በተዋረድ ከግንባር ቀደሙ የማሕበረሰብ ክፍል ሥር በመሆን የንቅናቄውን ተሳታፊዎች የመመልመል ሚናን በመውሰድ የአስተዳደር ስራ የሚያከናውን ሆኖ እናገኘዋለን።

በሌላ በኩል መደበኛው ነዋሪ (regular citizens ወይም Civilians/Sympathizers) በመባል የሚታወቀው ክፍል፥ የንቅናቄውን መሠረታዊ ዓላማ የሚጋራና ንቅናቄው በዕለት ተለት ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሒወቱ ዙሪያ ለውጥ እንደሚያመጣለት የሚያምን ሆኖ፣ መሬት ላይ ባለው አሁናዊ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ በእጅጉ የተማማረረ የኅብረተሰብ ክፍል ነው። ይህ ክፍል ለንቅናቄው ከፍተኛ ኃይል በመስጠትና ንቅናቄው ማሕበራዊ መሰረት እንዲኖረው ምቹ መደላደል በመፍጠር ረገድ የሚኖረው ሚና የአንበሳውን ድርሻ የሚወስድ ነው።

## ስልጠና ወይም ዝግጅት

ስልጠና በቀለም አብዮት ውስጥ የንቅናቄው ሒደት ግቡን እንዲመታ ለማድረግ የሚካሄድና በየትኛውም የቀለም አብዮት እንቅስቃሴ ውስጥ ከቶውንም የማይቀር ጉዳይ ነው። በዚህ ዓይነቱ የአብዮት እንቅስቃሴ ውስጥ የአብዮቱ አካሒያጆች ለእንቅስቃሴው ግብዓት የሚሆን ገንዘብ ማመንጨት፣ ንቅናቄውን በማፋፋምና የተሳታፊዎችን ቁጥር በማሳደግ እና መረጃን በማደራጀትና በማሰራጨት ስልጠና እንደሚወስዱ በጥናቱ ተመልክቷል።

## የመገናኛዘዴዎች (Media)፦

የመገናኛ ዘዴዎች የቀለም አብዮት ተቋማዊ አደረጃጀት ታህታይ መዋቅር መደምደሚያ (culminating point of the Movement's entire Infrastructure) ሲሆኑ፣ የማሕበራዊ ትስስሮችን ወይም መደበኛ የሆኑ እንደ ቴሌቪዥን፣ ራዲዮ፣ ጋዜጦችና መጽሔቶችን ሊያካትቱ ይችላል። በቀለም አብዮት እንቅስቃሴ ውስጥ የሚራመደው ርዕዮተ-ዓለም በሕዝብ ዘንድ ቅቡልነት እንዲኖረው በማድረግ ረገድ ሚዲያዎች ጎልህ ድርሻ እንደሚኖራቸው በጥናቱ ተመልክቷል።

ለማጠቃለል ያህል፤ የቀለም አብዮት በዚህ አጭር ጽሑፍ በምልአት ተጠቃሎ ሊገለፅ የማይችል የተለያዩ ማኅበራዊ ታህታይ መዋቅሮችን የሚያቅፍ ተቋማዊ አደረጃጀት ያለው የተቃውሞ ንቅናቄ እንደሆነ መገንዘብ ተገቢ ጉዳይ ነው። የሆነው ሆኖ ግን አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ከላይ ከተገለፁት መዋቅራዊና ተቋማዊ የቀለም አብዮት አደረጃጀቶች ጋር በማነፃፀር መመልከት የጉዳዩን ትክክለኛ ገፅታ ለመመልከት ይረዳል። በተጨማሪም ኅብረተሰባችንም ይሁን መንግሥት፣ ትክክለኛ የሆነውን ስዕል በመመልከት የሁኔታውን ትክክለኛ ትንተና መስጠት ቢችል የችግሩን መፍትሔ ለማግኘት ለሚደረገው ጥረት አጋዥ የሚሆንና ለችግሩ ተገቢ መፍትሔ ለማምጣት የሚያስችል ጠንካራ መሰረትን እንደሚሰጥ የሚያጠያይቅ ጉዳይ አይደለም።

በመጨረሻም የቀለም አብዮት ውስብስብና በተለያዩ የፖለቲካ ልሒቃን ዘንድ የተለያየ ትንተና ቢኖረውም፣ ከላይ የተጠቀሱት ታህታይ ማኅበራዊ መዋቅሮች ዓይነተኛ መለያዎቹ እንደሚሆኑ ግን ሁሉም ይስማሙበታል።

ቸር እንሰንብት!!!!!

# "የትግራይ ሕዝብ ዘላለማዊ ነው ሕወሓት ግን ዘላለማዊ ያልሆነ የአንድ ቡድን ስብስብ ነው!"

## ብርጋዲየር ጄነራል ተፈራማሞ




ከአሜሪካን ኢታማጆር ሹም ሽልማት የተቀበሉበት 2001 ዓ.ም

**ብርጋዲየር ጀነራል ተፈራ ማሞ በትግሉ ወቅት ስለ ነበሩ አንዳንድ ችግሮች፣ከተለያዩ የብአዴንና የሕወሓት አመራሮች ጋር ተከስቶ የነበረውን አለመግባባትና ሌሎች ተዛማች ጉዳዮችን በተመለከተ ያደረጉትን የመጨረሻ ቃለ ምልልስ ፍቃዱ ማህተመወርቅ እንደሚከተለው አቅርቦታል።**

**ግዮን፡- መለስ ዜናዊ በተገኙበት መድረክ፤ ምን ምን ጥያቄ አነሡ፤ ምላሹስ ምን ነበር?**

ብ/ጀነራል ተፈራ፡- መለስን ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁት በ1983 ዓ.ም ተምቤን አካባቢ የኢሕአዴግ ጉባኤ በተደረገ ጊዜ ነበር። አካላዊ ሁኔታው ሰፋ ያለ ስፖርተኛ የሚመስልና ፀጉሩ ሙሉ ነበር። በኤርትራ ጉዳይ ላይም፡- "የኢትዮጵያ ሕዝብ የኤርትራን መገንጠል ካልተቀበለውና ወደ ውጊያ ከገባ እኛ ምንድነው የምናደርገው?" የሚል ጥያቄ አነሣሁ። ያንን ጥያቄዬን መለስ ዜናዊ በዝምታ ሲያልፈው፤ ተወልደ "ሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት የት ሄዶ ነው ሕዝቡ እንደዚያ ዓይነት እርምጃ የሚወስደው? ይሄማ መንግሥት አይደለም ማለት ነው!" በሚል ምላሽ ሰጠበት።

በ1993 ዓ.ም ተሐድሶ ጊዜ ደግሞ ‹‹ቦናፖርቲዝም››ን እኛ ወደ አማርኛ የወሰድነው የቤተሰብ ፓርቲ በሚለው ነው፤ምክንያቱም ሁሉንም የአገሪቱን ሥልጣንም ሆነ የሀገሪቱን መዋቅር የሕወሓት አባላት፣ ደጋፊዎችና ተላላኪዎች ብቻ ናቸው የያዙት። መለስ ግን ደጋግሞ "አንጃው ነው ጥፋተኛው" እያለ ድክመቶችንና ስሕተቶችን ወደ ታችኛው ክፍል ሲያሳብብ… "ራስህ አይደል ወይ ስትመራው የነበረው? በይዘትስ አንድ አይደላችሁም ወይ? በኢትዮጵያ ሕዝብ ኪሳራ የራሳችን የምትሉትን ቡድን ለማበልፀግ እንዲመቻችሁ ሁሉንም ሥልጣን ጠቅልላችሁ ይዛችሁት ወይ?" የሚል ጥያቄ አቀረብኩ። ያኔ መለስ ለመጀመሪያ ጊዜ ትክ ብሎ ተመለከተኝ። ወደ ሌላ ትችት ሳይገባ "አንጃው ብቻ አይደለም ሥርዐቱም ከላይ የበሰበሰና የተበላሸ ስለሆነ ነው፤ ሁሉም መዋቅር በሕወሓት ብቻ ነው ላልከው 65 ፐርሰንቱን መዋቅር የያዘው አማራ ነው" በሚል ከአንድ ሰአት በላይ ትንታኔ ሰጥቶበታል።

**ግዮን፡- ከደርግ ውድቀት በኋላ የጦር ኃላፊነትዎ ምን ደረጃ ላይ ደረሰ?**

ብ/ጀነራል ተፈራ፡- አብዛኛውን የጨረስኩት የክፍለ ጦር አዛዥ በመሆን ነው። የመጀመሪያው

ተልዕኮዬ በመከላከያ ሚኒስቴር ሥር ሆኜ በአዲስ አበባና በዙሪያዋ ያለውን ሰላም የማረጋጋት ተግባር ስንፈጽም ቆየን። የሽግግር መንግሥቱ እንደተመሠረተ ደግሞ የተወሰኑ ክፍለ ጦሮች ከተማውን እየለቀቁ ሲሄዱ እኔ ሰሜን አዲስ አበባን በሙሉ ያዝኩኝ። ልክ ፖሊስ የሚሠራውን ሥራ እየሠራን ለአንድ ዓመት አዲስ አበባን ካረጋጋን በኋላ ቀስ በቀስ ለፌደራል ፖሊስ እየሰጠን ወደ አማራ ክልል ሄድን።

**ግዮን፡- ትግል የጀመሩበት የአማራ ክልል ቆይታዎ እንዴት ነበር?**

ብ/ጀነራል ተፈራ፡- በአማራ ክልል ደሴን፣ ደብረ-ማርቆስን፣ ዳንግላንና ደብረ-ታቦርን በአንድ አንድ ብርጌድ አደራጀነው። በክልሉ የተበተነው ወታደር በሽፍተኝነት መልክ ዘርፋ ሲያደርግ እሱን አስቆምን። በመቀጠል ኦነግ ከሽግግሩ ሲወጣ አንድ ብርጌድ ይዤ በወለጋ አቅጣጫ ገባሁ። እሱን እንደ ጨረስኩ ከክፍለ ጦር አዛዥነት ወደ ፓራ-ኮማንዶ አዛዥነት ተቀይሬ ቋራ ኢሕአፓን ለመምታት ሄድን። ኢሕአፓን ከቋራ ነቅለን ካወጣን በኋላ፤ መተከል ደግሞ አማራዎችን የማፈናቀል ግጭት ተከስቶ እሱን መፍታት ያዝን። ከዛም ሱዳኖች ጠረፍ ላይ መተማ አካባቢ እየገቡ ነዋሪዎችን እያፈናቀሉ፣ ያገኙትን ይገድሉ ይዘርፉ ነበር። በዚያ ሱዳኖችን ልክ አስገብተን ወደ ሰሜን ሸዋ ተጓዝን። በሰሜን ሸዋ ውስጥ የተደራጀ ቡድን እሥር ቤቶችን ይመታ ነበረና እሱን አረጋግተን ደግሞ ወደ ኦጋዴን ገባን። ልክ እንደ ፈጥኖ ደራሽ በመላ ሀገሪቱ እየተወረወርን ሰላም የማስጠበቅ ኃላነፊነታችንን ተወጣን።

**ግዮን፡- የማዕረግ ሹመትዎ ሁናቴ ምን እንደሚመስል ይንገሩን?**

ብ/ጀነራል ተፈራ፡- መልካም!...ኅብረ-ብሔራዊ ሠራዊት ከተመሠረተ በኋላ የሕወሓት ሠራዊት አጠቃላይ የአገሪቱ ሠራዊት ኮር ነው ሲሉ "ለምንድነው ሕወሓት ብቻውን ኮር የሚሆነው? ይሄ ተገቢነት የለውም!" የሚል አቋም ነበረኝ። እነሱ ደግሞ "የሕወሓት የበላይነት ያስጋሃል" ይሉኛል፤ ‹‹ትምክህተኛና የአመለካከት ችግር አለብህ›› በሚል ኦጋዴን ከፓራ-ኮማንዶ አገዛዥነት አውርደው ምክትል አደረጉኝ። እንደውም እኔ በውጊያ ወቅት ስመራቸው የነበሩትን አምጥተው አዛዤ አደረጓቸው። በምክትልነት ስምንት ወር እንደሠራሁ የ21ኛ ክፍለ ጦር አዛዥ አድርገው መለሱኝ። በዚህ ጊዜ ማዕረግ ሲጀመር ዝቅ ተደርጎ ነው የተጀመረው። ኃየሎምን ጨምሮ አሥር ጀነራሎች ነበሩ፤ ደቡብ የ21ኛ ክፍለ ጦር አዛዥ ሆኜ ከሠራሁ በኋላ ነበር ወደ ኮረኔልነት የተሸጋገርኩት።

**ግዮን፡- በበረሃ ትግሉ ወቅት የኮሎኔል ወይም የጀነራል ማዕረግ እንዴት ነበር የሚሰጠው?**

ብ/ጀነራል ተፈራ፡- ያኔ ማዕረግ የለም። ማዕረግ የሚባል ስለሌለ ዝም ብሎ ኃላፊነት ነው የሚሰጥህ።

**ግዮን፡- በወቅቱ ጀነራል የነበሩት እነ ኃየሎም እንዴት አገኙት ታድያ?**

ብ/ጀነራል ተፈራ፡- እነሱ ለድርጅቱ ማዕከላዊ ኮሚቴ ደርሰው ነበር፤ የግንባር አመራር እየሆኑ አድገዋል። ለምሳሌ ኃየሎም ሕይወቱ ሲያልፍ፤ ለክብሩ የሜጀር ጀነራልነት ማዕረግ ተሰጠው። ፃድቃን በኤታማዦር ሹምነቱ ሜጀር ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ ብርጋዲየር ሆኑ።

**ግዮን፡- የኢሕዴን ታጋዮች የተሰውለት፣ የወደቁለት ትግልና ዓላማ ‹‹የአማራ ሕዝብ ተጠቅሞበታል...›› ይባላል። ግን ግን በእውነት ታጋዮቹ የተሰዉለት ዓላማ ግቡን መቷል ወይ?**

ብ/ጀነራል ተፈራ፡- ትግሉ ተኮላሽቷል። በ1990 ዓ.ም የሕወሓት ሠራዊት መሪዎችና ተሳታፊዎች መቀሌ ላይ ተሰብስበው "ተገቢውን ማዕረግ አላገኘንም" የሚል ቅሬታ ሲያቀርቡ፤ ኦሕዴድ ደግሞ ደብረ-ዘይት አካባቢ ተሰብስቦ "መጀመሪያውኑ ማዕረግ ያላችሁን ውሸት ነው! ሁሉንም ሕወሓት ነው የጠቀለለው" በሚል ለማዕረግ ሽሚያ ሲሟገቱ፤ ኢሕዴን ቤት ግን በድንገት ሌላ አቅጣጫ ያዘ። አጋጣሚው የተፈጠረው የአገር አቀፍ ሠራዊት ከሆነው የአማራው ተወላጅ አዲስ አበባ ላይ ተሰባስቦ ወደ ባሕር-ዳር ለውይይት ሲሄድ ሁለት አቅጣጫን ይዞ ነው። ግማሹ ከአዲስ አበባ ሰሜን ሸዋን እና ደቡብ ወሎን እያየ፣ በላሊበላና ደብረ-ታቦር አድርጎ ባሕር-ዳር እንዲገባ ተደረገ። ግማሹ ደግሞ በፍቼ አድርጎ ጎጃምን እየታዘበ በበለሳ ባሕር-ዳር ላይ ከተመ። ለመጀመሪያ ጊዜም ካረፈበት ወጣ እያለ የትውልድ ቦታውን እየዞረ ማየት ጀመረ።

በዚያም ምክንያት ቁጭት እና ሐዘን ልቡን ሰበሩት። ማዕረግ አንሶኛል ምናምን የሚለውን አጀንዳ ጥሎ፤ በጉዞ ወቅት ልቡን የሰበረውን ክስተት መድረኩ ላይ መወርወር ጀመረ። "ሥርዐቱ ትክክል አይደለም! የአማራ ሕዝብ እንኳን ሊለማ ቀርቶ ያለውን እያሳጣነው ነው! ይሄም የሆነበት ዋናው ጉዳይ የኢሕዴን መሪዎች ከአማራ ጋር የሚያቆራኛቸዉ ነገር ባለመኖሩ ነው። የአማራን የልብ ትርታ የሚያዳምጡ አይደሉም" በሚል ፍጥጥ ብሎ ተነሣባቸው። አማራ ክልል በዋናነት በድህነት እየተገረፈ ያለውና ወደ ልማት እንዲገባ ያልተደረገው "የኔ" የሚለው ተቆረቋሪ መሪ በማጣቱ ነው። ከተለያየ ቦታ አማርኛ ቋንቋውን ስለተናገረ ብቻ የተሰበሰበ እንጂ ለአማራ ተቆርቋሪ መሪ የመሆን ፍላጎት ያላቸው አይደሉም...የሚል አጀንዳ ተነሣ። ስብሰባው በከረረ ሁኔታ ተጋጋለ። "ክልሉ እየሞተ ነው! መብራት የለም! መንገድ የለም! የመሠረተ-ልማት እጦት ተባብሷል፤ በክልሉ መሬት ላይ የመብራት መስመር ወደ ሌላ ክልል ረግጦ እያለፈ፤ የአማራ ሕዝብ ግን መብራት አያገኝም። ስለዚህ ይሄ ሕዝብ በዚህ ሥርዐት በግልፅ የኢኮኖሚ ጦርነት ተከፍቶበታል" የሚል ጠንካራ ትችት መጣ።

**ግዮን፡- ከመድረኩ ምን መልስ ተሰጠ?**

ብ/ጀነራል ተፈራ፡- ማድበስበስና ጥያቄዎችን ችላ የማለት ሁኔታ ነበረ። በረከትም መልስ ለመስጠት ሞከረ። ‹‹ተወላጆች አይደላችሁም›› ለሚለው ‹‹የትም ልወለድ ራሳችሁ አላታገላችሁኝም። ካርድ ሰጥቶኝ ማንም ያታገለኝ የለም" የሚል መልስ ሰጠ። አዲሱና ሌሎቹ ደግሞ ከነፍጠኛና ከትምክህተኛ ጋር ለማያያዝ ሞከሩ እንጂ መሠረታዊ ምላሽ አልነበራቸውም።

**...ሠራዊቱ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ መንግሥታዊ መዋቅሮቹ አገራዊ መዋቅር አይደሉም። አገራዊ ሠራዊት እንዳልሆነ ይታወቃል፡ ፡ ግን ሲናገሩ ሰምተሃቸው ከሆነ "የብሔር ተዋፅኦውን የጠበቀ" ነው ይላሉ...**

**ግዮን፡- ከስብሰባው በፊት ክልሉን ስትታዘቡ፤ "በአንድ አገር ሕዝብ ላይ የልማት ልዩነት ለምን ይከሰታል" የሚል ቁጭት ይበልጥ እንዲፈጠርባችሁ ያደረጉት ቦታዎች የትኞቹ ነበሩ?**

ብ/ጀነራል ተፈራ፡- ሁሉም ማለት ይቻላል። በዐይኔ ያየሁትን ለአብነት ብጠቅስልህ ሰሜን ጎንደር ላይ አማርኛና ትግሪኛ ተናጋሪ ሕዝብ አንድ ላይ ይኖራል። በአማርኛ ተናጋሪው በኩል የጠጠር መንገዶች አልፎ አልፎ ካልሆነ ትርጉም ያለው መንገድ የለም። በዚያኛው በኩል ግን አራት ደረጃቸውን የጠበቁ አስፋልቶች ተገንብተዋል። መብራት ይሄኛው ጨለማ ነው፤ እዛኛው መብራት ያያል። በተመሳሳይ ሰሜን ወሎ ባለፈው የግጭት ማዕከል የነበረው አካባቢ በጨለማ ሕይወቱን ሲገፋ፤ ያኛው ደግሞ በብርሃን ይኖራል። የአንድ አገር ሕዝብ አይመስሉም። ለዚህ ‹‹ትምክህተኞች ናችሁ! ከነፍጠኛው የገዥ መደብ የመጣችሁ ናችሁ!...›› የሚል ስም የመስጠት ምላሽ ብቻ ነው ያለው።

**ግዮን፡- በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት የእርስዎ ኃላፊነት ምን ነበር? የጦርነቱንስ ሁኔታ እንዴት ያስታውሱታል?**

ብ/ጀነራል ተፈራ፡- በወቅቱ እኔ አዲስ አበባ ጃንሜዳ አካባቢ፤ በግንቦት 20 ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ ነበርኩ። ከዛ ትምህርቱን አቋርጬ ወደ ጦርነት ገባሁ። 33ኛ የዓባይ ክፍለ ጦር አዛዥ ሆኜ ጦርነቱ ተጀምሮ እስኪቋጭ በባድመ ግንባር ነው የተዋጋሁት።

**ግዮን፡- የተዋጉበት የጦር አውድማ ጥሎት ያለፈው አሻራ ይኖራል?**

ብ/ጀነራል ተፈራ፡- አንደኛ በዚያ ጦርነት የተገኘው ድል የሻዕቢያን ዕብሪት አስተንፍሰን ቢከፍቱት ተልባ ነው ያደረግነው። ሻዕቢያ የተሻለ የመከላከያ ምሽግ ሠርቶ ቢዋጋም የተከፈለው ዋጋ ተከፍሎ ነው በማሰው ጉድጓድ የቀበርነው። ይሄ ድል እስካሁን ድረስ ሻዕቢያ ቀና ብሎ ድጋሚ እንዳያጠቃ አድርጎታል። በባድመ ግንባር በመጨረሻው ውጊያ ሻዕቢያ በ8 ክፍለ ጦር በመከላከል ላይ እያለ እኛ ደግሞ በ20 ክፍለ ጦር አጥለቀለቅነው። ባድመ ላይ በቆፈረው ምሽግ ከፊት ያጠቁኛል ብሎ ሲጠብቅ፤ በጎንና ጎን ገብተን ከጀርባው ተጠመጠምንበት። ቀን ሲጠብቀን ሌሊት ከተፍ እንልበታለን። የዚያን ጊዜ የሸንፈት አንጎበሩ አሁንም አለቀቀውም።

ሁለተኛው አሻራ ሕወሓት ተሸክሞት የነበረውን "መርግ" ከጫንቃው ላይ ነው ያነሣንለት። በዚያ ውጊያ ሕወሓት አክብዶና ፈርቶ የሚያየው ሻዕቢያን ነው። መነሻው ደግሞ ሕወሓት ሲመሠረት የውጭ ጉዳዩን የሚመራው "ጃማይካ" ሲሆን ወታደራዊውን ደግሞ ሙሴ(መሐሪ) ነበር የሚመሩት። የሻዕቢያ ነባር ታጋዮች በመሆናቸው፤ ሕወሓትን በማሳደግና አቅጣጫ በማስያዝ ዋና ተዋናዮች ነበሩ። ሕወሓት የተደራጀው የደጀን-አምባን ሥልጠና ጨምሮ ሁሉንም ሥልጠናዎች በሻዕቢያ ትከሻ ላይ ሆኖ ነው ። በዚህ ምክንያት ታጋይ ሲባል ሻዕቢያ፤ መሪ ሲባል ኢሳይያስ፤ ተዋጊ ጦር ሲባል የሻዕቢያ ብቻ ነበር የሚከሰትላቸው። ልክ በባድመም ሆነ በሌሎች ቦታዎች የኢትዮጵያዊያን ክንድ ሲያርፍበት፤ ጫንቃቸው ላይ እንደመርግ ሰቅዞ ይዟቸው የነበረው ፍርሐት ንቅል ነው ያለላቸው። ሦስተኛው ደግሞ በጦርነቱ ሰበብ የሕወሓት አመራር ከሁለት ተሰነጠቀ፡

→

የተገመሱት ሁለቱም በይዘት አንድ ናቸው። ምንም ልዩነት የላቸውም። የሕወሓት መሪዎች እጅግ ሲበዛ ነዋይ አፍቃሪዎች ናቸው።

**ግዮን፡- በወቅቱ ጦሩ ድል እያደረገ ወደ አስመራ አቅጣጫ የመገስገስ ፍላጎት የነበረው ሆኖ ሳለ በወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ፤ ጦሩ ከግስጋሴው እንዲገደብ ትዕዛዝ ሰጥተው ተግባራዊ ተደርጓል። ያ ለምን ሆነ?**

ብ/ጀነራል ተፈራ፡- የመጀመሪያው ሐሳብ ኤርትራን ሙሉ ለሙሉ መያዝ ነበር። ግን በዘመቻ ፀሐይ-ግባት ባድመን ካስለቀቅን በኋላ ወደ መረብ ገፍተን ማሻገር ሲገባን፤ ጠላት አፍንጫችን ላይ ሆኖ እዚያ የነበሩ አዛገሮች ወደ ዛል-አንበሳ ሄደው ድል ለማድረግ ቸኮሉ። የባድመ ድል በዛል-አንበሳ እንዲደገም አጓጓቸው። ጾረና ላይ አጥቅተው ወደ ደጋው የኤርትራ ክፍል ሊገቡ ሲሉ፤ የሻዕቢያ ጦር ያለ የሌለ ኃይሉን ተጠቅሞ የወገንን ጦር ንቅናቄ አከሸፈው።


በጾረና ግንባር የተሰለፈው የወገን ጦር እንኳን ሊያጠቃ መከላከል አቃተው። በዚህ ጊዜ የአዛገሮቹ ወደ መሀል አጥቅተን ድል እናደርጋለን የሚለው ጉጉት ተኮላሸ። እንደተፈራው ጾረና ላይ ሽንፈት ገጠመን። በዚህ ድል የመረቀነው ሻዕቢያ የተነጠቀውን ባድመን ድጋሚ ለመያዝ መጣ። ያን ዕብሪተኛ ኃይል በድጋሚ አወደምነው። በዚህ ጊዜ የቀድሞው የኢትዮጵያ ሠራዊት ታላላቅ ልምድ ያላቸው መኮንኖችም ተቀላቀሉን። ብዙ ጊዜያቸውን ኤርትራ በረሃ ውስጥ በመዋጋት ያሳለፉ እንደ ጀነራል ተስፋዬ፣ እንደ በኃይሉ ያሉ ሌሎች ብዙ ሙያተኞች ከተለያየ ቦታ መጡ። ዝግጅታችንንም ጨርሰን ኤርትራን ሙሉ ለሙሉ ለመያዝ ቆርጠን በተዘጋጀንበት ወቅት፤ ከላይ ያሉት አመራሮች እነ መለስና ሳሞራ "ዓላማችን ድንበራችንን ማስመለስ እንጂ የሰው አገር መውረር አይደለም" የሚል ሐሳብ ማቀንቀን ጀመሩ። ሠራዊቱ ግን ከመጀመሪያው የነበረው ፍላጎት ‹‹እያጠቃን ወደፊት እንቀጥላለን›› የሚል ነበር። እዚያ ላይ ክፍተት ስለተፈጠረ ጥቃት ፈፅመን ድንበራችንን አስለቀቅን እንጂ አልቀጠልንም።

**ግዮን፡- ከኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት በኋላ የት ተመደቡ?**

ብ/ጀነራል ተፈራ፡- የ108ኛ ኮር እና በሥሩ ያሉትን 31ኛ ዓድዋ ክፍለ ጦር፣ 33ኛ ዓባይ ክፍለ ጦር፣ 35ኛ ዋለልኝ ክፍለ ጦር እና 8ኛ ሜካናይዝድ ጦር መሪ ሆኜ ተመደብኩ። ዋና መምሪያውን ሽሬ ላይ በማድረግ የባድሜን ግንባር የመቆጣጠር ተልዕኮ ይዘን ነበር። ወዲያው የጀነራልነት ማዕረግ ሲመጣ ብርጋዲየር ጀነራል ሆኜ አንድ አራት ዓመት እዚያው መራሁ። በነዚያ ዓመታት የትግራይ ክልል የጋራ ኮሚቴ አባል ነበርኩ፡ አጋጣሚውም የትግራይ ክልልን በደንብ ለማወቅ ዕድል ፈጠረልኝ። ከዛ ቆይታዬ በኋላ ኮሮች በሙሉ ፈርሰው በአራት ዕዝ ሲዋቀር፤ የሰሜን ዕዝ ምክትል አዛዥ በመሆን እስከተነሳሁበት ድረስ ሠርቻለሁ።

**ግዮን፡- ታዲያ በጊዜው የትግራይ ሕዝብ የነበረውን ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ሕይወቱን እንዴት አገኙት?**

ብ/ጀነራል ተፈራ፡- በወቅቱ ከሌሎች ክልሎች በተለየ መልኩ አመራሮቹ ሕዝቡን አስገድደው ነበር የሚመሩት። ያው ከጫካ የመጡ ስለሆኑ ሁሉን ነገር በማስገደድ ነበር የሚፈፅሙት። ማኅበረሰቡ በንፅፅር ለመለወጥ የሚያደርገውን ፍላጎት እና ጉጉት ታያለህ። እዚያ ቦታ ላይ ሕዝቡ ለመለወጥ የሚያደርገው ጥረት ለየት ያለ ነው። ትግራይ ላይ ዘረፋ የለም። የሕዝቡ



ባሬንቱ ቤተመንግሥት ተገኝተው ከምክትሉና ከሎጀስቲኩ ጋር ስለቦታው በካርታ ቅኝት እያደረጉ



የኢትዮ-ኤርትራ የሠላም አዛዥ በባድመ ውጊያ ዙሪያ ውይይት ሲያደርጉ

የመቀራረብና የመግባባት ስሜት ደስ ይልሃል። አንዲት ማዳበሪያ ሲሰርቅ ቢገኝ ወዲያው በግምገማ ያፋጥጡታል። ሕዝቡ እንደ ሕዝብ ንፁሕ እና እንግዳ ወዳጅ የእግዚአብሔር ሕዝብ ነው። በሩቁ ሆነው ስም እንደሚያወጡለት አይደለም። ኢትዮጵዊ ስሜቱ የጋለ ነው። ለምሳሌ ሻዕቢያ ወደ ውስጥ ገብቶ ፈንጂ እንዳይጥል አደጋ እንዳይፈጥር፤ ሕዝቡ እያንዳንዱን ከዚያ አቅጣጫ የሚመጣ ዕቃ ይቆጣጠር ነበር።

**ግዮን፡- በመከላከያ ሠራዊቱ ውስጥ ‹‹ፍትሐዊ የሥልጣን ክፍፍል የለም። የአንድ ወገን የበላይነት ይንፀባረቅበታል።...›› የሚሉ ወገኖች ተበራክተዋል። አስተያየትዎ ምንድን ነው?**

ብ/ጀነራል ተፈራ፡- ሠራዊቱ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ መንግሥታዊ መዋቅሮቹ አገራዊ መዋቅር አይደሉም። አገራዊ ሠራዊት እንዳልሆነ ይታወቃል። ግን ሲናገሩ ሰምተሃቸው ከሆነ "የብሔር ተዋፅኦውን የጠበቀ" ነው ይላሉ። ይሄን ውስጠ-ምስጢር ካየኸው "እውነት አገራዊ ሠራዊት ከገነቡ ዐሥር ጊዜ እየደጋገሙ ስለ ብሔራዊ ተዋፅኦ ምን አናገራቸው?" ትላለህ። ባዶ መሆኑን ነው የሚያሳይህ። በሃይማኖታዊ ተቋማት ሁሉ ሳይቀር በመላ አገሪቱ የተቋቋሙ መንግሥታዊ መዋቅሮች በሙሉ አገራዊ አይደሉም። አገራዊ ይዘት እንዲኖራቸውም ስላልተፈለገ፤ የሕወሓትና ለሕወሓት ብቻ የቆሙ ናቸው።

**ግዮን፡- ከሰሜን ዕዝ አዛዥ የተነሱበትን ምክንያት ቢያብራሩልን?**

ብ/ጀነራል ተፈራ፡- ከ97 ዓ.ም ምርጫ ጋር የተያያዘ ነው። በ1997 ዓ.ም ምርጫ በተለይ የአማራ ማኅበረሰብ ኢሕአዴግን አልመረጠውም። ከዚህ የተነሣ በቀጥታ በቀል የጀመሩት በሠራዊቱ ውስጥ ባለው የአማራ ኃይል ላይ ነው። አብዛኛውን የአማርኛ ተናጋሪ መኮንኖች እየለቀሙ በተለያየ ቦታ አሠሯቸው። ከአዲስ አበባ ወደ 400 የሚሆኑ የአማራ የጦር መኮንኖችን አፍነው ወስደው ሐዋሳ ዙሪያ አጎሯቸው። የጎንደርንና የጎጃምን ወጣት እያፈሱ ብርሸለቆ ወሰዱት። ከወሎና ምሥራቅ አማራ የመጣውን ወጣት ደግሞ "ጭፍራ" የሚባል አፋር በረሃ ላይ አሠሩት። ይሄ ሁሉ እንግዲህ ከምርጫ 97 ጋር ተያይዞ በአማራ ላይ የተደረገ በቀል ነው። እኛን ከዕዝ ምክትል አዛዥነት አንስተው አዲስ አበባ ላይ የሆነ ዘመቻ ላይ አስገቡን።

**ግዮን፡- ምናልባት መሠረታዊ መነሻ ይኖራቸው ይሆናል።**

ብ/ጀነራል ተፈራ፡- መነሻቸው ወደፊት



ለመጀመሪያ ጊዜ የኢሕአዴግ የሠራዊቱ መሪዎች በሀገር አቀፍ ሠራዊት አስፈላጊነት ላይ ውይይት ሲያደርጉ ሥዬ ፣ ጻድቃን እና ሌሎችም በ1986ዓ.ም

ከታች ጀምሮ በሠራዊቱ የሚያድገው ኃይል ስጋት ስለተፈጠረባቸው ማባረርና ማሠር መፍትሔያቸው ነበር። ከተባረረው አማራ ወታደር ውስጥ በኋላ ከ20 ሺሕ በላይ እንደገና ተደራጅቶ ነበር። እንደውም ከእኛ ጋር አንድ ላይ የተከሰሱት መቶ አለቃባቡ እና ሻለቃ ፋናየ የሚባሉ የዚህ መሪዎች ናቸው። ከኦሮሚያም የዚህ ገፈት ቀማሽ የሆኑ አሉ። ለአብነት ጀነራል ከማል ገልቹ፣ ኮሎኔል ገመቹ እና ጀነራል ኃይሉን ጨምሮ ወደ አንድ ሻለቃ የሚገመት ጦር ከድቶ ወደ ኤርትራ ሄደ። የመሄዳቸው ምክንያት እነሱ እንደሚሉት ኦነግ ነው ምናምን ሳይሆን አጠቃላይ በተቋሙ አድሎ ብቻ ስለነበር፤ ጀነራል ሆኖ እያለ ነዳጅ እደላ ላይ ከሚሠሩት የ፶ አለቆች ጋር ይመድቡታል። ይባስ ብለው ከማልን ቅድሚያ የተሰጠውን ጀነራልነት ዝቅ አድርገው ክፍለ ጦር አዛዥ አደረጉት። ‹‹ለምን እሆናለሁ? ትክክል አይደላችሁም!›› አለ። እሱ ይሄንን የመሰለውን መገፋትና ጭቆና በመቃወም ነው ከድቶ የወጣው።

**ግዮን፡- በ97 ምርጫ ላይ በአማራ ክልል በብአዴን ከ21ሺሕ በላይ የመከላከያ ሠራዊት አባላት ተባረዋል። ይሄ ሁሉ ሠራዊት ከጥቅም ውጪ ሲሆን፤ በአገሪቱ መከላከያም ሆነ በመንግሥት ላይ የሚፈጥረው ክፍተት አልነበረም?**

ብ/ጀነራል ተፈራ፡- የበላይነቱ እኮ እዚህ ላይ ነው የሠራው። ከላይ ዋና ሥልጣኑን የያዘው ሕወሓት ስለሆነ ሥልጣኑ እስካልተነካበት ድረስ ክፍተት ፈጠረ፣ አልፈጠረ ደንታው አልነበረም። በ97 ዋና እንቅልፍ የሚነሣው የወላለቀ ሥልጣኑን መጠጋገን ነበረ።

**ግዮን፡- ከሌሎች ብሔሮች የተባረሩ፣ የታሠሩ ነበሩ?**

ብ/ጀነራል ተፈራ፡- ሞልተዋል። ከኦሮሞ ከነከማል ጋር ትስስር አላችሁ በሚል ሽፋን፤ ከጉራጌዎች፣ ከቀድሞው ጦር አባሎች ሰለባ ሆነዋል። ግን ጎልቶ የወጣውና በሰፊው የታየው የአማርኛ ተናጋሪው ላይ ነው።

**ግዮን፡- በሠራዊቱ ውስጥ የሚነሡ የፍትሕና የዴሞክራሲ ጥያቄዎች ምንድን ናቸው?**

ብ/ጀነራል ተፈራ፡- የማዕረግ አድሎ ይደረግ ነበር። የውጭ ሥልጠና ኮታ ቅድሚያ የሚሰጠው ለሕወሓቶች ነው። ትምህርት ሲመጣ ቅድሚያ ሕወሓቶች ያገኛሉ፤ የሰላም አስከባሪ ሲባል ሕወሓታዊያን ቀዳሚ ናቸው። አጠቃላይ ማኅበራዊ ግልጋሎ ለአንዱ ልጅ፣ ለሌላው የእንጀራ ልጅ ነው። ይህን መሰል ጥያቄዎች በጊዜው ይቀርቡ ነበር።

**ግዮን፡- አቶ በረከት ስምዖን በመጽሐፋቸው በእርስዎ ላይ አንዳንድ ነገሮችን አንሥተዋል። መጽሐፉን አንብበውት ከሆነ፤ ከዚህ አኳያ አስተያየትዎን ቢገልጹልን?**

ብ/ጀነራል ተፈራ፡- አቶ በረከት በመፅሐፉ ላይ ያለው "ጀነራል ተፈራ ማሞ ከምርጫ 97 በኋላ የትምክህት አመለካከት ያራምዳል፤ የተቋሙን መመሪያዎች መጣስና ከጓደኞቹ ጋር የመራቅ ሁኔታ ይስተዋልበት ነበር" የሚለውንና የመሳሰለውን ነው ያነሳው። "የትምክህት አመለካከት" የሚለውን በምርጫ 97 ብቻ ሳይሆን ከዛ በፊትም ያነሳው ነበር። ለምሳሌ ደርግ ከወደቀ በኋላ አዲስ አበባን ስናረጋጋ፤ ሁለት የኦሮሞ ድርጅቶች "እኔ ነኝ ፀረ ነፍጠኛ! እኔ ነኝ!" እየተባባሉ ይወዳደሩ ነበር። በዚህ ጊዜ የኦሕዴድ ካድሬዎች ሆን ብለው ጊዮርጊስ ያለው የምኒልክ ሐውልት ይፍረስ ብለው መጡ። እኔ ወዲያው ሰማሁና ቦታው ላይ ስሄድ "ሆ" እያሉ እየጨፈሩ ነው። ምን ሆናችሁ? ስላቸው "የምኒልክ ሐውልት ይፍረስ!" አሉ። ለምንድነው የሚፈርሰው? ሲባል ‹‹የነፍጠኛ ነው›› የሚል መልስ ሰጡ። "ይሄ የአገር ታሪክ እንጂ የምን ነፍጠኛ ነው? ትላንትና አንተ ወታደር ሆነህ "እምዬ ምኒልክ" እያልክ ስትዘፍን አልነበር ወይ?" ብዬ አባረርኳቸውና በሐውልቱ ላይ ጥበቃ መደብኩበት። ይህቺ እንግዲህ እንደ ትልቅ ዜና አብጣ ተሰማችና ምን ይላሉ? "ኦሮሞዎች ነፍጠኛ የፈፀመው በደል ከልባቸው ተሰምቷቸው ሲነሱ እሱ ግን ተከላከለ" አሉ። ተመልከት እንግዲህ ነፍጠኛና ትምክህት የሚለውን ስያሜ ለመስጠት ቸኩለው ሲያጠጋጉኝ። በዚህና በሌሎች አቋሞቼ ተነሥተው ከማንነቴ ጋር በማስተሳሰር እነ በረከት ትምክህተኛና ነፍጠኛ ያሉት ከምርጫ 97 በፊትም ነው። ምርጫ 97 ላይ እኔ ያልኩት "በምርጫው ሰሞን የተፈፀሙ ጭፍጨፋዎች ጣልያን ግራዚያኒ ከጨፈጨፈው የሚቀራረብ ነው" የሚል ሐሳብ ነበረኝ። በረከት ያን አባባሌን መነሻ አድርጎ ነው የፍረጃ ስያሜ የሰጠኝ።

ሌላው በረከት ያነሳው ‹‹መመሪያዎች አይቀበልም›› የሚል ነው፤ እዚህ ላይ እውነታ አለው። በሙሉ የተባረረው የአማራ ተወላጅ ለአምስት ዓመታት የትኛውም ቦታ ሥራ እንዳይቀጠር መመሪያ አውጥተው አስወሰኑ። ይሄን መመሪያም አልተቀበልኩትም ነበር፤የተባረረው የአማራ ጦር ጎዳና ላይ ወድቆ መቀጣጫ እንዲሆን ነው ሐሳባቸው። እነዚህ ልጆች ወደእኔ ሲመጡ አንድ ፅሑፍ አዘጋጀሁ። ልጆቹ በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ጠንካራ ትግል ያደረጉና በዲሲፕሊን የታነፁ በመሆኑ፤ የሥራ ቅጥር ትብብር እንዲደረግላቸው የሚል ይዘት ያለው የድጋፍ ደብዳቤ ለአብዛኞቹ አደልኳቸው። በዚያ የምስክር ወረቀት ደብዳቤ ምክንያት አብዛኞቹ ሥራ መያዛቸውን ሲረዱ ነው መመሪያ ይጥሳል የሚለው ምክንያት የቀረበብኝ። ይሄ ደግሞ ለእኔ ትክክለኛና ተገቢ ተግባር የምለው ነው።

**ግዮን፡- አሁን አገሪቱ እየገጠማት ላለው የፖለቲካ ቀውስ መንስኤውና ውጤቱ ምንድነው፤ መፍትሔውስ ምን መሆን አለበት ይላሉ?**

ብ/ጀነራል ተፈራ፡- መንስኤው አገራዊ ሥርዐት አለመኖር ነው። ከመነሻው ሥርዐቱ አገራዊ አይደለም። በአንድ ቡድን ጥቅምና ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ነው። ሌላው መንስኤ የሀብት ክፍፍሉ ፍትሐዊ አለመሆኑ ነው፤ አብዛኛውን ኅብረተሰብ አክስሮ የተወሰነውን ነው የሚያበለፅገው። ይሄ ደግሞ እንዳንፈላለግ ስለሚያደርገን የግጭቶች ሁሉ መንስኤ መሆኑ አይቀሬ ነው። መፍትሔው መሆን ያለበት ሁሉንም በእኩልነት የሚያስተናግድ →

አገራዊ ሥርዓት እንዲኖረን ማድረግ ነው፡፡ ደግሞ ተጋብተን ተዋልደናል፡፡ የጋራ ታሪክ፣ የጋራ አገር፣ የጋራ እምነትም አለን፡፡ ይህ ብቻውን ግን በቂ ስላልሆነ ሁሉን አሳታፊ የጋራ ሥርዐት ሊኖረን ይገባል፡፡ ለመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ጥብቅና የቆሙ አገራዊ ተቋማት ሊገነቡ ይገባል፡፡ ይሄን ለመፍጠር ደግሞ ሕዝቡ ምንጊዜም የበደለውን መታገል አለበት፡፡ ነገር ግን የትግሉ አቅጣጫ ንጹሐኖችን መንካት የለበትም፡፡ አገሬ ብለው በጉርብትናህ እየኖሩ እነሱ ምን አደረጉህ? ዋናው ጠላትህ ሰቅዞ ይዞህ እሱን መታገል እየተገባ፤ ኑ ውጡ ኑ ግቡ ማለቱ የዛሬን እያየህ የነገን አለማየት ነው፡፡

**ግዮን፡- በትግራይና በአማራ ክልል አጎራባች ቦታዎች ተደጋጋሚ ግጭቶች ይነሣሉ፡፡ እስካሁንም ያልበረዱ አሉና ስለነዚህ ጉዳዮችስ ምን ይላሉ?**

ብ/ጀነራል ተፈራ፡- ዋናው ችግሩ ያለው አሁንም ከአገራዊ ችግሩ ጋር ተሸርፎ ያለ ፍትሐዊ ልማት አለመኖሩ ነው፡፡ በአንድ ወገን የጠጠር መንገድ ጠሮበት ሲሰቃይ፤ በዚያኛው ወገን ደግሞ የአስፋልት ምቾት ያንገላታዋል፡፡ በሰሜን ጎንደር አቅጣጫ ደረጃቸውን የጠበቁ አስፋልቶች የትግራይን መሬት ሲጨርሱ ቆመዋል፡፡ አጠቃላይ አገራዊ በሆነ ደረጃ ከሆነ ፍትሐዊ የሆነ ልማት ያስፈልጋል ማለት ነው፡፡ ወደ ሁለቱ ክልል ጉዳይ ስንመጣ አንደኛው መንስኤ ሕወሓት በኃይል የወሰደው መሬት አለ፡፡ ሰቲት ሁመራ የተባለው በመሠረቱ ከጥንት ጀምሮ የአማራ ነው፡፡ ደብቀውት ነው እንጂ ሕወሓቶች ትግል ሲጀምሩ "ድንበራችን ተከዜ ምላሽ" የሚል ዘፈን ነበራቸው፡፡ ለህሊናቸው የሚኖሩ ታጋዮች ሁሌ ይናገሩታል ድንበራችን ተከዜ ነው እያሉ፡፡ መንገሻ ሥዩም አንድ ጊዜ በቪኦኤ የተናገረውም ከተከዜ ማዶ የአማራ ነው ብሎ ነው፡፡ እውነታው የትግራይ ሕዝብ በኢትዮጵያዊነታቸው መጥተው ያርሱ ነበር፡፡ ግን ምንም ችግር የለውም፡፡ ኢትዮጵያዊነታችን ካለ ጎንደር ላይ፣ ባሕር-ዳር ላይ ቢኖሩ የተጠናከረ አንድነት ይፈጥራል፡፡ ይሄ ሕወሓት በጉልበት የወሰደብን መሬት ሊመለስ ይገባል፡፡ ሁለተኛው የወፍላም መሬት፣ በኮረም የአላማጣውና የጨርጨር መሬት ነው፡፡ በዚያ አካባቢ ያለው ሕዝብ ሥነ-ልቦናው ከወሎ ጋር ነው፡፡ ይሄም ወደነበረበት ከተመለሰ መጀመሪያ ላይ የሁለቱ ክልሎች ግንኙነት ወደ ቀደመው ጤናማነቱ ለመመለስ በር ይከፍታል፡፡ ይሄ ካልሆነ እንኳን ለአብሮነት ለጉርብትና አንፈላለግም፡፡ የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ እየቆየ የሚፈነዳ ነው፡፡ እውነተኛ መፍትሔው ይሄው ነው፡፡

**ግዮን፡- ፈተና ላይ ያለው ቤተሰባዊ ትስስርስ?**

ብ/ጀነራል ተፈራ፡- ቤተሰባዊ ትስስሩማ ምንም የምትለየው ነገር አይደለም፡፡ ትግሬው ወደ አማራው ገብቷል፡፡ አማራው ወደ ትግራይ ገብቷል፡፡ አሁን ጎንደር ላይ ስትሄድ የትኛው አማራ፣የትኛው ትግሬ እንደሆነ እንኳን መለየት አትችልም፡፡ የወሎም እንደዛ ነው፡፡ ተዓምር እኮ ነው! ከጥንት ጀምሮ ድንበርተኞችና ክፉ ደጉን በጋራ ተባብረው ያሳለፉ ናቸው፡፡ አሁን ለተፈጠረው ችግር ዋነኛው ተጠያቂ ፖርቲው ነው፡፡ የሕወሓት ነጥቆ የመስፋፋት አደገኛ ፖሊሲ ነው ችግሩን የወለደው፡፡ እዚህ ላይ ፖርቲው "ሕወሓት ማለት የትግራይ ሕዝብ ነው፡፡ የትግራይ ሕዝብ ሕወሓት ነው" የሚል መርዝ ረጭቶ እውነቱን ከውሸቱ ቢያደበላልቀውም ሐቁን ግን ሕዝቡ ያውቀዋል፡፡ የትግራይ ሕዝብ ዘላለማዊ ነው፡፡ ሕወሓት ግን ዘላለማዊ ያልሆነ የአንድ ቡድን ስብስብ ነው፡፡ ከተወሰነ ዓመታት በኋላ የሚጠፋ ነው፡፡ በትክክል ካየነው በጉርብትናም ሆነ በብዙ ነገር ለትግራይ ሕዝብ ከአማራ በላይ አስተማማኝ ዋስትና የለውም፡፡ አማራውም እንደዛው፡፡



ብ/ጀነራል ተፈራ እና በቀለ ገርባ

**ግዮን፡- በ2000 ዓ.ም አሜሪካ ሄደው ነበር፡፡ ብዙ ሰውም በዛው ይቀራሉ ብሎ ጠብቆ ሳለ እርስዎ ግን እንደተባለው ሳይሆን ተመልሰዋል፡፡**

ብ/ጀነራል ተፈራ፡- አሜሪካ በአሸባሪነት ዙሪያ ላይ ለምታደርገው ውይይት ለመካፈል አትላንታ ጆርጂያ ነው የሄድኩት፡፡ በወቅቱ በማንነታችን ላይ ከባድ ጥቃት እየተፈፀመብን ስለነበር ለምን እዛው አትቀርም የሚሉ ጥያቄዎች ነበሩ፡፡ እኔ ግን ጭራሽኑ እዚህ ወገናችን በማንነቱ እየተገፋ ያንን ትቶ መቅረት የማንነቴም መገለጫ አይደለም፤ የተከፈለው መሥዋዕት ይከፈል እንጂ ወደ አገሬ ሄጄ የሚመጣውን እቀበላለሁ በሚል ተመልሼ መጣሁ፡፡ ችግሩን ተጋፍጦ መፍትሔ መፈለግ እንጅ ችግሩን በመሸሽ የሚፈጠር ለውጥ የለም፡፡ በብዙዎች የምታዘበውና የሚያሳዝነኝ በእኛ ደረጃ ያለ ኃይል ሸሽቶ እና እጁን አጣጥፎ ቁጭ ብሎ ማን ጉዳዩን እንዲይዘው ተፈልጎ እንደሆነ አይገባኝም፡፡

**ግዮን፡- በትግል ሕይወትዎ የተነሱበትን ዓላማ አሳክቻለሁ ይላሉ?**

ብ/ጀነራል ተፈራ፡- በግሌ አዎ አሳክቻለሁ፡፡ በራሴ ውሳኔ ለሆነ ለውጥ ወደ ትግል ገባሁ፤ በየጊዜው በእያንዳንዱ ተሳትፎ እዚህ ደረጃ ላይ ደርሻለሁ፡፡ በአጠቃላይ ትግሉ በአገራዊ ደረጃ የታለመለትን ውጤት ባያመጣም እኔ ግን መንገዴን እስካሁን ድረስ አልሳትኩም፡፡ በመጨረሻም ወደዚህ ደረጃ ያስገባኝም ያው "አለቅም" ያልኩት መንገዴ እንጂ ሌላ ፍላጎት ኖሮኝ አይደለም፡፡

**ግዮን፡- ጀነራል በሁለት ክፍል በዘለቀው ቆይታችን ሰፊ ሐሳብ ሲያንሸራሽሩ በመቆየትዎ ከልብ እያመሰገንን ቀረ የሚሉት ወይም የሚያስተላልፉት መልዕክትዎን ማሳረጊያ አድርገን የግዮን አንባቢያንን ይሰናበቱ፡፡**

ብ/ጀነራል ተፈራ፡- መልካም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ጊዜ ላለመቸገር፤ ዕድሜ ልክ እየተቸገረ ነው፡፡ ውስጣዊ ነፃነት ሊኖረው ይገባል፡፡ ውስጣዊ ነፃነት የሚመጣው በትግል በመሆኑ በሁሉም ቦታ መነጣጠሉ ቀርቶ በጋራ ነፃነትን ለማረጋገጥ መታገል አለበት፡፡ እውነተኛ ሥርዐትና እኩል ተጠቃሚነትን ለማግኘት እነዚህን በትግሉ ማረጋገጥ አለበት፡፡ እነዚህን ለማረጋገጥ ግን ከንጹሐኖች ጋር ግብግብ አያስፈልግም፡፡ ከወገን ጋር ግብግብ ሌላ ቁስል ለቀጣዩ ትውልድ ማውረስ ነው፡፡ ያለነፃነት ሕይወት የለም፡፡ በየቴሌቭዥኑ የሚባለው ሰላም፣ ልማት ሁሉ በነፃነት ውስጥ ነው የሚገኘው፡፡

---

ማረሚያ

በባለፈው የብ/ጀነራል ተፈራ ማሞ ቃለ ምልልስ በገጽ 17 ላይ ‹‹የተወለድኩት ጉማ ወረዳ ነው›› የሚለው በስህተት ስለሆነ ‹‹ቡግና ወረዳ›› በሚል ይስተካከል፡፡ በተለያዩ የጽሑፉ ገጾች ላይ ‹‹ሻለቃ›› የሚለው ቃል ‹‹ሻምበል ወይም ሐይል›› ተብሎ እንዲታረም ለአንባቢያን እንገልጻለን፡፡

ዝግጅት ክፍሉ

ምልከታ



በተረፈ ወርቁ

# የ«የፍቅር ሕግ» በቴዎድሮስ ካሣሁን ‹ማር እስከ ጧፍ› ዜማ!




## ፩. እንደ መንደርደሪያ

ጥበብ በአንድ አገር ሕዝቦች ታሪክና ሥልጣኔ ባህልና ቅርስ እንዲሁም የብሔራዊ ማንነት ግንባታ ሂደት ላይ የራሱ የሆነ ከፍተኛ ሚና አለው። ጥበብና የጥበብ ሥራዎች በተለያዩ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችና እንዲሁም በሰው ልጆች የዕለት ተዕለት ማኅበራዊ ግንኙነቶችና መስተጋብር ላይ ያለው ጉልህ አስተዋፅኦ ከፍተኛ እንደሆነም የዘርፉ ምሁራን ይስማሙበታል። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት (የኢኮኖሚክስ) ምሁር፣ ሐያሲና የሥነጽሑፍ ሰው ጋሽ አስፋው ዳምጤ ‹‹ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ›› ለሁለት ዓመታት በተከታታይ ባደረገው ‹‹ልማትና ባህል በኢትዮጵያ›› በሚለው የውይይት መድረክ ላይ ‹‹ሥነ-ጥበብና ልማት›› በሚል ባቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፋቸው፡-

‹‹…ሰው በተፈጥሮው ከአራዊት ወይም ከእንሰሳት የሚዛመድባቸውን ባሕርያት መሞረድ፣ ማለዘብ፣ እና የሰብዐዊነት ባሕርያቱን ማጎልበት፣ ብሎም የማኅበራዊ ሕይወት ንቃቱን ከፍ በማድረግ፣ በጎና ሁለንተናዊ ለሆኑ የልማት የጋራ ግቦች ለመነሳሳት ምቹ የሚያደርገው የአስተሳሰብ ዝንባሌ እና አመለካከት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የጥበብ ዘርፎች ሁሉ ዓላማና ግብ ነው።›› በማለት የጥበብ ሥራዎች በሰው ልጆች ሁለንተናዊ ሕይወት ውስጥ ያለውን ዘርፈ ብዙ ፋይዳውን እንዲህ ገልጸውታል።

በጥበብ ዘርፍ ውስጥ ከሚካተቱትና ከፍጥረት ወይም ከሰው ልጆች ታሪክ ጅማሬ ዘመን ጋር አቻ ሊባል በሚችል በጥንታዊነቱ የሚነሳው የሙዚቃ ጥበብ በሰው ልጆች ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሕይወት ውስጥ ትልቅ አሻራ እንዳለው ብዙዎች የዘርፉ ምሁራን ይስማሙበታል።

ከዚሁ ከጥበብ ሥራ ጋር በተያያዘም የአገራችን ሙዚቃ በአፍሪካ ሆነ በዓለም መድረክ ምን ያህል ተደማጭ ነው?፣ ምን ያህልስ ተጽእኖ ፈጥሯል?፣ ሙዚቃችን እያደገ ነው ወይስ …?፣ ባለሙያዎቻችንስ በጥበብ ሥራዎቻቸው የወጡበትን ወይም የተገኙበትን የሕዝባቸውን ወይም የአገራቸውን ታሪክ፣ ባህል፣ ቅርስ፣ ትውፊት፣ ማንነት እያስተዋወቁ ነውን?፤ በአገራችን ያሉ የጥበብ ባለሙያዎችስ ላለንበትና ለሚያጋጥሙን ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተግዳሮቶቻችንና ፈተናዎች መፍትሔ በማመላከት፣ ስለ ፍቅርና ተስፋ፣ ስለ →

ሠላምና ዕርቅ፣ ነጻነትና ፍትሕ በመጮኽ፤ ለሕዝባቸው አንደበት፣ ዓይንና ጆሮ በመሆን ሙያዊ ግዴታቸውን እየተወጡ ነው ወይ ወይስ …? ወዘተ. የሚሉ ጥያቄዎችን ብናነሣ ምላሹ ብዙም የሚያረካ እንዳልሆነ እርግጠኛ ነኝ፡፡

በነጋ ጠባ "የሙዚቃችን ነገር ወዴት እየሔደ ነው" በሚል እሮሮና ብሶት በገነነበት በዚህ በእኛ ዘመን በአገራችን የሙዚቃ ኢንዱስትሪ ውስጥ እንደ መስቀል ወፍ ብቅ በማለት እንደ አጥቢያ ኮከብ ደምቀው ያበሩና እያበሩ ያሉ ከያኒዎችን አልፎ አልፎም ቢሆን አይተናል፡፡ ክፋቱ ቁጥራቸው ጥቂት ሆነ እንጂ፡፡ ከእነዚሁ በቁጥር ጥቂት ከሆኑ የእኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን የሙዚቃ ባለሙያዎቻችን መካከልም ከያኒ ቴዎድሮስ ካሣሁን (ቴዲ አፍሮ) በግንባር ቀደምትነት ተጠቃሽ ይመስለኛል፡፡

በዚህ በዛሬው ጽሑፌ በጥበብ ዘርፍ ውስጥ ግዙፍ ድርሻና ረጅም ታሪክ ስላለው ስለሙዚቃ በመግቢያዬ አንዳንድ ቁም ነገሮችን ማንሣቴ አለምክንያት አይደለም፡፡ በያዝነው ዓመት መባቻ ላይ ቴዎድሮስ ካሣሁን (ቴዲ አፍሮ) ባወጣው ‹ኢትዮጵያ› በሚለው አልበሙ የዕውቁን ኢትዮጵያዊ ደራሲ፣ የክቡር፣ ዶ/ር ሐዲስ አለማየሁን ዘመን አይሽሬ (Classical) የኾነውን ‹ፍቅር እስከ መቃብር› የልቦለድ ድርሰትን መሠረት አድርጎ በተሠራው ‹‹ማር እስከ ጧፍ›› በሚለው የዘፈን ስንኞች ላይ ከያኒው በግጥሞቹ ውስጥ ስላካተታቸው ‹የፍቅርን ሕግ የወንጌልን ሕግ› ስለሚያንጸባርቁ የግጥም ስንኞቹ ከክርስትና ሐይማኖት አስተምኅሮ አንጻር ጥቂት የራሴን የሆነ ምልከታና አስተያየት ለማካፈል በማሰብ ነው፡፡

## ፪. የ‹‹ፍቅርሕግ›› በ ‹ማር እስከ ጧፍ› ዜማ የግጥም ስንኞች፡-

በቴዎድሮስ ካሣሁን በሁሉም የሙዚቃ ድርሰት ሥራዎቹ ውስጥ ሊባል በሚችል ደረጃና በተለየ ኹኔታ ‹ፍቅር› ዋነኛ ርዕሰ ጉዳይ ሆኖ በተደጋጋሚ ቀርቧል፡፡ ከያኒው በሙዚቃ ድርሰቶቹ ውስጥም ሆነ ስለ ሥራዎቹ በሚሰጣቸው ቃለ ምልልሶችና ማብራሪያዎችም ‹ፍቅር› ግንባር ቀደምትነት የጥበብ ሥራው መሠረትና የማዕዘን ድንጋይ እንደሆነ በተለያዩ ጊዜያት በአጽንኦት ሲገልጽ ሰምተነዋል፡፡

የቴዲ አፍሮ እነዚህ የፍቅር ዜማዎቹ ከነገረ ሐይማኖት- ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አስተምኅሮ፣ ከቤተክርስቲያኒቱ ታሪክ፣ መንፈሳዊ ትውፊትና ሥርዓት ጋር ጥብቅ የኾነ ቁርኝት ያለው መሆኑ በሥራዎቹ ውስጥ በሚገባና በግልጽ ይንጸባረቃል፡፡ ከያኒው ለአገሩ ኢትዮጵያ የሺሕ ዘመናት ታሪክ፣ ገናና ሥልጣኔ፣ ባህልና ትውፊት ካለው ስሱነትና ቅናት (Sensitivity) የተነሣም ከሚለያየን ይልቅ በፍቅር- በአንድነት የሚያስተሳስረንን የታሪካችንን ሰበዝ በመምዘዝ በጠንካራ የግጥሞቹ መልዕክትና ውብ የዜማዎቹ ፍሰት ፍቅርን ከፍ ከፍ በማድረግ፣ የሚበጀን አንድነትና ኅብረት መሆኑን ለመስበክ ተጠቅሞበታል፡፡

ቴዲ የታሪክ ምሁራኑ፤ ‹‹የታሪክ ዕውቀት ለኅብረተሰብ ዕድገት ቁልፍ መሳሪያ ነው፡፡ ›› የሚለውን የታሪክ ሐቅ ከመረዳቱም በላይ በተከታታይ የሙዚቃ ሥራዎቹ ተግባራዊነቱን በተጨባጭ ሊያሣየን ሞክሯል፡፡ ከጃ ያስተሰርያል (ከግርማዊነታቸው) እስከ ጥቁር ሰው፣ ከዳህላክ እስከ ፊዮሪና፣ ከአክሱም ሐውልት እስከ ፋሲል ግምብ፣ ከደብተራ ተዋናይ እስከ ሐዲስ ዓለማየሁ- በዛብህና ሰብለ የፍቅር ገድል ውስጥ፤ የኢትዮጵያዊነት - ታሪክና ሥልጣኔ፣ ባህልና ቅርስ፣ ፍቅርና አንድነት በብዙ ከፍ ከፍ ተደርገዋል፡፡ ከያኒው ታሪክን በሚገባ መመርመር ያለውን ጠቀሜታ ከመረዳት በላይም ታሪካችንን ለጥበብ ሥራዎቹ መሠረት፣ የማዕዘን ድንጋይ፣ ውበትና ድምቀት አድርጎ ተጠቅሞባቸዋል፡፡ በዚህም ከአገርና ከአኅጉር አልፎ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሳይቀር ትልቅ ስኬትን ተጎናጽፎበታል፡፡

‹‹ (A People without History is like a Tree without a Root) ታሪክ የሌለው ወይም ታሪኩን የማያውቅ ሕዝብ/አገር ሥር እንደሌለው ዛፍ ማለት ነው፡፡›› እንዲል የቀድሞው የአሜሪካ ጥቁር ፕሬዝደንት ባራክ ኦባማ፤ ቴዲ አፍሮ የሺሕ ዘመናት አኩሪ ታሪካችን እና ገናና ሥልጣኔያችን፣ የትናንትና ማንነታችን መሠረትና ለአገራችን የወደፊት ርዕይና የዕድገት ግሥጋሴ ቁልፍ መሆኑን ደጋግሞ አቀንቅኗል፤ እንዲሁም ክፉና በጎ ያልኾኑ የትናንትና የታሪክ ውርሶቻችንም በፍቅርና በሠላም መንገድ በመነጋገርና በመግባባት አስወግደን ወደፊት መራመድ እንዳለብንም ፍቅርን ከፍ በማድረግ-ሠላምን፣ ይቅርታን፣ ዕርቅን በሙዚቃዎቹ ሰብኳል፤ እየሰበከም ነው፡፡

ቴዎድሮስ ካሣሁን በዚህ አብዝተው ፍቅርን በሚሰብኩ የጥበብ ሥራዎቹም በብዙዎች ልብ ውስጥ በፍቅር እንዲነግሥ፣ ታላቅ የክብርና የዝና አክሊልን እንዲደፋም አስችሎታል፡፡ ዘንድሮው ‹‹ኢትዮጵያ›› የሚል ስያሜ በሰጠው አልበሙም እንደቀደሙት ሥራዎቹ ሁሉ ‹ፍቅር› ዋንኛ ርዕሰ ጉዳዩና ዐቢይ መልእክቱ ሆኖ ቀርቦአል፡፡ በዚህ ጽሑፌ በተለይም ደግሞ ‹‹ማር እስከ ጧፍ›› በሚለው ሥራው ውስጥ የተካተቱትንና ያስገረሙኝ፣ ግን ደግሞ እምብዛም ያስተዋልናቸው የማይመስሉ የግጥም ስንኞች ናቸው ለዚህ ጽሑፌ ዐቢይ ምክንያት የሆኑኝ፡፡ እንሆ ከእነዚህ ግጥሞች ውስጥ ልጥቀስ፡-

‹‹ለካ ሰው አይድንም በደገመው መጽሐፍ፣
እንደ ሰም አቅልጦ ፍቅር ካረገው ጧፍ፤
‹‹ለካ ሰው አይድንም በኦሪቱ ገድል፣
ወንጌል ይዞ ገብቶ ፍቅር ካረገ ድል፡፡››

በእነዚህ የግጥም ስንኞች ውስጥ አንድ ዘላለማዊ፣መለኮታዊ እውነትን ፈልቅቀን ለማየት እንሞክር እስቲ፡፡ ቴዲ በእነዚህ ዐራት አንጓ በኾኑ የግጥሙ ስንኞች ውስጥ ከሰው ልጆች የሥነ-ፍጥረት ታሪክ ጅማሬ በመነሣት፣ ሰው የአምላኩን ትእዛዝና ሕግ አፍርሶ በኃጢአት በወደቀበትና በዚህም የተነሣ ደግሞ በተላለፈበት ፍርድ-ከወደቀበት የሞት ፍርሃትና የሲኦል ባርነት ከዛሬ ከ፳ሺሕ ፳፻ ዓመታት በፊት በተገባለት አምላካዊ የተስፋ ቃል መሠረት ከኃጢአትና ከሞት ባርነት ነጻ የወጣው በ‹‹ፍቅር/የወንጌልሕግ›› መሆኑን ነው በሚገርም አስተውሎት ሊያስታውሰን፣ ሊያሳስበን የሞከረው፡፡

ይህን ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊ ሐሳብ በጥቂቱ ለማብራራት ልሞክር እስቲ፡፡ እንደ ክርስትና ሃይማኖት አስተምህሮ ‹‹ሰው የመለኮት ባሕርይ ተካፋይ የኾነ እጅግ የከበረ ፍጥረት ነው፡፡›› ሁሉም ፍጥረት ስለ ሰው ፍቅርና ስለ ሰው ክብር ተፈጥሯል፡፡ በሃይማኖትም ኾነ በሳይንሱ ዓለም፡ - ሰው የፍጥረተ ዓለሙ ሁሉ ቁንጮ፣ ዕፁብ፣ ድንቅና ውብ ፍጥረት እንደሆነ ነው አብዝተው የሚናገሩት፣ የሚያስተምሩት፡፡

በሥነ ፍጥረት ታሪክ ውስጥ በስድስቱ ቀናት ከተፈጠሩት ፳፪ቱ ፍጥረታት መካከል ሰውን የሚተካከል ፍጥረት የለም፤ አልኖረም፤ አይኖርምም፡፡ ፈጣሪ ሰውን ከፈጠረ በኋላ ‹‹ከፈጠራቸው ፍጥረታት ሁሉ መካከል ሰው እጅግ መልካም እንደሆነ ዐየ፤›› ይለናል የኦሪት ዘፍጥረት መጽሐፍ ጸሐፊ ሊቀ ነቢያት ሙሴ፡፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትም ለሰው ልጅ ድንቅ ስለሆነ አፈጣጠሩና በአምላኩ ዘንድ ስለተቸረው ፍቅርና ክብር ሲናገሩ ‹‹ሰውን እጅግ ወደደው፣ ሳመው፣ አከበረውም፡፡›› ይሉናል፡፡ ‹‹ቅዱሳት በሚሆኑ እጆቹ በርሱ አሳምሮ ፈጠረው፣ ሳመው፣ ወደደውም፡፡ የሕይወትንም መንፈስ በርሱ ላይ እፍ አለ፡፡›› እንዲሉ ሠለስቱ ምዕት /፫፻፲፰ቱ ሊቃውንት በቅዳሴያቸው፡፡

በተመሳሳይም ከዓለማውያን ጸሐፍት መካከልም እንግሊዛዊው ደራሲ፣ ባለ ቅኔና ጸሐፊ ተውኔት ዊሊያም ሼክሲፒርም በሐምሌት ድርሰቱ ውስጥ የሰውን ክቡርነትና ታላቅነት እንዲህ ይገልጸዋል፡- ‹‹… ሰው እንዴት ዕፁብና ድንቅ ፍጥረት ነው፤ በቅርፁ በውበቱና በንግግሩስ እንዴት ያስደንቃል! በሥራውም መላእክትን ይመስላል፤ በመልኩም የፈጣሪውን! የዚህ ዓለም ድንቅ ውበት፣ ድንቅ ሥራ፣ ከፍጥረታት ሁሉ የላቀ!! ሐሳቡስ እንዴት ክቡር ነው፡፡ ለአፈጣጠሩም ጥበብ ማብቂያ አይገኝለትም፡፡››

እንደ ሚልተን ያሉ የምድራችን ዕውቅ ባለ ቅኔም ‹Paradise Lost› በሚለው ሥራው ውስጥ ሰውን እንዲህ ይገልጸዋል፤ ‹‹እንደ ሌሎች ፍጥረታት አራዊት ያልኾነ፣ በማሰብ ብቃቱ የተቀደሰ … በክብሩም እንደ ገነት የተፈራና የገነነ …፡፡›› በመንፈሳዊውም ሆነ በሳይንሱ ዓለም አስተምህሮ ትልቆ መሣፍርት ከሌላቸው የእግዚአብሔር ሥነ-ፍጥረታት መካከል፤ ሰው በአምላኩ አርአያና ምሳሌ በፍቅር ስለ ፍቅር የተፈጠረ እጅግ የተከበረ፣ ድንቅ፣ ክቡርና ግሩም ፍጥረት ነው፡፡

ይህ ፈጣሪ ለሰው ልጆች ያለው ልዩ ፍቅር በሥነ ፍጥረት ታሪክ ሒደት ውስጥ ብቻ ሣይሆን በኋለኛው ዘመን ራሱ ፈጣሪ አምላክ ሰው በኾነበት አስደናቂ ፍቅሩ፤‹‹የሰው ልጅ ከተፈጠረበት የፍቅር ጥበብ ይልቅ የዳነበት የፍቅር ጥበብ ይልቃል፣ ይደንቃል፡፡›› ሲሉ የሃይማኖት መተርጉማን ሰው በፈጣሪው ዘንድ የተቸረውን፣ ከማስተዋል የሚያልፈውን፣ ታላቅ የኾነውን የፍቅሩንና የክብሩን ልዕልና ያመሰጥራሉ፡፡ ይህ የፈጣሪ ዘላለማዊ ፍቅርም ከቤተልሔም ግርግም እስከ ቀራኒዮ ተራራ በፍቅር ተጀምሮ በፍቅር የተቋጨ ድንቅ እንደሆነ ያወሳሉ፤ ይተርካሉም፡፡ ‹‹ዘንተ ኵሎ በእንተ ፍቅረ ሰብእ ገበርከ - ይህን ሁሉ ስለ ሰው ፍቅር አደረግኽ፡፡›› እንዲሉ አበው ሊቃውንት፡፡

የቤተክርስቲያናችን ሊቅ የኾነው ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም በቅዳሴው፤ በኃጢአትና በአለመታዘዝ ምክንያት የሞት ፍርድና ኩነኔ የታወጀበትን ሰውን ለማዳን እግዚአብሔርን ፍቅር ከዙፋኑ እንደሳበው እንዲህ ሲል ይናገራል፡ - ‹‹ኃያል ወልድን ፍቅር ከመንበሩ ሳበው እስከ ሞትም ድረስ አደረሰው፡፡››

ቴዲ አፍሮ በ‹‹ማር እስከ ጧፍ›› ዜማው ግጥሙ ውስጥ ይህን የሰው ልጅ የዳነበትን ዘላለማዊ ድንቅ ምሥጢር ፍቅር መሆኑን ያዜማል፤ ይቀኛል፡፡ የድኅነታችን መሠረትም ይኸው ‹መለኮታዊ ፍቅር› መኾኑን ያወሳል፡፡ ‹‹ሕገ ኦሪት›› ፍቅር በሆነው በ‹‹ሕግ ወንጌል›› ፍጻሜን እንዳገኘችና በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት፣ የእናታችንና የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ልጅ፣ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ- ጌታችንና አምላካችን፣ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ‹ፍጹም ሰው፣ ፍጹም አምላክ ሆኖ› በፍቅሩ ሰውን ማዳኑን፣ ለሰው ልጆች ሁሉ ቤዛ፣ መድኃኒት መሆኑን ያመሰጥራል፡፡

የሚደንቀው ነገር ከያኒው በዚህ የግጥም ስንኞቹ በሕገ-ኦሪት/በሙሴ ሕግ ውስጥ ያሉ ሁሉ እነርሱ ከዚህ ዘላለማዊ ከኾነው ከእግዚአብሔር ፍቅር ተራቁተውና ከተስፋው ቃል ተለይተው፣ ያለ ተስፋ በሞት ፍርሃትና በሲኦል ባርነት ውስጥ እንዳሉም ይሰብካል፤ ያውጃል፤ እንዲህ ሲል፡፡

‹‹ለካ ሰው አይድንም በኦሪቱ ገድል፣
ወንጌል ይዞ መጥቶ ፍቅር ካረገ ድል፤››

እንግዲህ ‹‹ማር እስከ ጧፍ›› ዜማ ፈርጀ ብዙ በኾነው የግጥሞቹ ስንኞቹ ‹ፍቅር የሁሉ ነገር ፍጻሜ፣ የመዳናችን እውነትና ታላቅ ምሥጢር› እንደሆነ ነው ሊያስታውሰን፣ ሊያሳስበን

የሞከረው። መጽሐፍም፡- ‹‹ፍቅር ሕግ ፍጻሜ ነው።›› እንዲል። ‹‹የሰው ልጅ በሰዎችና በመላእክት ልሳን ቢናገር፣ ተራራን የሚያፈልስ፣ ሙታንን ከመቃብር የሚያስነሳ ታላቅ እምነት ቢኖረው፣ ኃላፊውንና መጻኢውን ጊዜ ለማወቅ የሚያስችል እውቀትን፤ የተሰወረውንና የተሸሸገውን ምሥጢራትን ሁሉ የሚያውቅበት ጥበብን ቢታደል፣ ያለውን ሁሉ ለድሆች ቢሰጥ እንኳን …ፍቅር ግን ከሌለው ከንቱ ነው።›› ይህ ሁሉ ያለ ፍቅር ‹እንደሚንሸዋሸዋ ጽናጽል› ከመሆን ያለፈ ፋይዳ እንደሌለው ነው ብርሃን ዓለም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በጻፈው መልእክቱ ላይ የሚነግረን።

## ፫. ያለ ፍቅር ሁሉም ከንቱ ነው!

ቴዲ አፍሮ በዚሁ ‹ማር እስከ ጧፍ› ዜማው የግጥሙ ሌላኛው ስንኞች ውስጥ ደግሞ ተመሳሳይና ተያያዥ የሆነ የፍቅርን እሳቤን የሚያቀነቅን ዘላለማዊ እውነትን ይሰብካል። እንዲህ ሲል፡-

‹‹ለካ ሰው አይድንም በደገመው መጽሐፍ፣
እንደ ሰም አቅልጦ ፍቅር ካረገው ጧፍ፤››

ከያኒው በዚህ ግጥሙ ጸሎት ያለ ፍቅር፣ እምነት በፍቅር የሆነ ሥራ ከሌለው ከንቱ እንደሆነ በስንኞቹ በማንጻሪያነት ተጠቅሞበታል። እስቲ ይሄን ሐሳብ በጥቂቱ ዘርዘር አድርገን እንየው። የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የ‹ዳዊት ጸሎት› በሁሉም መንፈሳዊ አገልግሎቶቿ ውስጥ አብዝታ የምትጠቀምበት የጸሎት መጽሐፍ ነው። እንደ ቤተክርስቲያናችን አምልኮ ሥርዓትና ትውፊትም መዝሙረ ዳዊት አባቶቻችን ካህናትና ምእመናን ጠዋት ማታ የሚደግሙትና ከፈጣሪያቸው ጋር የሚገናኙበት፣ የሚነጋገሩበት እጅግ የተወደደና ከፍ ያለ ክብር የሚሰጠው መንፈሳዊ ድርሰት መሆኑም የታወቀ ነው። ለዚህም ይመስላል አበው የዳዊት ጸሎትን ‹ጸሎቶች ሁሉ ጸሎት› መሆኑን ከፍ ለማድረግና ለማጉላት ሲሉም እንዲህ መተረታቸው። ‹‹ከዘመድ እናት፣ ከምግብ ፍትፍት ከጸሎትም ዳዊት።››

ግና ማንም በጸሎቱ ትጉና ብርቱ የሆነ ግን ደግሞ በፍቅር ከሆነ ቅንነት፣ በጎነት የጎደለ ሰው ቢኖር እርሱ ምስኪንና ከሕይወት መንገድ የተሳሳተ መሆኑን አጉልተውና አስፍተው ያስተምራሉ። የቴዲ አፍሮ ‹ማር እስከ ጧፍ› የግጥም ስንኞች ይህን የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንን ሊቃውንት አስተምህሮ ነው ሊያስታውሱን፣ ሊነግሩን የፈለጉት። አባቶቻችንም‹‹ከ፻፶ዳዊት የልብ ቅንነት/ገርነት ይበልጣል›› ሲሉ መተረታቸውም ያለ ፍቅር የሆነ፣ ቅንነትና በጎነት በጎደለው ሕሊና በየቀኑ ከምንደግመው ጸሎት ይልቅ ከፍቅር የኾነ ቅንነት፣ በጎነት የሚበልጥና የሚልቅ መሆኑን ሲያስተምሩን፤ ሲያመሰጥሩልን ነው።

ይህን ሐሳብ የሚያጠናክርልኝ ገዳማውያን አባቶቻችን በልብ ቅንነት፣ በፍቅር የሚደረግ ጸሎት ዋጋው ከፍ ያለና በፈጣሪ ዘንድም ተሰሚነት ያለው መሆኑን ከሚያሳስቡበት ታሪኮች መካከል አንዱን ላንሣ። በአንድ ደሴት የሚኖሩ መነኮሳት አባቶች መካከል ገዳማውያኑን የተቀላቀሉ ወጣኒ/ጀማሪ መናኝ ሰው ነበሩ። እኚህ ሰው ትምህርት የሌላቸው ግን ደግሞ ልበ ቅን የፍቅር ሰው ነበሩ። እኚህ ገዳማዊ መናኝ ሰው ዘወትር ሲጸልዩ ‹‹አትማረኝ አትማረኝ እያሉ ነበር፤ ታዲያ በአንድ ወቅት ይህን ጸሎት ሲደግም የሰሙት መናንያን አባቶች መካከል አንዱ መነኮስ እንዲህ አሏቸው፡- ‹‹አባቴ ይህ እንዴት ያለ ጸሎት ነው?! ከዛሬ ጀምረው መጸለይ ያለብዎት ማረኝ! ማረኝ! እያሉ ነው፤›› በማለት የጌታችንን ‹የአቡነ ዘበሰማያትን› ጸሎት አስጠንተዋቸው ይለያያሉ።

ታዲያ በነገታው እኚህ ብዙም ትምህርት የሌላቸው መናኝ እኚያ የገዳሙ አባት ያስተማሯቸው ጸሎት ይጠፋቸዋል። እናም በደሴቲቱ ባሕር ላይ በታንኳ ተሳፍረው ወደ ሌላ ቦታ ወደሚሔዱት መናኝ አባት ዘንድ በባሕሩ ላይ በእግራቸው እየሮጡ፤ ‹‹አባቴ እረ! ያስተማሩኝ ጸሎት ጠፋኝ›› በማለት እየጮኹ ወደ እርሳቸው ይገሰግሳሉ። መነኩሴው አባትም እንደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በባሕሩ ላይ በእምነት ሲራመዱ፣ ያይዋቸውን አባት የእምነታቸውን ታላቅነትና የልባቸውን ቅንነት በማድነቅ፤ ‹‹አባቴ ሆይ አልተሳሳቱም፤ ድሮ የሚጸልዩትን ጸሎት ጸልዩ፤ እርሱን አታቋርጡ አሏቸው።›› በታንኳቸው ላይ እንዳሉ።

ይህ ታሪክ ‹‹ከ፻፶ ዳዊት የልብ ቅንነት›› የሚለውን የአባቶቻችንን አባባል የሚያጠናክርልን ነው። ልብ አምላክ ዳዊትም በጸሎቱ፤‹‹ቅንነት ፊትህን ታየዋለች።›› ሲል መጸለዩ ሰዎች በፍቅር በሆነ ቅን ልብና በትሑት መንፈስ ፈጣሪያቸውን ለማየትና እንደሚቻላቸው ሲያመሰጥር ነው። የቤተክርስቲያናችን አባት የሆነው አባ ሕርያቆስ በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ቅዳሴው፤ ‹‹በፍቅር፣ በትሕትና፣መንፈስን ንጹሕ በማድረግ ነቢያት እግዚአብሔርን አይተውታልና፤ ፊት ለፊትም ተያይተዋልና።›› እንዲል።

## ፬. እንደ መውጫ/ማጠቃለያ

እንግዲህ ፈጣሪን የምናይበት፣ ከሞት ወደ ሕይወት፣ ከጨለማ ወደ ብርሃን የተሸጋገርንበት ታላቁ ጥበብ፣ ዘላለማዊው እውነት ፍቅር መሆኑን ልብ ይሏል። ከያኒ ቴዎድሮስ ካሣሁን/ቴዲ አፍሮም በጥበብ ሥራዎች ስለዚህ ታላቅ ፍቅር፣ ስለዚህ ዘላለማዊ እውነት ደጋግሞ አቀንቅኗል፤ ሰብኳል። ከያኒው ‹በማር እስከ ጧፍ› ዜማውም እስከ መቃብር ድረስ በዘለቀው በሰብለ ወንጌልና በበዛብህ ፍቅር መነሻነት በዛብህ በውክልና የቆመላትን የጥንታዊቷን፣ የሐዋርያዊቷን፣ ኩላዊቷን/Universal የሆነችውን የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን አስተምህሮ፤‹የፍቅር ሕግ/የወንጌል ሕግ የሕገ-ኦሪት ፍጻሜና የሰው ልጆች ሁሉ ድኅነት መሠረት መሆኑን› በአራት ስንኞች ግጥም ውስጥ እንዲህ በሚደንቅ መንፈሳዊ ጥበብና አስተውሎ ሊያሳስበን፣ ሊያስታውሰን ሞክሯል። ቴዲ አፍሮ በዚህና በሌሎቹ ቀደምት ሥራዎቹም ይህ ‹የፍቅር ሕግ› በልዩነትና በደም ለደመቀው ፖለቲካችን መፍትሔ መሆኑንንም ደጋግሞ አንስቶታል።

በእውነትም፣ በእርግጥም ይህ የፍቅር ሕግ/የወንጌል ሕግ የሰው ልጆችን ሁሉ ከሞት ወደ ሕይወት፤ ከድቅድቅ ጨለማ ወደ ሚደነቅ ብርሃን ያሻገረን ቅዱስ ሕግ ነው፤ ይህ የፍቅር ሕግ/የወንጌል ሕግ ወዳጆቻችን ብቻ ሣይሆን ጠላቶቻችንንም ጭምር እንድንወድ የሚያስተምረን ሕግ ነው፤ ይህ የፍቅር ሕግ የዘር፣ የድንበር፣ የቋንቋ … ወዘተ. ልዩነት ሳያደረግ ሁሉን የሚቀበል፣ ሁሉንም የሚያቅፍ ሕግ ነው፤ ይህ የፍቅር/የወንጌል ሕግ በራሳችን ላይ እንዲሆን የማንፈልገውን ማንኛቸውንም ነገር በሌሎች ላይ እንዲሆን የማንፈቅድበት ሁሉን በፍቅር የሚገዛ ‹ወርቃማ ሕግ› ነው።

በዚህ የፍቅር ሕግ የዘረኝነት ግምብ ተንዷል፣ የጥላቻ አጥር ፈራርሷል፣ የልዩነት ድንበር ተጥሷል። በዚህ የፍቅር ሕግ የዓለማችን ታላላቅ ፖለቲከኞችና የነጻነት ታጋዮች የጠላቶቻቸውን ልብ ማርከውበታል፣ የሕዝባቸውንና የዓለምን ልብ ሁሉ አሸንፈውበታል። አሜሪካዊው የጥቁር ሕዝቦች መብት ታጋይ፣ የሃይማኖት ሰባኪና የሥነ መለኮት ምሁር የሆኑት ዶ/ር ኪንግ ማርቲን ሉተር፣ The Strength of Love በሚለው መጽሐፋቸው፤ በወንጌል ቅዱስ ቃል ‹‹ባልንጀራህን እንደ ራስህ አድርገህ ወደድ፣ ጠላትህንም ጭምር ውደድ›› የሚለው የክርስትናው ዓለም ‹ወርቃማ ሕግ/የፍቅር ሕግ/የወንጌል ሕግ› ለጥቁር ሕዝቦች መብት መከበር ባደረጉት እልህ አስጨራሽ ትግላቸው ለአሸናፊነትና ለድል እንዳበቃቸው በስፋት ጽፈዋል።

በሌላም በኩል አፍሪካዊው ‹የሰላምና የዕርቅ ሰው› ኔልሰን ሮሂላላ ማንዴላ/ሚዲባም ይኽንኑ ‹የፍቅር ሕግ› በመጠቀም ያን ዘረኛውንና አስከፊውን የአፓርታይድ ሥርዓት ከራሳቸውና ከሕዝባቸው ጫንቃ ላይ እንዲወርድ አድርገዋል። ማንዴላ በፍቅር ሕግ የዘረኝነትን፣ የጥላቻን፣ የልዩነትን ግምብ በመናድ ለሰው ልጆች ሁሉ ፍቅር፣ ሰላምን፣ ዕርቅን ሰብከዋል። በዚህ ‹የፍቅር ሕግ› በቃል አስተምረው፣ በተግባር ኖረው ሌሎችም እንዲኖሩ አስተምረው አልፈዋል። ማንዴላ ጥላቻና ክፋት በነገሠባት ዓለማችን ‹በፍቅር ሕግ› መርሕ ለመኖር መንገዱ ሁሌም አልጋ በአልጋ እንደማይሆንና፣ ሰላምንና ፍቅርን የሚሰብኩ፣ ጥላቻንና መለያየትን የሚያወግዙ፣ ለፍትሕና ለእውነት በጽናት የሚከራከሩ እነርሱ - በመንገዳቸው ላይ መከራንና የእሾኽ አክሊልን መጋፈጥ እንደሚያጋጥማቸውም በአንድ ወቅት በአንድ ዓለም አቀፍ መድረክ ባደረጉት ንግግራቸው እንዲህ ገልጸውት ነበር፤

“The path of those who preach Love, and not Hatred, is not easy. They often have to wear a crown of thorns.” ~Nelson Mandela from a message to the Global Convention on Peace and Non-violence, New Delhi, India, 31 January 2004.

*መልካም የሰሙነ ሕማማት ሳምንት ይሁንላችሁ!*

*ሰላም!*





**ደረጀ መላኩ**

# የቅዠት ሰዎች ወረራና የዕልም ዛፎች ተጋድሎ

በድንጋይ ዘመን ‹‹ዕልም›› የምትባል የዛፎች አገር ነበረች። ይህቺን የዛፎች አገር በተለያየ ጊዜ የቅዠት ሰዎች ሊደፍሯት ቢሞክሩም ጥቅጥቅ ደኗ ስለሚያስፈራ፣ አንበሶችና ነብሮችም ስለሚኖሩባት ሳትደፈር ትኖር ነበር። የቅዠት ሰዎች ዕልምን በእሳት ሊያቃጥሉ ደጋግመው ቢሞክሩም የዕልም ምድር ደረቅ ስላልነበረ፣ ዝናብም ስለማይጠፋ የማቃጠሉ ተንኮል ሳይሳካ ቀረ። የድንጋይ ዘመን ሲገባደድና ባልጩት በብረት መሣሪያ ሲተካ የቅዠት ሰዎች ዕልምን በምሳር ለመድፈር የስለላ ጉንጉን መጎንጎንና መረብ መዘርጋት ጀመሩ።

የቅዠት ሰዎች የስለላ መረብ በይበልጥ የተዘረጋው ከጠማማ ዛፎች ዙሪያ ነበር። ጠማማ ዛፎች ቀጥ ብለው መውጣትና መቆም ስለማይችሉ፣ ቀጥ ያሉት ዛፎች “ጎባጦች፣ አጎብዳጆችና አጎንባሾች” እያሉ ይንቋቸው ነበር። ጠማማ ዛፎች በፊንታቸው ቀጥ ያሉ ዛፎችን እንደ ረጅሟ የአለቃ ገብረሐና ሚስት ወይዘሮ ማዘንጊያ ሽቅብ እያዩ “ሥራቸውን ቢቦድሱት ማየትና መስማት የማይችሉ ቀውላሎች!” እያሉ ይሰድቧቸው ነበር። ይህንን በጠማማና በቀጥተኛ ዛፎች መካከል ያለውን ቅራኔ የቅዥርት ሰዎች በዘረጉት የስለላ መረባቸው አጠኑ። በጥናታቸውም የዕልም አገር ሳትደፈር የኖረችው በዛፎች ትብብር፣ በተለይም ደግሞ በቀጥተኛ ዛፎች ቀጥ ያለ አቋቋም፣ አስፈሪነትና ግርማ ሞገስ መሆኑን ተገነዘቡ።

በዚህ ግንዛቤም ጠማሞችን ከቀጥተኞች አጣልተው፣ ጠማማዎቹን ከጎናቸው የሚያሰልፉበትንና ቀጥተኞችን የሚያጠፉበትን ሰነድ አረቀቁ። “ቀጥ ያሉ ዛፎች እናንተን ጠማሞችን እንኳን እንደ ዛፍ እንደ ደን አካልም አይቆጥሯችሁም፣ እንደ ደን አካል ስለማይቆጥሯችሁም አፈሩን፣ አየሩንና ፀሐዩንም ተቆጣጥረው በአካል እንድትጣመሙና እንድትቀጭጩ አደረጉ፣ በዚህም ምክንያት ዐይን ለዐይን ሳይሆን ቁልቁል እያዩአችሁ ይኖራሉ፡፡ መንፈሳችሁንም እንደ ጥጥ አሳስተውና በራስ የመተማመን ሥነ-ልቡናችሁን እንደ ሙክት ፍሬ ሰልበው እንደ ኩምቢ አቀርቅራችሁ ምድርን ብቻ ስታዩ እንድትኖሩ አስገደዷችሁ” እያሉ ያለመታከት ሰበኳቸው።

የቅዠት ሰዎችን ስብከት የሰሙ እድሜ ጠገብ ጠማማ ዛፎች “ይህንን ዛፍን እርስ በርሱ የሚያጋጭ መሰሪ የባዕድ ስብከት አትስሙ! ቀጥተኛ ዛፎች የበለጠ የቅዠት ሰዎች ዘመድና ወዳጅ ሊሆኑን አይችሉም፣ በመካከላችን ያለውን ችግር ራሳችን እንፈታዋለን” ብለው ለግላጋ ዛፎችን እያስተማሩ ለብዙ ዓመታት የቅዠትን ሰዎች ተንኮል አከሸፉ። ዳሩ ግን ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ የቅዠት ሰዎች ያላሰለሰ ስብከት የጠማማ ዛፎችን ልብ እንደ ልጃገረድ ማሽኮርመምና ማማለል ቻሉ። አሽኮርማሚዎቹ የቅዠት ሰዎች “ከጠማማ ዛፎች የምንፈልገው ትንሽ እርዳታ ነው። ከጎበጡት ቅርንጫፎቻችሁ የተወሰኑትን ብትለግሱን ቀጥ ያሉ ዛፎችን አጥፍተን የዕልምን ምድር የጠማማ ዛፎች ምድር እናደርጋታለን፣ ሥሚንም ከዕልም ዛፎች አገር ወደ ጠማማ ዛፎች አገር እንቀይረዋለን” ብለው ሲሰብኳቸው ጠማሞች ቀጥ ያሉ ዛፎች እንደ ዳይኖሰር ጠፍተው የዕልም ምድር በጠማማ ዛፎች ስትሸፈንና ሥሚም የጠማማ ዛፎች አገር ሲሆን ታያቸውና ጎባጣ ቅርንጫፎቻቸውን ለቅዠት ሰዎች ለማበርከት እንደ አዲስ አባባ የስኳርና የዘይት ሰልፈኞች ተራ ለማያዝ ተሽቀዳደሙ። ይኸንን የጠማማ ዛፎች እሽቅድድም የተመለከቱ የቅዠት ሰዎችም ከጎባጣ ቅርንጫፎች የሚጠርቡትን እጀታ ከምሳር አጋብተው የዕልም ዛፎችን ሲከተክቱ፣ በዚህ ክትከታ ምክንያትም ቀጥተኛና ጠማማ ዛፎች ተጣልተው እርስ በርሳቸው ሲተላለቁ፣ በዚህ የመተላለቅ ግርግርም የደኑ አውሬዎች ደንብረው ሲጠፉና አውሬዎች ሲጠፉም የዕልምን ምድር እንደልባቸው ሲጠቀሙ ታያቸውና ተደሰቱ።

የቅዠት ሰዎች ጎባጣ ቅርንጫፎችን ከጠማማ ዛፎች ተረከቡና “የተደበቀው ውበታችሁ ሰዎች ለጠማማ ዛፎች ክብር ያላቸው፣ ለፍትህ የቆሙና ጠማማ ዛፎችን ከቀጥተኛ ዛፎች ጭቆና ለማላቀቅ ከሰማይ የወረዱ መላእክት” አሉና ሰገዱላቸው።

የቅዠት ሰዎች በጠማማ ዛፎች መሪነት ከእጀታ በተሰካ ምሳር ቀጥ ያሉ ዛፎችን እየገነደሱ የመርካቶ ዘራፊ ጂዶ እንደመታው ነጋዴ መዘንደብ ሲጀምሩ በዕልም ምድር ድንጋጤና ውዥምበር ተፈጠረ። ውዥንብሩ እየጠራ ሲሄድ ዛፎች በተናጥል በአልሞት ባይ ተጋዳይነት ከቅዠት ሰዎች እየወደቁ ወገባቸውን ሰበሩ፣ ከፊሎቹም የምሳርን ጥርስ አዶለዶሙ፣ ሌሎችም እጀታዎችን እየታገሉ ሰንበር በሰንበር አደረጉ። …በዚህ ትንቅንቅ ልባቸው እንደ ቅቤ የቀለጡና ውሀ ሲመጡና ኦክሲጂን ሲፀዳዱ ኖረው አፈር ለመሆን የወሰኑ መሐል ሰፋሪ ዛፎች ደሞ “ጊዜ እስኪያልፍ ያባትህ ባርያ ይግዛህ!” በሚል የጡርቂዎች ፈሊጥ ከጠማማ ዛፎች ተመሳስለው መከራን ለማለፍ ማንነታቸውን ለመቀየር መጉበጥ ጀመሩ፣ በአደባባይ ቀጥተኛ ዛፎች እንደሆኑ ለመናገር ተቸገሩ።

ከብዙ እልቂት በኋላ ቀጥተኛ ዛፎች በምስጢር ተሰባሰቡና “በምን ምክንያት ለእልቂት በቃን፣ ማንስ ፈጀን? እንዴትስ ራሳችንን መከላከል አቃተን” እያሉ መወያየት ጀመሩ፣ ከፊሎቹ “ያስፈጁን ከራሳችን የወጡ ጠማማ ዛፎች

**…ወንድሞችህን በጎባጣ እንጨት፣ በምሳርና በቅዠት ሰዎች አስፈጅተህ አንተ በሰላም ልትኖር ታስባለህ.. በወንድሞችህ መቃብር የሰላም ሐውልት ልትገነባ ታቅዳለህ፤ ሆዳም! ስንት ዘመን ለመኖር ይኸንን ያህል ለከርስህ ትገዛለህ? ወንድሙን በክህደት የሚያስበላ ከፈጣሪ፣ ከፍትህና ከታሪክ የተጣላ እርጉም ነው!”…**

እንዲወጣና እንድታምሩ ጠርበን ቅቤ እንቀባችሁ” በሚል ማታለያ እየጠረቡና ቅቤ እየቀቡ እጀታ ሰሯቸው፣ እጀታ ከሰሯቸው በኋላም “የበለጠ ለማስጌጥና ዘመናዊ ለማድረግ” በሚል መሸንገያ ምሳሮችን እንደ ሎቲ ሰኩባቸው። እጀታዎች ምሳሮች እንደ ሎቲ ሲሰኩባቸው ከዛፎች ባህል እጅግ ራቁና እንደ አካላቸው ሁሉ የመንፈስ ጉብጥናም ተጠናወታቸው፣ የመንፈስ ጉብጥና ስለ ተጠናወታቸውም የሚያብረቀርቁትን የምሳር ሎቲዎች ስላንጠለጠሉ ከጥንታዊ ዛፍነት ወደ ዘመናዊ ብረትነት የተቀየሩ መሰላቸው። የቅዠት ሰዎች ዛፎችን ለመቁረጥ ሲሄዱ በትከሻቸው ሲሸከሟቸው ያከበሯቸው መሰላቸው።… እንደ እጀታዎች ጠማማ ዛፎችም እጀታዎችን ከቅዠት ሰዎች ትከሻ ሲመለከቱ “እውነትም የቅዠት ናቸው!” እያሉ ሲቆጩ ከፊሎቹ ደግሞ “አህያውን ቢፈራ ዳውላውን! እኛን የፈጁን የቅዠት ሰዎች ጠፍጥፈው የሰሯቸው ምሳሮች ናቸው!” እያሉ ተከራከሩ። የቀሩትም “ቀንደኛ ጠላቶቻችን የቅዠት ሰዎች ናቸው!” ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጡ። በእንደዚህ ዓይነቱ ጉንጭ አልፋ ክርክር ቀጥ ያሉ ዛፎች መግባባት ስላልቻሉ ግጭት ተፈጠረና በአንድነት መቆም ተሳናቸው። ይኸንን የቀጥተኛ ዛፎችን የአቋም መፈረካከስ የተመለከቱ ጠማማ ዛፎችም “ቀጥ ብለው መሄድ የማይችሉ ጠማሞች እያሉ ሲተርቱብንና ሲሰድቡን ኖረው ዛሬ እነሱ ቀጥ ብሎ መሄድ አቃታቸው። እንደ ወልካፋ እየተወላከፉና እንደማገር እየተወናገሩ ገመናቸውን ማሳየት ጀመሩ ኪ…ኪኪ…ኪኪኪ…” እያሉ ሳቁ፣ተሳለቁ።

የቅዝርት ሰዎችም ይህንን የዛፎችን ትርምስና ብጥብጥ ተጠቅመው አንበሶችና ነብሮችን አቅፈው በመያዝ የዕልምን ምድር አስከብረዋት የኖሩት ዛሬ ቀን ጥሏቸው በአንድነት መቆም ያቃታቸውን ዛፎች መጨፍጨፉን ቀጠሉ፡፡ የሚጨፈጨፉት ዛፎችም "እኔ አለቃ ልሁን፤ እኔ ልምራ" በሚሉ ፉክክሮችና "ጊዜ ያመጣውን ጊዜ ይመልሰዋል" በሚል አጉል ተስፋ ተተብትበው በተናጠል ማለቁን ቀጠሉ፡፡ አንዱ ቡድን "የኔ ትግል ስልት ፍፁም ነው!" ሲልና ሌላው የዚህን ቡድን ሥልት አጣጥሎ የራሱን ሥልት ፍፁምነት ሲሰብክ ብዙ የዛፍ ልጆች ተጨፈጨፉ፡፡ አንዱ ዛፍ ከሩቅ ተገንድሶ ሲወድቅ ሌላው "ከእኔ እስኪደርሱ አምላክ መፍትሔ ያመጣል" ሌላውም "እኔን እስኪያገኙኝ አንበሶችና ነብሮች የቅዝርትን ሰዎች ይለቅሟቸዋል" እያለ እንደ ፀጋዬ ገብረመድህን ቀዌሳ የማይነጋ ህልም ሲያልም በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ዛፎች አለቁ፡፡ በዛፍ ቡድኖች አለመግባባት፣ በመሐል ሰፋሪው ብዛትና ራስን የመከላከል ድክመት የዕልም ምድር እንደ በደኖ ገደልና እንደ ጋንቤላ ሜዳ በሬሳ ተሸፈነች፡፡ ሌላው ቀርቶ አንዳንድ እጀታዎችም በጭፍጨፋው ብዛት አንገቶቻቸው እየተቀሉ ከምድጃ ተማገዱ፡፡ አያሌ ምሳሮችም ጥርሳቸው ረግፎ አዷማ እየተሰሩ አፈር መብላት ጀመሩ፡፡

አንገቶቻቸው የተቀሉ እጀታዎች ከእሳት መጣላቸውን የሰሙ ጠማማ ዛፎች "አገልግሎታችን ሲያልቅ መጨረሻችን ገሀነመ እሳት መሆኑን መች አወቅን" እያሉ ማጉረምረም ጀመሩ፡፡ የቅዝርት ሰዎች ግን "አንድም እጀታ ከእሳት አልተጣለም!" ሲሉ ሙልጭ አርገው ካዱ፡፡ በቅዝርት ሰዎች አጭበርባሪነት፣ አረመኔነትና በጠማማ ዛፎች ክህደት የበገኑ ቀጥተኛ ዛፎች የአልሞት ባይ ተጋዳይ ተጋድሎ ቀጠሉ፡፡ እንደ ዋንዛ ያሉ ጠንካራ ዛፎች የእጀታን ጭንቅላት መተርከክና አንገቱን መቅላት ጀመሩ፡፡ እንደ ቁጥቋጦ ያሉ ዘዴኛ ዛፎችም ድንጋዮችን በቅጠሎቻቸው ሸፍነው ካጠገባቸው የበቀለን ቀጥ ያለ ዛፍ የሚጨፈጭፍ ምሳር ጥርስ መሰባበር ጀመሩ፡፡ እንደ አጋምና ቀጋ ያሉ ተናዳፊዎችም የቅዝርት ሰዎችን ቆዳ በመገሽለጥና አይናቸውን በማፍሰስ ታገሉ፤ዳሩ ግን እነዚህ ዛፎች የሚያደርጉት ተጋድሎ የተናጥል ስለነበር አንዱ እጀታ ሲቀጭ ሌላው እየተተካ፣ አንዱ ምሳር ጥርሱ ሲረግፍ ሌላው ጥርሳም እየተተካ፣ አንዱ የቅዝርት ሰው ዓይኑ ሲፈስ ሌላው ስስታም ዓይኑን ይዞ ከች እያለ ዛፎች ለድል አልበቃ አሉ፡፡

ለድል አልበቃ ያሉበትን ምክንያት ለመመርመርና የትግል ስልት ለመቀየስ አስተዋይ ዛፎች መጀመርያ ምስጢራዊ ውይይት አደረጉና ቀጥለው ጠቅላላ ስብሰባ ጠሩ፡፡ በስብሰባው ወቅትም የተለመደው ጭቅጭቅ ተጀመረ፡፡ ሰብሳቢው ሾላ "አለም ከተፈጠረች ጀምሮ ታፍረንና ተከብረን ተኖርንበት ምድር እንዴት ልንጨፈጨፍ ቻልን?" ብሎ ጥያቄውን ሳይጨርስ .."ምን ጥያቄ አለው! ያስጨፈጨፈን የራሳችን ጠማማ ነው?" አለ ዋንዛ በንዴት!.. የተናደደውን ዋንዛ የጎሪጥ እያዬ ኮባ የተባለው ተክል "አህያውን ቢፈራ ዳውላውን! የቅዝርት ሰዎች እኛን እንዲያጠፋ የጠፈጠፉት ምሳር ተቀምጦ የራሱን ወገን ይወቅሳል" አለ፡፡ ..ዋንዛም ኮባን በንቀት እያዬ "ተናግረህ ሞተኻል! ጥርሳሙ ምሳር ወገን ከምትለው ጠማማ ዛፍ ወሲብ ባይፈጽም አቅሙን ከየት ያመጣው ነበር! " ሲል ወጠረ፤ "አቅሙን የሚያገኘውማ ከጠማማው ዛፍ ሳይሆን ከቅዝርት ሰዎች ነው" አለ ኮባን የደገፈው እንሰት፤ በኮባና በእንሰት ክርክር ያልረካው የስብሰባው መሪ ሾላ "ኮባና እንሰት የምታስቡት በቅጠላችሁ ይመስለኛል! የእኛው ጠማማ የቅዝርት ሰዎችን እጆችና የምሳርን ቀለበቶች ባያገናኝ የቅዝርት ሰው አቅም በምን ታምር ወደ ምሳር ተላልፎ ምሳር እኛን እንዲከትፍ ያበቃው ነበር?" እያለ እንደ ፊዚክስ ሳይንቲስት ጉልበት ወይም ኃይልን ከአንዱ ቁስ ወደ ሌላው የመፍሰስን ሂደት አስረዳ፡፡ ..ይህ የጉልበት ወይም ኃይል ፍሰት አገላለጽ ቀለም በደም ሥርም ሆነ በአፍ ቢሰጣቸው ከማይገባቸው እንደ ብሳና ካሉት ዛፎች በቀር ሁሉንም ቀጥ ያሉ ዛፎችን ልቦና አረካ፡፡ .. ልቦናቸው በመርካቱም የጠማማ እንጨት ክህደትና አስፈጅነት እንደ መስተዋት ቁልጭ ብሎ ታያቸውና ቅርንጫፎቻቸውን እያፋጩ "ጠማማ ይሰበር! ባንዳ ይቀልጠም! ከሀዲ ይቃጠል!" እያሉ መፈክር አሰሙ፡፡

በጠማማ ዛፍ ክህደት፣ አስፈጅነትና ቀንደኛ ጠላትነት በተደረሰው ስምምነት ያልተደሰተ የገዴ ማደርያ ዛፍ "ጦርነት ውስጥ ከምንገባ የተወሰነውን የዕልም ክፍል አስረክበን በእርቅ ብንፈታውና ሰላም ቢሰፍን ይሻላል" ብሎ ሳይጨርስ "አንተን ብሎ ገዴ! ገድህ ይጥፋ! የምታስረክበው አካባቢ ያሉት ዛፎች ወንድሞችህ አይደሉም? ወንድሞችህን በጎባጣ እንጨት፣ በምሳርና በቅዝርት ሰዎች አስፈጅተህ አንተ በሰላም ልትኖር ታስባለህ.. በወንድሞችህ መቃብር የሰላም ሐውልት ልትገነባ ታቅዳለህ፤ ሆዳም! ስንት ዘመን ለመኖር ይኸንን ያህል ለከርስህ ትገዛለህ? ወንድሙን በክህደት የሚያስበላ ከፈጣሪ፣ ከፍትህና ከታሪክ የተጣላ እርጉም ነው!" አለ ዋንዛ ቅርፊቱ በላብ ወርዝቶ፤... በዋንዛ አቋም የረካው ዘንባባ "አንዱ በይ ሌላው ተበይ ሆኖ ሰላም የለም!" ብሎ ለዋንዛ ያለውን ድጋፍ ተናግሮ ሳይጨርስ

> **የቅዝርት ሰዎች የስለላ መረብ በይበልጥ የተዘረጋው ከጠማማ ዛፎች ዙሪያ ነበር፡፡ ጠማማ ዛፎች ቀጥ ብለው መውጣትና መቆም ስለማይችሉ፤ ቀጥ ያሉት ዛፎች "ጎባጦች፣ አጎብዳጆችና አጎንባሾች" እያሉ ይንቋቸው ነበር**

በዘንባባ ንግግር የተገረመው በለስ "አንተም ዘንባባ... አንተም ሰላምን በመስበክ ፋንታ ለጦርነት ድጋፍ ሰጠህ?... ስምንተኛው ሺ የደረሰ መሰለኝ.. የሰላም ምልክትነትህ የት ደረሰ?" አለ፡፡ ..ዘንባባም በለስን ቁልቁል በትዝብት እያዬ "ዕፀ- በለስ! እንደ ልማድህ ለማሳሳት ታልሆነ ያልኩትን አጥተኸው አይመስለኝም፤ ቀበሮ በግ መብላቱን ታላቆመ፤ ዓለም ከተፈጠረች ጀምሮ ለበላው በግ ካሳ ካልከፈለና ንሰሐ ካልገባ፤ በግን ከቀበሮ ተስማማና ሰላም ፍጠር ብትለው እንዴት ሊሰማህ ይችላል? ...የምታውቀው እባብ ሲውጥህ እግርህን ዘረጋግተህ ስጠው የሚል ቃል ከየትኛው መፅሀፍ ተፅፏል?..፣ ሰይጣን ቀኝ ፊትህን ሲመታህ ግራህን ስጠው የሚል ትዕዛዝስ የትኛው አምላክ አስተላልፏል?" በሚሉ ጥያቄዎች አፋጠጠው፡፡

በዚህ ጠንከር ያለ ክርክር ግራ የተጋባው ብሳና "አምላክ ሆይ! ደብቀን የያዝናቸውን አንበሶችና ነብሮች አስነስተህ የቅዝርትን ሰዎች አጥፍተህ እኛንም እርስ በራሳችን ተመናክስ አድነህ በሰላም አኑረን" ብሎ ወዝቦ እንደ ገፋው ቅርንጫፎቹን ዘቅዝቆ ለእግዞታ ከምድር ተደፋ፡፡ ብሳናን ለእግዞታ ሲደፋ ያየው ዋንዛ "ድፍት ያርግህ ብስናታም! አንበሳ ነፃ ያውጣን እያልክ ነጋ ጠባ ትደፋለህ! ዛፍን ነፃ ማውጣት ያለበት ራሱ ዛፍ ነው! በሞግዚት ነፃነቱን ያገኘ ፍጡር ባለም የለም! በሞግዚት ነፃ አውጣኝ ብትለውም እግዜር አይረዳህም! ሲያምርህ ይቅር!" ሲል ተቆጣ፡፡ ዋርካ ስብሰባው ወደ መፍትሔ ሳይሆን ወደ ቡድን ውዝግብ መሄዱን ተረዳና ‹‹ጎበዝ.. ወደ ቁም ነገሩ እንግባ! ለመሆኑ ከፊታችን የተደቀነብን ትግል የመኖርና ያለመኖር የህልውና ትግል መሆኑን ስንቶቻችን ተረድተናል? ... የህልውናችን ትግል ከዳር እሚደርሰው በተግባር የሚተረጎም የረቀቀ የጋራ የትግልና ስልት ሲኖር ብቻ ነው፡፡ ይህ የጋራ የትግል ሥልትም የሚተለመው ሁላችንም የየራሳችን ተሰጥኦና ሙያ ማበርከት ስንችል ነው፡፡ የጥፋት አዋጅ ታውጆብን መንተቱና መጋጨቱ መጥፋታችንን ያፋጥናል እንጅ መፍትሔ አይሆንም›› በማለት ሀሳቡን አስቀመጠ፡፡

በውይይቱ ቅርፅ መያዝ የተደሰቱ አንድ የእጣን ሊቀ ጠበብት "እሽዋ...እሽዋ.." እያሰኙ እንደ እጣን ማጨሻ ቅርንጫፎቹን እርግፍ እርግፍ አርጎ አካባቢውን አጠነና "አንድም ሁለትም ሆናችሁ ተገኙ፤በመካከላችሁ እገኛለሁ ብሏል" ብለው ንግግራቸውን ጀመሩ፤ በመቀጠልም "እንደዚህ ዓይነት የመደማመጥና የመረዳዳት መንፈስ በመካከላችን ሲፈጠርና እኛም ስንረዳው እርሱም ይረዳናል፤ ፈጣሪ ግፈኞችን ያንበረክካልና እኛም ስንጥርና ስንረዳው ሳንደርስባቸው የደረሱብንን የቅዝርት ሰዎች ያንበረክክልናል፡፡.. ስናጎርሳቸው የነከሱንን ጠላቶች ያመነዥክልናል፤ እኛን ለማጥፋት የተጠፈጠፈውን የምሳርን ጥርስ ይሰርብርናል፤ የከሀዲዎችን ክንድም ያዝልልናል፡፡ በእነኚህ መረን በለቀቁ አረመኔዎችም አንበሶችና ነብሮችን ሊለቅባቸው ይችላል፤ ሳንሄድባቸው ለመጡብን፣ ሳንነካቸው ለነኩን፣ ሳንወስድባቸው ለወሰዱብን፣ ባበላናቸው ላስታወኩብንና ባጠጣናቸው ለሸኑብን ማዕበልና ጎርፍ ሊያወርድ ይችላል..." ብለው ሀላፊነትን ሲወስዱ ጭብጨባው ቀለጠ፡፡

ተረኛው አባ እጣን የተጨማደደ ቅርፊታቸውን እንደ ካባ ደርበው አስተያየታቸውን ቀጠሉ ‹‹..እግዚአብሔር ሁለት ልብ አይፈልግም፤ ለእግዚአብሔርና ለሳጥናኤል መገዛት አይቻልም፤ እግዚአብሔርና ሳጥናኤል ዘወትር ጦርነት ላይ ናቸው፡፡ የጦርነት ሜዳቸውም የሰው ልብ ነው፡፡ ሰው ልቡን ለሳጥናኤል ሰጥቶ እየካደ፣ የሰውን ሐብት እየተመኘ፣ እየሰረቀ፣ እየተስገበገበ፣ እርስ በርስ እያጋጨ፣ እያመነዘረ፣ እየመቀነ፣ እየገደለና እያሰቃየ እጁን ለፈጣሪ ቢዘረጋ ከየትኛው ሰማይ እሚኖር እግዚአብሔር ይሰማዋል?... በዘረፈውና አጭበርብሮ ባካበተው ገንዘብ የአምልኮት ሥፍራ ቢሰራ የትኛውን አምላክ ሊያታልል ይችላል? አምላክ ቀናተኛ መሆኑን አበክሮ ነግሮናል፤ ከእርሱ በቀር ሳጥናኤልንም ሆነ የሳጥናኤልን ጣኦቶች ገንዘብና ስልጣንን እንዳናመልክ አስጠንቅቆናል፤ ስለዚህ ሙሉ ልባችንን ለእግዚአብሔር ሰጥተን፤ ትስስራችን አጠንክረን፣ በሙያችን ተሰልፈን፤ ከሀዲና ባንዳን ከጉያችን እንደ መዥገር ነቅለን ለፍትህና ለነፃነት ከታገልን እግዚአብሔርም እንደ ዛሬው አብሮን በውይይታችን መሀል ይቆማል... ከማመንታትና ሁለት ልብ ከመሆን አውጥቶ ለድል ያበቃን እግዚአብሔር ይመስገን፤ እርስ በርሳችን አጋጭቶ ሊያጠፋን ከሚነሳ ጠላት ይጠብቀን፤ የሰማእታትን ነፍስ ይማር" ብለው ንግግራቸውን ሲጨርሱ ሁሉም ዛፎች "አሜን፤ አሜን፤ አሜን፡፡" እያሉና የተጨፈጨፉት ወገኖቻቸውን እያሰቡ በቅርንጫፎቻቸው ተቃቅፈው እንባቸውን ከቅጠሎቻቸው እንደ ነሐሴ ዝናብ አወረዱ፡፡

# ‹‹ከመጋረጃ ጀርባ››

## አንድነትን የሰበከልን ቴአትር



ፍቃዱ ልመንህ

የቴአትሩ ርዕስ፡- ‹‹ከመጋረጃ ጀርባ››
ደራሲ፡- ቶፊቅ ኑሪ
አዘጋጅ፡- ዳግማዊ አመለወርቅ ፈይሳ
ተዋንያን፡- ይገረም ደጀኔ (አስቴር)፣ ፍቃዱ ከበደ፣ ሳጅን መኮንን ንጉሴ፣ አንዱዓለም ደጀኔ (አባቡ)፣ እየሩሳሌም ኃ/እየሱስ፣ ብሩክ ምናሴ እና ፅዮን ዳኛቸው
ዝግጅት አስተባባሪ፡- ሚካኤል ሕፃነወልድ
ረዳት አዘጋጅ፡- መሠረት ኃይሌ
የመድረክ ገፅ ፕሮዳክሽን እና ዝግጅት፡- ለማ ፀደቀ፣ በላይ ኪዳኔ እና ዘውዱ ገ/ማርያም
የመብራት ስርጭት፡- ወርቁ ታምራት
ሜካፕ፡- ምስራቅ ለገሰ
የድምፅ ስርጭት፡- ሬዲዋን አወል እና አምሳሉ ጌታቸው
አልባሳትና ቁሳቁስ፡- የትምወርቅ በቃሉ እና አሰለፈች እንግዳ
መድረክ ዲዛይን፡- በላይ ኪዳኔ
የድምፅ ግብዓት፡- ሬድዋን አወል
የሚታይበት ቦታ፡- ሀገር ፍቅር ቴአትር
የሚታይበት ቀንና ሰዓት፡- እሁድ ከ8:00 ሰዓት ጀምሮ




### መግቢያ - መግባቢያ

ሂስ እና መስታወት ሥራቸው ተመሳሳይ ነው። ቆንጆውንም ሆነ ጉድፉን ማሳየት። መስታወት ለምን ጉድፉን አሳየኸኝ? ተብሎ እንደማይሰበረው ሁሉ ሂስ ለምን ተሰጠ ተብሎ ማኩረፍ አይገባም።

ብዙዎቹ የሀገራችን የጥበብ ባለሙያዎች ሥራቸው ላይ ሂስ ሲሰጥ ለምን ተነካን የማለት አባዜ አለባቸው። ሂስ በትክክል የሚሰጥ ከሆነ ያሳድጋል።

ለማንኛውም ሂስ ወደ መስጠቱ ሥራዬ ተመልሻለሁ። ፈተና የሆነብኝ ግን ጥሩ ሐሳብ ባነሳውና አብዛኛው ተመልካችን ባስደሰተው ቴአትር መጀመሬ ነው። ይህንን ቴአትር ያላዩት እንዲያዩት እየጋበዝኩኝ የላሉ ብሎኖቹን እንዲያጠብቅ ጥቆማ እሰጣለሁ።

### የቴአትሩን ታሪክ ለማስታወስ

‹‹ከመጋረጃ ጀርባ›› የተሰኘው ቴአትር በውስጡ ‹‹እቴሜቴ›› የተሰኘ ሌላ ቴአትር መድረክ ላይ ለማቅረብ የሚደረግን ውጣ ውረድ ያሳያል። በቴአትሩ በርካታ ልጆች የወለደችው እናት ባሎቿ ያስቸገሯትን ያህል የልጆቿ አለመስማማትም በሽታ ላይ እንደጣላት እናስተውላለን። ልጆቹ እናታቸውን ለማዳን የሚያደርጉትን ግብግብ ለ2:45 ሰዓት መድረክ ላይ እንመለከታለን።

### ስለ ቴአትሩ አሠራር ጥቂት መረጃ

ይህ ቴአትር 2005 ዓ.ም ላይ በቴአትር ቤቱ ተገምግሞ አልፎ ሆኖም መድረክ ላይ ለመውጣት ከአራት ዓመት በላይ የፈጀ ነው። የመጀመሪያው አዘጋጅ ዶ/ር ተሻለ አሰፋ የተዋንያን ሥነ-ምግባር አማሮት ጥናት አስጠንቶ የመድረክ ልምምድ እንደ ጀመረ አቋረጠው። ከይገረም ደጀኔ እና ከፍቃዱ ከበደ ውጭ በርካታ ተዋንያን የተፈራረቁበት ይህ ቴአትር ብዙዎቹ ተዋንያን የሥነ-ምግባር ችግር የነበረባቸው ስለነበሩ ሰዓት አክብሮ ከመገኘት ጀምሮ ሌሎችም የራሳቸው ችግሮች ተደራርቦበት ቴአትሩ ቀድሞ ለመድረክ እንዳይበቃ አድርጎታል። በእርግጥም ሥነ-ምግባር የሌለው ተዋናይ ኢትዮጵያዊነትን የሚሰብከውን ቴአትር መሥራት አይገባውም። እነዛ አስቸጋሪዎቹ ተዋንያን አንድነት ሳይኖራቸው ስለአንድነት የሚሰብከውን ቴአትር አለመሥራታቸው ለበጎ ነው ያሰኛል። በዚሁ አጋጣሚ ፍቃዱና ይገረምን ስለ ሥነ-ምግባራቸው ሳላደንቅ አላልፍም።

### ከቴአትሩ መልካም ጎኖች መካከል...

‹‹ከመጋረጃ ጀርባ›› በቴአትር ቤቱ ታሪክ ከ‹‹የቀለጠው መንደር›› እና ከ‹‹ፍሬሽ ማን›› ቴአትር ቀጥሎ ተመልካችን እያጋፋ 8:00 ሰዓት ለሚጀምረው ከ6:00 ሰዓት ጀምሮ እያሰለፈ

የሚገኝ ቴአትር ነው፡፡ ቴአትሩ የሚያነሳው ሐሳብ ተመልካቹን ያስደሰተ፣ ያሳቀ፣ ያስለቀሰ ነው፡፡ የኢትዮጵያ መገለጫዎችንና ምኞታችንን በመድረክ ያሳየ፣ ምናለ ቴአትሩ እንደሚለው በኖርን የሚያስብል፤ በአንድም በሌላም አንድነትን የሚሰብክ፣ ድርሰቱና ዝግጅቱ የተዋሃደ ቴአትር ነው፡፡

ቴአትሩ የሰውን የልብ ትርታ ያዳመጠ፣ በጭብጨባ የታጀበ፣ በዚህ ወቅት ስልጣን ላይ ከሚገኙት ባለስልጣናት ጀምሮ ብዙዎች ሊያዩት የሚገባ ነው፡፡

የሃይማኖትን እና የብሔርን ጉዳይ በድፍረት አንስቶ ለመድረክ በማብቃቱ ደራሲውን፣ አዘጋጁን፣ ተዋንያኑን፣ ሌሎች ባለሙያዎችንና ቴአትር ቤቱን ሳላመሰግን አላልፍም፡፡ የልባችንንና የምንፈልገውን በቴአትሩ ላይ እንዳየነው ሁሉ፤ አንድነታችንን በእውነተኛ ሕይወታችንም ተግብረነው ለማየት ያብቃን!

በሁለት ገቢርና በሰባት ትዕይንት የተቀነበበው ‹‹ከመጋረጃ ጀርባ›› ቴአትር፤ የትዕይንት መሸጋገሪያዎቹ ገላጮች ናቸው፡፡ ለቴአትሩ ሲባል አዲስ መሸጋገሪያዎች ቢሠሩለት ደግሞ የበለጠ ያምር ነበር፡፡

ቴአትሩ የኢንፕሮቫይዜሽንን ጥቅም አጉልቶ ያሳየን ሲሆን ተዋንያን ተፅፎ የተሰጣቸውን ብቻ ሳይሆን ሐሳቡን ተረድተው ታሪኩን ማሳመር እንደሚገባቸው ጥቆማ የሰጠ ነው፡፡ ስለዚህ አንዳንድ ተዋንያን የሚሆነው አይታወቅምና ከመድረክ ጀርባም መብሰል እንደሚኖርባችሁ ልብ ይሏል፡፡ በመጨረሻ ትዕይንት ጀምሮ በፈጠራው የመጨረሻ ትዕይንት የሚያበቃበት መንገድም አዲስ ቅርፅ ነው፡፡

ቴአትሪ እጅ ለእጅ መያያዙን፣ ማንነታችንን የሚያሳየውን ቡናውን፣ ቂጠማውን፣ ልብሱን፣ ሞሰቡን፣ ጉርሻውን፣ መከባበሩን… ኢትዮጵያዊነታችንን የሚገልፅልንን ድርጊት መድረክ ላይ አሳይቶናል፡፡ ለዚህም አድናቆቴ ከፍ ያለ ነው፡፡ ቴአትሩ ደግመው ሲያዩት የበለጠ ውበቱ ይጨምራልና ያላያችሁት እንድታዩት፣ ያያችሁት ደግሞ እንድትደግሙት እየጋበዝኩ ቴአትሩን ላዩትና በሙያው ውስጥ ለሚገኙት ትምህርት ይሆን ዘንድ ሂሳዊ ዳሰሳየን እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡፡

## የላሉ ብሎኖችን ለማጥበቅ ወይንም እስፓናቶ የሆኑትን ለመቀየር የሚጠቅሙ ነጥቦች

ቴአትሩ የተደከመበትን ያህል በቸልታ የታለፉ ጉዳዮች እንዳሉት ተገንዝቤያለሁ፡፡ የዐምድ ጥበት ስላለ በተሰጠኝ ልክ ነጥብ ነጥቡን ለማንሳት እሞክራለሁ፡፡

ሙዲ ሽረፋ ዶክተሩን ሲተዋወቀው የሚያሳየው እንቅስቃሴ ሳቅ ፍለጋ መሆኑ ያሳብቃል፡፡ ‹‹ሰብሰብ በሉ›› የምትለዋ አዝማች ቃል ለትዕይንት አንድ ብቻ ሁና መቅረቷ የገፀ-ባሕሪያት ወጥነት ችግር እንዳለ ያሳያል፡፡ ለምሳሌ ደምለው በትምህርት እንዳልዘለቀ እየታወቀ ‹‹ሳታምን ነው አሥር ጊዜ ጂሰስ የምትል›› ሲል እንሰማዋለን፡፡ ‹‹አማርኛውን አሳለጠው ኮ›› ሲልማ ይሄን ዘመን አመጣሽ ቃል እርሱ ሊለው እንደማይችል ስለሚገባን ቃላቶች በየባሕሪያቸው የመሰካካት ችግር እንዳለ ያመላክታል፡፡

የተለመዱ አባባሎች ለደምለው መወከላቸው ቅሬታ ባያስነሳም፤ ሙዲ ሽረፋ ተረት ጀምሮ ‹‹አለ ደምለው›› የሚለው አባባል ግን ‹‹አሉ እነ ደምለው›› በሚል ቢቀየር ጥሩ ነው፡፡ ሙዲ ሽረፋ ‹‹ጉራጊኛ ትችያለሽ›› ከማለቱ በፊት ጉራጌኛ አውርቶ ቢያፋጥጣት የተሻለ ይሆናል፡፡ በዚሁ አጋጣሚ ለሞክሼዬ ምላሱን የሚያወጣውና ቃላቶችን አስረዝሞ ለሳቅ የሚያመቻቸው ነገር ‹‹ቀርቶብሃላ›› ዓይነቱ ከሌሎች ቴአትሮቹ ጋር እያመሳሰለበት እንደሆነ ንገሩት፡፡ በእርግጥ በሳምንት ውስጥ በተለያዩ ቴአትር ቤቶች የተለያዩ ገፀ-ባሕርያትን ተላብሶ ስለሚተውን አለመምታታቱ ያስደንቀዋልና የቀደመውን አስተያየት እንዝለለው፡፡

ደራሲው ለገጸ-ባሕሪያቱ ስም ሲያወጣላቸው ትርጉም እንዲኖረው ቢያደርግ አክብሮታችን የበለጠ ይሆን ነበር፡፡ የአዘጋጇን ስም ትንሳኤ ማለቱ ጥቁምታ ስለሚሰጥ የእርሷን በበጎነት እይዘዋለሁ፡፡ ታዬ ንዋይስ? ብትሉኝ ሥነ-ምግባሩን በትክክል አይገልፀውም እላችኋለሁ፡፡

> **…የሙላቱ ምሰጣ መጋነኑን ብናልፈው እንኳን ሙዲ ሽረፋ ለተመልካች በቀጥታ የሚናገረውን ቢያቆመው ጥሩ ነው፡፡ ቴአትሩ በሆነ ባልሆነው ከተመልካች ጋር የሚፋጠጠው ነገር በዝቷል፡ ፡ ይሄም ቁም ነገር አለው በሚል ወደ ተመልካች እየመጡ ተናግሮ መሄድ ሲበዛ ያስተቻል…**

ዶክተሩ ‹‹ውጤቱን አሜሪካ እንልካለን›› ይላል፤ በቅፅበት ደግሞ ሜሪ ስታሳስበው ውጤቱን ለመናገር ይሞክራል፡፡ ይህ አድራጎት ቴአትሩን የቴአትር ቤት ድራማ ሳይሆን የኬጂ ድራማ ያስመስለዋል፡፡ ስንት ታዛቢ ባለበት ሀገር በግድ እመኑ አይሠራም፡፡ አዘጋጁ የደከመውን ያህል ችላ ያላቸውም በርካታ ነገሮች አሉ፡፡ የዶክተሩ ጋዋን፡፡ በፍጥነት ኦፕራሲዮን መሥራቱ ሳያንስ የደረቀ ደም የነካው ጋዋን ሲያወልቅ ግን ያበሳጫል፡፡ እርጥብ ደም የነካው ጋዋን ቢያስቀምጥና እነ ደምለው ሲነኩት እጃቸው ላይ ደሙ ቢቀር ጥሩ ይሆን ነበር፡፡ በፎጣቸው እንዲጠርጉት ወይንም ገብተው እንዲታጠቡ ማድረግ ይችላል፡፡ አዘጋጁ እጃቸውን ሲታጠቡ ያሳየንን ያህል ለደሙም ሊጨነቅ ይገባል፡፡ ቴአትር ስለሆነ በግድ እመኑ በሚል እሳቤ ደረቅ ደም የነካው ጋዋን አሳይቶናል፡፡

## ለሳምንት የሚቆይ ግልኮስ አለ ወይ?

የሚለውን ጥያቄ ማንሳታችንን ትተን ሜሮን እንኳን ይህንን የዶክተሩን ሐሳብ አለመሟገቷ ይገርማል፡፡ ኦፕራሲዮን ተደረገች የተባለችውን እናታቸውን ዓይተው በቅፅበት የወጡበት አካሄድም ለተመልካች ለመንገር መጓጓትን እንጂ እውነታን አያሳይም፡፡ አራቱ ልጆቿ ባልተማሩ ሰዎች መወከላቸውም ሀገሬውን ሁሉ ጥቅል መኃይም አስመስሎታልና ሳቅ ፍለጋ ተብሎ ሲሠራ ተምሳሌቶችን ያበላሻል፡፡

ትንሳኤ ትዕይንቱን ሲጨርሱ ከጓዳ ሁና ‹‹ስከታተላችሁ ነበር›› የምትለው ሁኔታም አዘጋጁ ቴአትሩን ሲያዘጋጅ እንደዛ ሁኖ እያያቸው ነው ወይ ያዘጋጀው? የሚያስብል ነው፡፡ ከእውነታው ባንወጣ ጥሩ ነው፡፡ በድፍረት አራተኛ ግርግዳን አፍርሶ እንደልቡ ያዘጋጀውን ቴአትር አዘጋጇንም ከተመልካች እንድትወጣ ማድረግ ይችል ነበር፡፡ በኪነ-ጥበብ ሕግን አውቆ ሕግን መሻር ይቻላል፡፡ ያሻሻልነው ሕግ ግን ሕገ-ወጥ የሚያደርገን መሆን የለበትም፡፡ የዚህ ቴአትር የዝግጅት ድክመትም ይሄው ሕገ-ወጥ አካሄድ ነው፡፡ ምናልባት ደራሲው ቤቱን ሳሎን አድርጎ ከሠራው ሁሉም በተዘጋጀ በር ሊገባ ይገባል፡፡ አዘጋጁ ግን የደራሲውን ሳሎን አፍርሶ መቼቱን በረንዳ ቢያደርገውና እናታቸው ቤት ውስጥ ብትቀመጥ ለምን አራተኛ ግርግዳ አፈረስክ? ብዬ አልሟገተውም ነበር፡፡ ይህን ቴአትር በሀገር ፍቅር ቴአትር ቤት ስለተለማመዱት እነ ሜሮን ወደ መድረኩ መውጫ ደረጃ ላይ ሁሉ እንዲቀመጡ ተደርገዋል፡፡ ደረጃ የሌለው መድረክ ላይ ይመድረክ ቢባል ብሎኪንጉ ሊፈርስ ነው? ወይንስ ሜሮን ተሸማቃ እንድትቀመጥ ሊደረግ ነው? ወንዶቹ ደረጃ ላይ ተቀምጠው የሚወያዩበትስ ትዕይንት? መድረኩ ደረጃ ከሌለው ሶፋው እያለ ብሎኪንጉን ላለማፍረስ እንደቃሚ ሊቀመጡ ነው? የሐሳቡን ከፍታና ዝቅታ በተዋናይ እላይ መሆንና እታች መሆን የሚገለፅበትን ሁኔታ አዘጋጁ እንዴት ከግንዛቤ ማስገባት አልቻለም? በርካታ ቴአትሮችን እንደ ማዘጋጀቱ ይሄን ጉዳይ ችላ ማለት አይገባውም ነበር፡፡

የሙላቱ ምሰጣ መጋነኑን ብናልፈው እንኳን ሙዲ ሽረፋ ለተመልካች በቀጥታ የሚናገረውን ቢያቆመው ጥሩ ነው፡፡ ቴአትሩ በሆነ ባልሆነው ከተመልካች ጋር የሚፋጠጠው ነገር በዝቷል፡፡ ይሄም ቁም ነገር አለው በሚል ወደ ተመልካች እየመጡ ተናግሮ መሄድ ሲበዛ ያስተቻል፡፡ ሆኖም እንደ ‹‹ከዚህ መሀል ሽንቱ ያልመጣ ማን አለ?›› ዓይነት ንግግሮች አፅንኦት ተሰጥቶባቸው በአግባቡ ለተመልካቹ ፊት ለፊት የተነገሩበትን መንገድ ሳላደንቅ አላልፍም፡፡

የሞባይሉ ማርክና የተመረጠለት የጥሪ ድምፅ አንድ አለመሆን፤ ሞባይሉ ሲነሳም ብርሃን አለመታየቱ ትኩረት ለሚያደርግ ሰው ምቾት አይሰጥም፡፡ ሜሮንን የመኪና ቁልፍና ሞባይል እንድትይዝ ብትደረግ፣ እንዲሁም ከዶክተሩ ጋር ባትጨፍር ይመረጣል፡፡አራቱም ወንዶች ስንቅ ይዘው በአንድ ላይ መግባታቸው ሳያንስ መድረክ ላይ ተመልካች እንዲያያቸው መሳሳማቸው ያን ያህል አግባብ አይደለም፡፡

የመጨረሻዎቹ ትዕይንቶች ከመነሻው ላይና መጨረሻ ላይ ሲጀምሩ የሦስት መንግሥታት የሕዝብ መዝሙሮች ይሰማሉ፡፡ መቼቱን ስለሚጠቁሙልን ጥሩ አገባቦች ናቸው፡ ፡ ሆኖም የሕዝብ መዝሙሮችን ሙሉውን ካልተጠቀምንባቸው የመጨረሻዎችን አንጓዎች መጠቀም እንደሚገባን እየታወቀ በዘፈቀደ አንዱን ከመሀል ሌላውን ከመጀመሪያውና ሦስተኛውን ከመጨረሻው አዳቅሎ እንዲቀርብ ሆኗል፡፡ ይሄም ይታሰብበት፡፡

ቴአትሩን ሁለቴ ዓይቼዋለሁ፡፡ መጀመሪያ ባየሁት ጊዜ ቴአትሩ ሲጀምር አንድ ወንበር አልወደቀም ነበር፡፡ ተምሳሌትነቱን አድንቄ ወጥቻለሁ፡፡ በሁለተኛ ቀን ዕይታዬ ደግሞ ሁሉም ወንበሮች ወድቀው ቴአትሩ ይጀምራል፡፡ ወጥነት ያስፈልጋል፡፡

ቴአትሩ በሰውኛ ዘይቤ ኢትዮጵያን እንድንመለከታት ተደርጎ የተፃፈና የተዘጋጀ እስከሆነ ድረስ የታማኝነት ጥያቄ እንዳያስነሳ፤ የአባታቸውንና የዕድሜያቸውን ሁኔታ ግምት ውስጥ ማስገባት ይገባ ነበር፡፡ ወይንም በዕድሜ ልዩነት ያላቸውን ገፀ-ባሕሪያት መሳል ነበረበት፡፡

መድረኩ ባላንስ ስለሚጎለው ወደ ቁምሳጥኑ አጋድሏል፡፡ በዚያ ላይ ቴአትሩ የተለያዩ ስፖት ላይቶች የሚፈልግ ቢሆንም ተሟልቶለት አልተሠራም፡፡

ምንም እንኳን ታዬ ስለቀረ ተጨንቆ ነው ቢባልም ስለቴአትሩ በሬዲዮ እየተነገረ ነው ሲባል ችላ የሚል ደራሲ መሳል ከእውነታው ያፈነግጣል፡፡ ይህም ማለት ይህ ፅሑፍ በግዮን መፅሔት ላይ ታትሞ እያለ አዘጋጁና ደራሲው በሌላ ጉዳይ በመጠመዳቸው አያነቡትም እንደ ማለት ነው፡፡ ያም አለ ይህ ካላነበቡት እነሱ ልክ ናቸው፡፡ ካነበቡት ደግሞ በቴአትሩ ላይ ማስተካከያዎችን ሊያድርጉ ይችላሉ የሚል ግምት ይኖረኛል፡፡



ከገጽ 5 የዞረ

ኢትዮጵያዊነትን ማስቀደም የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን ግዴታ እንደሆነ ሲናገሩ ሰምቻለሁ። ይሄን አመለካከታቸው የድርጅቱም አመለካከት ማድረግ የሚችሉ ከሆነ ይሄ ለኢትዮጵያ ፖለቲካ አንድ ትልቅ እምርታ ነው ብዬ አስባለሁ።

በነዚህ ምክንያቶች ተስፋ አድርጌያለሁ። ይሄ ተስፋ ግን እርግጠኛ የሚኮንበት አይደለም። ምን ያህል ነፃነት ኖሯቸው በስብስቡ የሚሰጠውን ውሳኔ አሸንፈው ከላይ የገለጹትን እነዚህን አስተሳሰብ የድርጅቱ አስተሳሰብ ማድረግ ይችላሉ? የሚለው በጥያቄ ምልክት የሚገባ ይሆናል። ዞሮ ዞሮ በአዲስ መሪነት ሲመጣ በጣም ውስብስብ ችግር ባለበት ሁኔታ የመጡ ሰው ናቸው። ስለዚህ እድል ሰጥቶ ለለውጥ የሚያደርጉትን ጥረት በጥንቃቄ እያዩ መደገፍ ተገቢ ይመስለኛል። ድጋፍ እንግዲህ የምንሰጠው ሰላማዊ ሰልፍ በመውጣት መፈክር በማሰማት ሳይሆን ቢያንስ የተረጋጋ ሰላማዊና ለለውጥ በሚያመች ሁኔታ ፋታ እንዲያገኙ በቂ ጊዜ በመስጠት ህዝቡ የራሱን ትብብርና እገዛ ሊያደርግላቸው ይገባል ብዬ ነው የማምነው።

**ግዮን፡- የእሳቸው መመረጥ ህዘባዊ ናቸው ያስብላል ወይስ እንደ ከዚህ ቀደሙ ግለሰቦች የድርጅቱ ተልዕኮ አስፈፃሚ ብቻ ይሆናሉ?**

አቶ ልደቱ፡- ይሄ ወደፊት በተግባር ነው የሚታየው፤ ቅድም ያነሳሁላሁ አመለካከቶች ለአገር የሚጠቅም ህዝቡ የወደደላቸው በመሆኑ የአገር አስተሳሰብ ቢሆን የምወደውና ኢዴፓ የታገለለት አስተሳሰብ ነው። ግን ምን ያህል ገፍተውበት ከዳር ያደርሱታል የሚለውን ወደፊት የምናየው ነው የሚሆነው።

**ግዮን፡- ዶክተር አብይ ወደ ስልጣን መጥተዋል። በአሁኑ ሰአት ቅድሚያ ሰጥተው ሊሰሯቸው የሚገቡ ችግር ፈቺ ናቸው የሚባሉ ጉዳዮች ምንድን ናቸው?**

አቶ ልደቱ፡- ዶክተር አብይ ብቻቸውን ያደርጉታል ወይ? አይመስለኝም እንደ አቶ ሽፈራው መግለጫ ከሆነ በቡድን ነው የሚሰራው፤ እርሳቸው የቡድን መሪ እንጂ ብቻቸውን የሚያደርጉት ነገር የለም ብለው ነው የተናገሩት። ስለዚህ እነዚህ ያነሳሃቸው ጉዳዮች ሁሉ በኢህአዴግ ታምኖባቸው ወደ ተግባር መለወጥ ያለባቸው ናቸው። የመሪው መመረጥ በጣም መሰረታዊ የሆነ ለውጥ ያመጣል ብለን መጠበቅ የለብንም። ስለዚህ ኢህአዴግ ዝም ብ ሎ በሌሎች ጉዳዮች ዙሪየያ ጭምጭምታ መሄድን ትቶ ቀጥታ ወደ ፖለቲካው መፍትሔ መግባት አለበት። እሱ ነው ችግሩን በሃላፊነት ሊፈታ የሚችለው። እና የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ከዚህ ጋር ተያይዞ መታየት አለበት እንጂ እሳቸው ወደ ስልጣን ስለመጡ የሚለወጥ አይመስለኝም፤ ለህዝቡ ጥያቄ የሚመጥን የፖለቲካ መፍትሔ መስጠት ነው ወሳኙ፤ እዛ ደረጃ ላይ በሙሉ ልቡ ኢህአዴግ አልገባም። መግባት አለበት፤ ይህ ካልሆነ መልሶ የማይነሳበት ምክንያት የለም።

**ግዮን፡- አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የዜጎችን በነፃነት የመንቀሳቀስ መብት ይገድባል እየተባለ ነው፤ በግልፅ እንዳየነውም በተለያዩ ቦታዎች ዜጎች እየተያዙ ነው፤ ከዚህ አንፃር ያልተፈቱ የፖለቲካ እስረኞችን ከመልቀቅ አዋጁን ከማስተካከል ብሄራዊ እርቅን ከመፍጠር አኳያ ከአዲሱ መሪያችን ምን ይጠበቃል?**

አቶ ልደቱ፡- በዚህ ደረጃ እሳቸው የሚፈልጉትን ነገር ያደርጋሉ የሚል እምነት የለኝም። የቡድን አስተሳሰብና አሰራር ባለበት መስመር ውስጥ እርሳቸውና ተከታዮቻቸው በሚፈልጉት መንገድ ያስኬዱታል ብዬ አልጠብቅም።እውነቱን ለመናገር አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ በተለይ በኢህአደግ ዙሪያ እየሆነ ያለውን ነገር በተለመደው መልኩ የፖለቲካ ትንታኔ የምንሰጥበት አይመስለኝም። አንዳንድ የማይጠበቁና ግራ አጋቢዎች እያየን ነው የሚሆነውን ነገር መጠበቅ ነው የሚሻለው።

**ግዮን፡- ውይይታችን ለመቋጨት ያህል እርስዎ አንድ የፖለቲካ ሰው እንደመሆንዎ ለሕዝቡና ለኢህአዴግ በዚህ አጋጣሚ የሚያስተላልፉት መልዕክት ምንድነው?**

አቶ ልደቱ፡-አሁንም ኢህአዴግ እየሰራ ያለው የራሱን የውስጥ ድርጅታዊ አንድነት እንደገና አጠናክሮ ለሌሎች አስርት አመታት የስልጣን እድሜውን የሚያራዝምበት ስልት እያመቻቸ ነው ብዬ አምናለሁ። ከህዘቡ ጥያቄ ጋር የሚመጣጠን መሰረታዊ የፖለቲካ መፍትሔ ለችግሩ ለመስጠት ሲዘጋጅ እያየሁ አይደለሁም። ይሄ ነገር አያዋጣም፤ ለተወሰነ ጊዜ መግዣነት ከማገልገል ያለፈ ፋይዳ አይኖረውም። መጨረሻ ግን ማጣፊያው አጥሮት ችግሩ መልሶ የበለጠ ጥልቅና ውስበስብ ሆኖ ሊከሰት ይችላል። በተደጋጋሚ እንዲህ አይነት የግዜ መግዣ ስልቶች በተከናወኑ ቁጥር የአገር ህልውና እንዳይመለስ ሆኖ ጥያቄ ውስጥ መግባቱ የማይቀር ነው። ስለዚህ ሳይመሽ ሳይረፍድ ወደ ትክክለኛው የፖለቲካ መፍትሔ መግባት አለበት። ከዚህ በኋላ በኢህአዴግ ብቻ ሊፈታ የሚችል ችግር የለም። ይሄ ችግር ከፖለቲካም በላይ ነው።

የአገር ህልውና ጉዳይ ነው። ህዝቡን በየደረጃው የሚያሳትፍ፤ የህዝቡ ወኪሎች የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን የሚያሳትፍ ሁሉን አቀፍ የሆነ የለውጥ ሂደት መፍጠር አለበት። አንድ የለውጥና የሽግግር ተቋም በአገር ደረጃ ማቋቋም፣ መነሻው መድረሻው በህግ ተወስኖ የሚቆይበት ጊዜና ተግባር ተወስኖ መፈፀም አለበት። ግቡ ደግሞ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ተካሂዶ ህዝቡ የሚፈልገውን መንግስት የሚመርጥበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት። ይሄ ከመሆኑ በፊት ግን ህዝቡም በሰላማዊና በህጋዊ ትግል ከተስፋ መቁረጥ ውስጥ ወጥቶ በራስ የመተማመን አድሮበት በማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ዙሪያ ተሰብስቦ በሙሉ ልቡ የሚታገልበት ሁኔታም መፈጠር አለበት።

ከዚህ በኋላ ነው ወደ እውነተኛ የምርጫ ሂደት መግባት ያለበት። እንደዚህ አይነት ተጨባጭ የሆነ ሪፎርም ውስጥ ካልተገባ ኢህአዴግ የራሱን ጥቅምና የበላይነት አስጠብቆ በገደብ የሚያመጣው የተሃድሶ እንቅስበቃሴ ወይም ለውጥ ችግሩን በዘላቂነት ይፈታዋል ብዬ አላስብም።

በህዝቡ በኩል ያለው ክፍተት ህዝቡ ራሱ መፍትሔ እየጠበቀ ያለው ከኢህአዴግ ነው። ይሄ ስህተት ነው ብዬ አምናለሁ። ህዝቡ የራሱን ፍላጎትና ጥቅም የሚወክሉበት ፓርቲዎች እንዲኖሩ መታገል ነው ያለበት፤ ይሄ ክፍተት በከፍተኛ ደረጃ ኢትዮጵያ ውስጥ አለ። ህዝቡ በተናጠል ባልተደራጀና ባልተጠና ሁኔታ የሚያካሂደው ትግል ሄዶ ይከሽፋል። ከንቱ ይቀራል። ስለዚህ ያ እንዳይሆን እና ተቃውሞ ጎራ በአሁኑ ሰአት ከምንም በፊት ትኩረት የሚረባረብበት የሚገባ የህዝቡን ፍላጎትና አመለካከት ሊወክሉ የሚችሉ ጠንካራ የፖለቲካ ፓርቲዎች በአስቸኳይ ተቋቁሞ ወይም ተጠናክረው የህዝቡን ትግል የሚመሩበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት። ትኩረቱን፣ ጉልበቱን፣ ጊዜውን ማጥፋት ያለበት ህብረተሰቡ እዚህ ላይ ነው ብዬ አምናለሁ። በእኛ በኩል ይሄ እንዲሆን እየጮህን ነው፤ የሚሰማን አላገኘንም፤ በጣም ትኩረት ያላገኘ ዝም ተብሎ የተተወ ጉዳይ ነው። በዚህም ምክንያት ህብረተሰቡ አሁን መፍትሔ የሚጠብቀው የእርሱን አስተሳሰብ ከሚያራምዱ ፓርቲዎች መሆኑ ቀርቶ ከኢህአዴግ ሆኗል። ይሄ በጣም የሚያሳዝን ነገር ነው።

# «ዶክተር አብይ የህዝቡን ጥያቄ ካልመለሰ፤ የከፋ ችግር ይገጥመዋል»

## ዶ/ር መራራ ጉዲና



ግዮን፡- ዶክተር አብይ አህመድ ዓሊ አዲሱ የኢህአዴግ ሊቀመንበር ሆነው ተመርጠዋል፤ ካለዎት ፖለቲካዊ ልምድ አንፃር የእርሳቸውን ሹመት እንዴት አዩት?

ዶ/ር መራራ፡- ዶክተር አብይ ላለፉት በርካታ ዓመታት ኦህዴድ ውስጥ ከቆየበት አንፃር ካየነው እሱ ከሌሎች የተሻለ ነው፡፡ አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ እንቅፋት የሆኑትን ታሪካዊ ፈተናዎች እንዴት ያልፈዋል? የሚለው ነገር ውሉ አድሮ የሚታይ ነው፡፡

ዋናው ጉዳይ ኢህአዴግ ለለውጥ ተዘጋጅቷል ወይ? የሚለው ነው፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ የፖለቲካ እስረኞችን በሙሉ ይፈታል ወይ? የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ያነሳል ወይ? የሚሉት ወሳኝ ጥያቄዎች ከዶክተር አብይ ፊት ተደቅነዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአገሪቱ ውስጥ ካሉ ፓርቲዎች ጋር ወደ ሐቀኛ ክርክርና ብሔራዊ መግባባት መምጣት መቻል ይጠበቅበታል፡፡ ይሔን ለማድረግ ገዥው ፓርቲ ተዘጋጅቷል ወይ? የሚለው ግን ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

ዶ/ር አብይ በመንታ መንገድ ላይ ነው የቆመው፡፡ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የሚንቀሳቀሰው ከኢህአዴግ ጋር መሆኑን መዘንጋት የለብንም፤ ይሄንን ችግር ማለፍ ከቻለ የተሻለ ዕድል ይገጥመዋል፡፡ ካልቻለ ደግሞ እስካሁን ከነበሩት ጠቅላይ ሚንስትሮች የባሰና የከፋ ችግር ሊገጥመው ይችላል፡፡

ግዮን፡- የእሳቸው መመረጥ ህዝባዊ ናቸው ያስብላል? ወይስ እንደ ከዚህ ቀደሙ የድርጅቱ ተልዕኮ አስፈፃሚ ብቻ ይሆናሉ?

ዶ/ር መራራ፡- ከላይ ለዘረዘርናቸው ችግሮች በራሱ አዲስ አቅጣጫና በህዝቡ ፍላጎት መንገድ ጥያቄዎችን በመመለስ ችግሮችን ማለፍ ከቻለ ህዝባዊ ጠቅላይ ሚኒስትር ነው ማለት ይቻላል፡፡ ያንን ሳያደርግ ከቀረ ግን ያው እንደ ቀደሙት ጠቅላይ ሚኒስትር የድርጅት አጀንዳ አስፈፃሚ ብቻ ይሆናል ማለት ነው፡፡

ጠረጴዛ ላይ ያሉትን የህዝብ ጥያቄዎችን መመለስ ይኖርበታል፡፡ ለነገ ከነገ ወዲያ የማይባሉ አንገብጋቢ ጥያቄዎች ለዶክተር አብይ ከባድ ፈተና ይሆናሉ፡፡ ዋናው ነገር እነሱን በሰከነ መንገድ አስተውሎ መመለስ የአዲሱ ተመራጭ የቤት ስራ ነው፤ ይሄ ሲሆን ብቻ ነው ዶክተር አብይ ህዝባዊ ናቸው ማለት የሚቻለው፡፡

ግዮን፡- ከምርጫው ሳምንታት አስቀድሞ ኸርማን ኮኸን በቅርቡ ዶክተር አብይ ቀጣዩ ጠቅላይ ሚኒስትር ይሆናሉ የሚል አስተያየት ሰጥተው ነበር፡፡ ይሄ አባባል ምርጫው ላይ የአሜሪካ ግፊት አለበት አያስብልም?

ዶ/ር መራራ፡- እሱን ርግጠኛ አይደለሁም፡፡ ይሄ በአብዛኛው የኢህአዴግ የውስጥ የቤት ስራ ይመስለኛል፡፡ ግፊት ካለ በኦሮሚያ አካባቢ ወጣቶች ያነሱትን የተቃውሞ እንቅስቃሴ ለማረጋጋት በኢህአዴግ በኩል የተሰራ ይመስለኛል፤ ምናልባት ግፊት ካለ ማለቴ ነው፡፡

ግዮን፡- የኦህዴድና የብአዴን መቀራረብ በተመለከተ ሀሳብዎን ያጋሩን፤ የሁለቱ የመጣመር ጉዞስ ሕወሓትን ያሰጋዋል ማለት ይቻላል?

ዶ/ር መራራ፡- ማን ከማን ጋር እንደ ተሰለፈ የሚይሳይ ግልፅ የሆነ የውስጥ መረጃ የለኝም፡፡ ሕወሓት ላይ ተፅዕኖ ሊያደርጉ ይችላሉ ወይ? የሚለውን እርግጠኛ ሆኜ ብዙ ነገር ለማለት አልፈልግም፤ እውነታውም መረጃውም ችግር ስላለው ማለቴ ነው፡፡

ግዮን፡- ዶክተር አብይ አዲስ ካቢኔ ይመሰርታሉ ተብሎ ይጠበቃል ላለፉት 27 ዓመታት ያልተነካው የደህንነትና የመከላከያ ወሳኝ ኃላፊነት ቦታዎች ላይ ሹም ሽርና አዲስ ሚዛኑን የጠበቀ ሹመት ማየት አይጠበቅብንም?

ዶ/ር መራራ፡- አንድና ትልቁ ፈተና እሱ ነው፡፡ ዶክተር አብይ ይሄንን ችግር በተመለከተ አዲስ አሰራር ተከትሎ ይለውጠዋል ወይስ ባለበት ያስቀጥላል የሚለው ጉዳይ ነው ወሳኙ ነገር፡፡ ይሄ መቀየር ያለበት አካባቢ መሆኑ ምንም ጥያቄ የለውም፡፡ ግን አሁን ህዝቡ እንደ ሚፈልገው ማድረግ ይችላል ወይ? የሚለው አጠያያቂ ይመስለኛል፡፡

ዋናው ነገር ሕወሓትና ኢህአዴግ ለለውጥ ተዘጋጅተዋል ወይ? ነው፤ ድርጅቶቹ ለለውጥ ምን ያህል ራሳቸውን እንዳዘጋጁ እርግጠኛ አይደለሁም፡፡ የህዝብ ጥያቄን ቀባብቶ ማለፍ ሳይሆን መሰረታዊ ለውጥ ያስፈልገዋል፤ እንደሚታወቀው አራቱ የኢህአዴግ ድርጅት መሪዎች አገሪቷን ወደ ብሔራዊ መግባባት እንመራለን ብለው ቃል ከገቡ ሶስት ወር ያለፈው ይመስለኛል ግን እስካሁን ድረስ ብዙም የታየ ነገር የለም፡፡

በርግጥ የተወሰኑ የፖለቲካ እስረኞችን ፈቷል፤ አንዳንዶቹ ተመልሰው ቢገቡም፡፡ ከዚህ በዘለለ ለዘለቄታው የሚሆን የተጨበጠ ነገር እያየን አይደለም፡፡ አሁን በቅድሚያ መከናወን ካለባቸው ጉዳዮች መሃል የፖለቲካ እስረኞችን መፍታት፣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ማንሳት፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር መደራደር ይጠቀሳሉ፡፡

አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እያለ ሐቀኛ ከምንላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ለመደራደር መሞከር በጣም አስቸጋሪ ነው የሚሆነው፡፡ ሜዳው ንጹሕ የድርድር ሜዳ አይሆንም፡፡ ይሄ ጊዜ ሊሰጠው የማይገባ አንገብጋቢ ጉዳይ መሆኑን ኢህአዴግ ልብ ሊለው ይገባል፡፡ ሐቀኛ ድርድር ውስጥ ሳይገባ ብሔራዊ ዕርቅ የለም፡፡

ግዮን፡- ውይይታችንን ለመቋጨት ያህል እርስዎ አንድ የፖለቲካ ሰው እንደ መሆንዎ ለህዝቡና ለኢህአዴግ በዚህ አጋጣሚ የሚያስተላልፉት መልዕክት ምንድነው?

ዶ/ር መራራ፡- ችግሮች እስካልተፈቱ ድረስ የኢትዮጵያ ህዝብ ሠላማዊና ህጋዊ ትግሉን ከመቀጠል ውጪ ምንም አማራጭ ያለው አይመስለኝም፡፡ የኢህአዴግ መሪዎች በነካ እጃቸው ብሔራዊ መግባባትን እንፈጥራለን ብለዋል፤ እሱን ጠንክረው ቢሰሩበት የተሻለ ይሆናል ብዬ አስባለሁ፡፡

ከዚህ በኋላ በባለፈው መንገድ ከመጓዝ ይልቅ ረጋ ባለ ሁኔታ አስበው ተጨማሪ ሕይወቶች ሳይጠፉ፣ሀገሪቷ ተጨማሪ ቀውስ ውስጥ ሳትገባ የህዝቡን ጥያቄ በማዳመጥ መሪዎች በፍጥነት ምላሽ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡ ህዝቡ አሁን ነቅቷል፣ እንደ በፊቱ እናውቅልሃለን ሲባል ዝም አይልም፤ "በግድ እንግዛህ" ያመጣው ነውጥ በገሃድ ታይቷል ፤ይሄን ኢህአዴጎች ቢያስቡበት ጥሩ ነው፡፡

# «የተመረጠው ኢህአዴግ ነው፤ ምንም ለውጥ የለውም»

## አቶ ቡልቻ ደመቅሳ

**ግዮን፦ ዶክተር አብይ አህመድ ዓሊ አዲሱ የኢህአዴግ ሊቀመንበር ሆነው ተመርጠዋል። ካለዎት ፖለቲካዊ ልምድ አንፃር የእርሳቸውን ሹመት እንዴት አዩት?**

አቶ ቡልቻ፦ ዶክተር አብይ ተመረጠ ማለት ለእኔ ኢህአዴግ ተመረጠ ማለት ነው።

**ግዮን፦ ስለዚህ ምርጫው ምንም ለውጥ የለውም ማለት ነው?**

አቶ ቡልቻ፦ ለውጥ ይኖረዋል፤ ለውጡ ግን ኢህአዴግ የሚፈልገው አይነት ሰው መሆኑ ነው። ህዝቡ የእሱን መመረጥ ይፈልገው አይፈልገው አላውቅም። እኔ የራሴን ሃሳብና እምነት ነው የምናገረው። የሚገርምህ ነገር ዶክተር አብይ ኦሮሞ ስለሆነ አንዳንድ ሰዎች እየደወሉልኝ "እንኳን ደስ ያለህ" ይሉኛል (ሳቅ) ነገሩ እንዲህ ቀላል ነገር አይደለም።

**ግዮን፦ አዲሱ የኢህአዴግ ሊቀመንበር ካላቸው የፖለቲካ ልምድ አንፃር የተሰጣቸውን ሃላፊነት በአግባቡ ይወጣሉ ብለው ያምናሉ?**

አቶ ቡልቻ፦ በቅርቡ የሚያውቁት ሲያወሩ እንደ ሰማሁት ከሆነ ችሎታና ብቃቱ ሊኖረው ይችላል። ግን እኛ የምናወራው በፖሊሲ ጉዳይ ከማን ጋር ነው የሚሰራው? የማንን ሃሳብና እቅድ ነው የሚያስፈፅመው? ስራ ላይ የሚያውለውና የሚያምንበት ጉዳይስ ምንድነው? የሚሉት ጉዳዮች ናቸው ወሳኞቹ። ዶክተር አብይ የኢህአዴግ አመራር እስከሆነ ድረስ ማንኛውም ነገር የኢህአዴግ ነው ማለት ነው። ለውጥ አለ ብሎ በድፍረት ለመናገር የሚቻለው ለውጡ ስር ነቀልና ፖሊሲውና ስትራቴጂው ሲቀየር ብቻ ነው።

**ግዮን፦ ለውጡ እንዲመጣ ከተፈለገ ዶክተር አብይ ወደ ጠቅላይ ሚኒስትርነቱ ቦታ እንደተዛወሩ በፍጥነት መስራት አለባቸው ብለው የሚያምኗቸው ጉዳዮች ምን ምን ናቸው?**

አቶ ቡልቻ፦ በዋነኝነት የሚጠበቀው ወደ ህዝቡ ሰላምን ማምጣት ነው። ሰላም የሚፈጠረው ኢህአዴግ ለዘመናት ሲያደርገው እንደነበረው በግድ፣ በጉልበት፣ ሳይሆን በሰላማዊ ሥርአት ሰላምን ለዘለቄታው ለህዝቡ ማምጣት ይኖርበታል። በየሳምንቱና በየወሩ ህዝቡ ሆ ብሎ አደባባይ የሚወጣበትና የሚገደልበት፣ የሚደበደብበት ሁኔታ ከዚህ በኋላ እንዳይፈጠር ጠቅላይ ሚኒስትሩ መስራት ይጠበቅባቸዋል።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሁልጊዜ በጉልበትና በሃይል እየተገዛ መኖር መሮታል። ይሄን ተከትለው የተነሱ የነፃነት ጥያቄዎች ናቸው አሁን ያየነውን ችግር የፈጠሩት። ኢህአዴግ ሁሌም ቢሆን የህዝቡን ጥያቄ ለመስማት ሳይፈልግ ቢቆይም አልሰማም የሚባልበት ጊዜ ላይ አይደለም አሁን ያለው።

**ግዮን፦ የዶክተር አብይ ምርጫ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በመላ ኦሮሚያ የተስፋፋውን የኦሮሞ ወጣቶች አመፅ ለማብረድና በተዛማጅ የሌሎች ሰዎችን ፍላጎት ለማሟላት ታስቦ የተደረገ**



**ምርጫ ነው የሚሉ ወገኖች አሉ፤እርስዎ በዚህ ላይ ያለዎት አስተያየት ምንድን ነው?**

አቶ ቡልቻ፦ እኔ እንግዲህ ኢህአዴግ አይደለሁም ከምን አንፃር እንደመረጡት አላውቅም ነገር ግን በተወሰነ መልኩ እኔም ሰው እንደሚያስበው አስባለሁ። በነገራችን ላይ ኦሮሞ ብቻ ሳይሆን አማራውም ሆነ ሌላው ህዝብ ዘንድ ብትሄድ ብዙ ሰው ደስተኛ አይደለም፤ ስለዚህ የእሱ መመረጥ ይሄንን ሁሉ ነገር ያስረሳል የሚል እምነት አለኝ። እንደ ተባለው የሚነሱትንም ተቃውሞዎች ለጊዜውም ቢሆን ጋብ ያደርጋል ብዬ አስባለሁ።

**ግዮን፦ የኦሮሞ ወጣቶችም ሆኑ ሌሎች የህብረተሰቡ ክፍሎች የሚፈልጉትን ጥያቄ መመለስ ካልቻሉ ዶክተር አብይ ምን ይገጥማቸዋል?**

አቶ ቡልቻ፦ ይወርዳሉ፤ ሌላ ሰው ይመረጥበታል ከዚህ የተለየ ምንም ምርጫ እንደማይኖራቸው በዚህ አጋጣሚ ሊገነዘቡት ይገባል።

**ግዮን፦ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ መነሳት፣ ያልተፈቱ የፖለቲካ እስረኞችን ከመልቀቅ አኳያ ከአዲሱ መሪ ምን ምን ይጠበቃል?**

አቶ ቡልቻ፦ ዶክተር አብይ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን በፍጥነት ያሻሽላል ብዬ ነው የማስበው። አሁን በተለያዩ የኦሮምያ ክልሎች ችግሮች አሉ፤ የተጠየቀው ጥያቄ አልተመለሰም። ይሄንን ነገር በአንድ ጊዜ መመለስ ካልቻለና ህዝቡን ፀጥ ካሰኘ ለእኔ ትልቅ ስራ ነው። ይሄ የእኔ ፍላጎት ብቻ አይደለም፤ ግን ዶክተር አብይ በተወሰነ መልኩም ቢሆን ለቦታው ተገቢ ይመስለኛል። የእኔ ፓርቲ እሳቸውን አልመረጠም። ምርጫው የኢህአዴጎች ነው፤ ስለዚህ አሁን ቅድሚያ የሚሰጠው የህዝቡን ጥያቄ መመለስ ነው።

**ግዮን፦ ኦህዴድና ብአዴን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተወሰነ መልኩ ተቀራርበዋል ይባላል ይሄ አካሄድ ለሕወሓት ችግር ይፈጥራል?**

አቶ ቡልቻ፦ በእኔ ግምት ኦሮሞ ለመጀመሪያ ጊዜ በእንዲህ ዓይነት ከፍተኛ ኃላፊነት ላይ ሲቀመጥ ሕወሓቶች ሊደሰቱ፣ አሜን ብለው ሊቀበሉ ይገባል። በሌላ በኩል እንመልከተው ካልን ቄሮዎች፣ የሚቃወሙት፣ የሚረብሹት ማንን ጠልተው ነው? (ሳቅ) ግን ዋናው ነጥብ ለአገሪቱ የሚበጅ ነገር መስራቱ ላይ ነው እንጂ አንዱን የበላይ ሌላውን የበታች አድርጎ መመልከት ዋጋ የለውም፤ ሁሉም ድርጅቶች በቅንነት ለአገራቸው ሊያገለግሉ ይገባል።

**ግዮን፦ ዶክተር አብይ አዲስ ካቢኔ ሲያቋቁሙ ለረጅም ጊዜ ያልተነካውን የመከላከያና የደኅንነት ታላላቅ ኃላፊነቶች ከሕወሓት እጅ በማውጣት አዲስ ተሿዋሚ በቦታው ላይ ማስቀመጥ አለባቸው የሚሉ ወገኖች አሉ ይሄንን እንዴት ያዩታል ይሆናል ብለውስ ይስባሉ?**

ዶ/ር ቡልቻ፦ እሱ አይደረግም፤ አይነካም ብዬ ነው የማምነው። እንዲህ ያለ ቦታ ከህወሃት/ኢህአዴግ እጅ አይወጣም። በምንም መንገድ ይሆናል ብዬ አላስብም። ይህ ለዘመናት እንዳየነው ይሄን መሰሉን የኃላፊነት ቦታ ራሳቸው ይዘው ነው ነገሮችን የሚያሽከረክሩት፤ ለሌላ ሰው አሳልፈው አይሰጡም።

**ግዮን፦ ይሄ ለውጥ ቀርቶ አፈና እስር ከበረታ የዶክተር አብይ መመረጥ የሚፈይደው ነገር አይኖርም ነው እያሉት ያሉት?**

ዶ/ር ቡልቻ፦ በትክክል። እኔ እንደማምነው ደህንነት ፣መከካላከያውን በተመለከተ ያሉ ወሳኝ ቦታዎችን ሁሉንም በአንድ ጊዜ አሳልፈው ለእሱ ይለቁለታል የሚል አቋም የለኝም። አንተ ስታስበው ሁሉንም ነገር ለእሱ ለቀው ቁጭ ብለው የሚያዩ ይመስልሃል? አይሆንም። እንዲህ ያለው ነገር ለዘመናት ከያዙት መንገድ እንዲወጣ ፈፅሞ አይፈልጉም።

**ግዮን፦ በመጨረሻ ለኢትጵያ ህዝብ ብሎም ለኢህአዴግ የሚያስተላልፉት መልዕክት ምንድነው?**

ዶ/ር ቡልቻ፦ የኢትዮጵያ ህዝብ በዚህ ጨዋታ ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፤ ህዝቡ ካልገባ አይሆንም። ህዝቡን ንቆ ወደ ውጪ መተው የትም አያስደርስም። ህዝቡን እንደ እውቀትና ችሎታው መጠን የሚጠይቀውን ነገር ተገንዝቦ የሚፈልገውን ነገር ማድረግ ነው፤ በዚህ ዘመን መፍትሔ ሊሆን የሚችለው።

ፖለቲካ ማለት ህዝቡ የሚፈልገውን ነገር ማድረግ ማለት ነው። በጠቅላላው በዋናነት አንድ መሪ በህዝቡ መወደድ አለበት፤ ይሄ ወሳኝ ነገር ነው። ወደ ስልጣን ያመጣውን ህዝብም መሪው ማስደሰት አለበት፤ ህዝቡ የሚፈልገውን ነገር ማድረግ አለበት። ይሄንን በዚህ አጋጣሚ ለህዝቡና ለሚመለከተው አካል የማስተላልፈው።

# «ህዝቡንም ሊያሳምን የሚችል አካሄድ ይከተላሉ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ»

## አቶ ተመስገን ዘውዴ

**ግዮን፡- ዶክተር አብይ ዓሊ አዲሱ የኢህአዴግ ሊቀመንበር ሆነው ተመርጠዋል። ካላቸው ፖለቲካዊ ልምድ አንፃር የእርሳቸውን ሹመት እንዴት አዩት?**

አቶ ተመስገን፡- እውነቱን ለመናገር የዶክተር አብይን የኋላ ታሪክ እና የፖለቲካ ልምድ አላቸው፤ የላቸውም የሚለውን ነገር በደንብ አላውቅም። በትክክል ኢትዮጵያን መምራት ይችላሉ የሚል ግምት ወስደው፣ እርግጠኛ ሆነው ያደረጉት ምርጫ በዲሞክራሲያዊ ስርአት እስከሆነ ድረስ እቀበለዋለሁ።

**ግዮን፡- የእሳቸው መመረጥ ህዝባዊ ይሆናሉ ያስብላል ወይስ እንደ ከዚህ ቀደሙ የድርጅቱ ተልዕኮ አስፈፃሚ ብቻ ይሆናሉ?**

አቶ ተመስገን፡- እንግዲህ ዶክተር አብይ የተለየ መንገድና እቅድ ካልነደፈ በስተቀር ያለፈው የኢህአዴግ ሥርዐት በአብዛኛው የድርጅታቸውን ራዕይ ማስፈፀም ነው እንጂ የህዝቡን የልብ ትርታ የማዳመጥ ባህል የላቸውም። በአዲሱ ጠቅላይ ሚኒስቴርም እንዲህ አይነት ነገር ይሆናል የሚል ጽንፍ ለመያዝ መጀመሪያ ስራቸውን ማየት ያስፈልጋል። ፍርድ ለመስጠት መጣደፍ ተገቢ አይመስለኝም።

ያለፈው ልምድ የሚያሳየው ግን የኢህአዴግ ሰዎች የድርጅታቸውን ተልዕኮ በማስፈፀም ደረጃ ሲሰሩ እንጂ ህዝቡ የሚፈልገውን ሲያደርጉ ወይም ከእነሱ አመለካከት ወጣ ያለ ድርጅት ካለ እነሱን የማዳመጥ፣ የፖለቲካ ምህዳሩን የማስፋት፣ የተለየና ጠቃሚ ሀሳብ ያላቸውን ሰዎች የማዳመጥና እድል የመስጠት ባህል የላቸውም። ይሄ አሰራር በዶክተር አብይ የስልጣን ጊዜ ይፈፀማል አይፈፀምም የሚለው እድል ሰጥተናቸው ወደፊት የምናየው ነው የሚሆነው።

**ግዮን፡- ዶክተር አብይ ወደ ስልጣን መጥተዋል። በአሁኑ ሠዐት ቅድሚያ ሰጥተው ሊሰሯቸው የሚገቡ ችግር ፈቺ ናቸው የሚባሉ ጉዳዮች ምንድን ናቸው?**

አቶ ተመስገን፡- እንግዲህ ዶክተር አብይ የመቶ ሚሊየን ህዝብ ጠቅላይ ሚኒስቴር ነው የሚሆነው፤ በአሁኑ ሠዐት ትልቁ ጉዳይ አንድነታችን መሸርሸሩ ነው። በኢህአዴግ 27 ዓመታት አገዛዝ አንድ ያጣነው ነገር ቢኖር ኢትዮጵያዊታችንን ነው። ኢትዮጵያዊነታችን ተሸርሽሯል፤ የታሪካችን የአንድነታችን መሠረት ኢትዮጲያዊነታችን ነበር። ሁላችንም ወደ መንደራችን ተመልሰን የምናስብ ከሆነ፣ በመንደር ደረጃ የምናስብ ከሆነ ኢትዮጵያ የምትባል አገር ላትኖር ትችላለች።

ስለዚህ ዶክተር አብይ የሁሉም ነገር ማጠንጠኛ ለውጥ ሊያመጡ ይችላሉ፤ ዋና ተግባራቸውም ህዝቡን ማረጋጋትና የአንድነት መሰረታችን ኢትዮትያዊነት መሆኑን በማመን ደግመው ደጋግመው ሊሰሩበት ይገባል። ይህ ካልሆነ ግን ያው የድርጅቱን ተልዕኮ ማስፈጸም ብቻ ነው የሚሆነው።

**ግዮን፡- አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የዜጎችን በነፃነት የመንቀሳቀስ መብት ይገድባል እየተባለ ነው። በግልፅ እንዳየነውም በተለያዩ ቦታዎች ዜጎች እየተያዙ ነው፣ ያልተፈቱ የፖለቲካ እስረኞችን ከመልቀቅ አዋጁን ከማስተካከል ብሔራዊ እርቅን ከመፍጠር አኳያ ከአዲሱ መሪያችን ምን ይጠበቃል?**

አቶ ተመስገን፡- ብዙ የሚጠበቅ ነገር አለ። ህዝቡን በማሰር የአገር መፍትሔን ማምጣት አይቻልም። ቀደም ብዬ አንድነት በማለት ያነሳሁልህ ነገር ከዚህ ጋር የተያያዘ ነው፤ ሰላማዊ ተቃውሞ ያቀረቡ ሰዎችንና ፖርቲዎች ወደ ሰላማዊ የመከራከሪያ መድረክ ማምጣት ይኖርባቸዋል። ይህ ሳይሆን ቀርቶ ዜጎች ዝም ብለው የሚታሰሩ ከሆነ በዛ መንገድ የሚፈጠር ለውጥ የለም፤ ኖሮም አያውቅም።

ስለዚህ በአገራችን ወደ ፊት የተሻለ ነገር እንዲፈጠር መፍትሔው በእስር ቤት ያሉ የፖለቲካ ሰዎችን መፍታት የፖለቲካ ፓርቲዎችን አቅርቦ ያለውን ችግር በድርድር መፍታትና ከተበላሸ የድርጅት ስራ ተላቆ በአዲስ አመለካከት ለሀገር መስራት ከዶክተር አብይ የሚጠበቅ ተግባር ነው። ተፎካካሪ ፖርቲዎችም ቢሆኑ እኮ ሌላ አገር የላቸውም፤ እዚሁ ነው አገራቸው። ስለዚህ ይሄ በጣም በትኩረት ሊሰራበት የሚገባ ጉዳይ ነው።

**ግዮን፡- ዶክተር አብይ አዲስ ካቢኔ ይመሰርታሉ ተብሎ ይጠበቃል ላለፉት 27 ዓመታት ያልተነካው የደህንነትና የመከላከያ ወሳኝ ኃላፊነት ቦታዎች ላይ ሹም ሽርና አዲስ ሚዛኑን የጠበቀ ሹመት ማየት አይጠበቅብንም?**

አቶ ተመስገን፡- ማንኛውም የመንግስት ተቋማት የኢትዮጵያን ህዝብ መምሰል አለባቸው። ይሄ ምንም ጥርጥር የለውም። መከላከያውም ሆነ ሲቪል ሰርቪሱም ሆነ ሌላው ተቋም የኢትዮጵያን ህዝብ የሚመስል መሆን አለበት። ስለዚህ ዶክተር አብይ ያሉትን ሁኔታዎች ዞር ብሎ በመመልከት የሚያስተካክል ካቢኔ መመስረት ይጠበቅባቸዋል። ይህም ይሆናል ብለን እንገምታለን፤ እንጠብቃለን ህዝቡንም ሊያሳምን የሚችል አካሄድ ይከተላሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

**ግዮን፡- የኦህዴድና የብአዴን መቀራረብ በተመለከተ ሀሳብዎን ያጋሩን የሁለቱ የመጣመር ጉዞስ ሕወሓትን ያሰጋዋል ማለት ይቻላል?**

አቶ ተመስገን፡- የሁለቱ ድርጅቶች መቀራረብ ሕወሓት ላይ ተፅዕኖ ይኖረዋል ብዬ አላምንም። ለልማት፣ ለዲሞክራሲ ለመልካም አስተዳደር አብሮ ለመስራት የተደረገ መቀራረብ ከሆነ በማንም ላይ ችግር አይፈጥርም። አብሮ ለመስራት እንደውም የበለጠ መቀራረብ ይኖርባቸዋል ብዬ ነው የማምነው።

ገዥው ፓርቲ ከዚህ በዘለለ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ተቀራርቦ መስራት አለበት። እኛ ሁሉንም ፖርቲዎች ፍፁም ቅን በሆነ መልኩ ተቀራርበው እንዲሰሩ ነው የምንፈልገው። የተለየ ሃሳብ ኖሮንም አያውቅም።

**ግዮን፡- ከምርጫው ሳምንታት አስቀድሞ ኸርማን ኮኸን በቅርቡ ዶክተር አብይ ቀጣዩ ጠቅላይ ሚኒስትር ይሆናሉ የሚል አስተያየት ሰጥተው ነበር። ይሄ አባባል ምርጫው ላይ የአሜሪካ ግፊት አለበት አያስብልም?**



አቶ ተመስገን፡- በነገራችን ላይ እኚህ ሰው ብዙ ጊዜ በኢትዮጵያ ፖለቲካ እጃቸውን የሚያስገቡ ሰው ናቸው። የዲሞክራሲ ሂደቱን በትክክል የሚረዱ አይደሉም። ምርጫ ማለት በእንጥልጥል ላይ ያለ ነገር ነው። መጨረሻው እስኪታወቅ ድረስ ማንም ሰው እንዲህ ነው ብሎ መናገር አይቻልም። በርግጥ እንደ ግለሰብ የራሳቸው ሃሳብ መግለፅ ይችላሉ ሆኖም ከዛ ደረጃ የዘለለ ከሆነ አስተያየታቸው ትክክል አይደለም። በመጠኑ እንደ ገለፅኩልህ እሳቸው ወደ ስልጣን የሚመጣውን ሰው መናገራቸውን ብዙም ቁም ነገር አልሰጠውም።

**ግዮን፡- ውይይታችን ለመቋጨት ያህል እርስዎ አንድ የፖለቲካ ሰው እንደመሆንዎ ለህዝቡና ለኢህአዴግ በዚህ አጋጣሚ የሚያስተላልፉት መልዕክት ምንድነው?**

አቶ ተመስገን፡- ዶክተር አብይ ለእዚህ ኃላፊነት ይመጥናሉ አይመጥኑም የሚለውን ተመልክቶ የኢህአዴግ ማዕከላዊ ም/ቤት ምርጫውን ያከናወነ ስለሆነ ለእሳቸው እድል ልንሰጣቸው ይገባል። የኢትዮጵያ ህዝብ ሰላም ወዳድ፣ ተከባብሮ የሚኖር ህዝብ ስለሆነ ለአዲሱ ተሿሚ በቅድሚያ ጥሩ የመስሪያ እድል ሊሰጣቸው እንደሚገባ ነው መልዕክቴን በዚህ አጋጣሚ የማስተላልፈው።

# 122 ዓመት ስንት ነው?

ሰሞኑን የመገናኛ ብዙኀን ኢትዮጵያና ሩሲያ ግኑኙነት የጀመሩበትን አንድ መቶ ሃያ ሁለተኛ ዓመትን በተመለከተ በተለያዩ ክንውኖች ሲዘክሩት ሰንብተዋል። በእርግጥ የሁለቱ ሀገራት ወዳጅነት ከአንድ ክፍለ ዘመን በላይ የሆነ ዕድሜ ጠገብ መሆኑን ለማሳየት መዛግብትን መፈተሽ ግድ ነው። የሩሲያና የኢትዮጵያ ዝምድና እስከምን ድረስ ነው ጥንታዊ መዛግብትስ ምን ይላሉ? የሚለውን ምላሽ ለማግኘት በጥቂቱ እንሞክራለን።



ከታላቁ ጴጥሮስ ዘመነ መንግሥት አንሥቶ እስከ የጥቅምቱ የሶሻሊስት አብዮት መፈንዳት ድረስ በሴንት ፒተርስበርግም ሆነ በሞስኮ በሚገኙት ቤተመንግሥቶች የነገሥታቱ ልዩ የክብር ዘቦች ሆነው ያገለገሉት ኢትዮጵያውያን ወታደሮች ነበሩ። አለባበሳቸውም ባለሁለት ራስ ንስር አሞራ ምስል የተጠለፈበት ጥቁር ከፋይ ወርቀዘቦ ጃኬት፤ በአብረቅራቂ ሐር ጨርቅ የተሠሩ ነጭ ተነፋነፍ ሱሪ እና ቀይ ቆብ ወይንም ነጭ ጥምጥም ነበር። በቫቲካን ቤተመንግሥት ውስጥ የሊውስ ጋርድስ በመባል የሚታወቁትን አልባሳት የክብር ዘብ አባላት ይለብሷቸው እንደነበር በቅርቡ ይፋ የሆኑ ጥናቶች አረጋግጠዋል። ለሩሲያ ንጉሠ ነገሥታት ክብር መገለጫ የነበሩት ቁመተ ሎጋዎቹ ኢትዮጵያውያን ወታደሮች የመጨረሻ ዕጣ ፈንታ ምን ሆነ? የብዙዎች ጥያቄ ነው።

## የሩሲያ እና የኢትዮጵያ የዘር ሐረግ

ብዙ ታሪክ ተመራማሪዎች የሁለቱ አገራት ሕዝቦች ግንኙነት አያሌ ዘመናት ያስቆጠረ እና የዘር ሐረግ ትስስር እንዳላቸው ማስረጃ አስደግፌው ይናገራሉ። ዋና ማጠናከሪያ የሚያደርጉት ደግሞ የዕውቁ ባለቅኔ የአሌክሳንደር ፑሽኪን አያት የሆነው ትውልደ ኢትዮጵያዊው የሩሲያ ጦር ጀነራል ሐኒባልን ነው።

ሁለተኛው ማረጋገጫቸው ደግሞ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተዋቂ የኒዩክሌር ሳይንቲስት የሆነው የኖቤል አሸናፊው አንድሬ ሳካሮቭም ኢትዮጵያዊ ዝርያ እንዳለው ይፋ ማድረጉ ነው።

በተጨማሪም በእንግሊዝ አገር ስሙ ገናና የነበረው ደራሲ ሰር ፒተር አስቲኖቭ ሩሲያዊ ወላጆቹን ዋቢ በማድረግ በእናቱ ከዐፄ ቴዎድሮስ የትውልድ ሐረግ የሚመዘዝ እንደሆነ ማሳወቁን እንደ ማስረጃ በመጥቀስ የአገራቱ ሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ዘመን ተሻጋሪ ብቻ ሳይሆን፤ የዘርና የደም ትስስር እንዳላቸው አስምረውበታል።

## የሩሲያ የዲፕሎማሲ ጥንስስ

ሩሲያ በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መባቻ ላይ ኤን ኤ አሲኖቭ በተባለ አገር አሳሽ መሪነት ከኢትዮጵያ ጋር ግንኙነት ለመመሥረት አድርጋው የነበረው ሙከራ ጅቡቲ ላይ በፈረንሳይ ተጨናግፎባታል። ከዓመታት በኋላ በ1889 ዓ.ም ባቪ. ኤች ማሽኮቭ የመራው የሩሲያ ልዑክ ከዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ጋር የጦር መሣሪያ ለመሸጥ ስምምነት ማድረጉን የሚያስረዱ ታሪካዊ መዛግብቶች አሉ።

ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ በመጀመሪያዎቹ የሥልጣን ዓመታቸው ከኢጣልያንና ከፈረንሳይ ቀጥሎ የዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት የመሠረቱት ከሩሲያ መንግሥት ጋር ነው። ሩሲያ ከኢትዮጵያ ጋር የጠበቀ የወዳጅነት መሠረቱን የጣለችው የጥቁሮች ሁሉ ድል በሆነው የአድዋ ድል ላይ ነው። በጦርነቱ ወቅት ታላቁ ንጉሥ እምዬ ምኒልክ የተጠቀሟቸው መድፎች ሩሲያ ሠራሽ ከመሆናቸው ባሻገር፤ ሩሲያውያን የጦር አማካሪዎች እና ሐኪሞችም ነበሩ። ለአብነት ያህል ሰርጌቪች ሊዮንቴቭ፣ ሊዮኔድ አርማቶቭ፣ ኒኮላይ ጌማሎቭ እና አሌክሳንደር ብላቶቪች ለሀገራችን የፀረ-ቅኝ ትግል የበኩላቸውን ሚና ከተጫወቱት ሩሲያውያን መሃል ይጠቀሳሉ። በዚሁ አጋጣሚ ለኢትዮጵያ ክብር ከተዋደቁት ሩሲያውያን መካከል አሌክሳንደር ብላቶቪችን ታሪክ እናንሳ።

## አሌክሳንደር ብላቶቪች እና ኢትዮጵያ

የሕክምናና የውጊያ ሊቁ አሌክሳንደር ብላቶቪች በሩሲያው ንጉሥ በዳግማዊ ኒኮላይ ትእዛዝ ከሩሲያ ቀይ መስቀል ልዑክ ጋር አብሮ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው በአድዋ ጦርነት ጊዜ ነበር።

አሌክሳንደር ብላቶቪች የሕክምና ባለሙያነቱን ተጠቅሞ ብዙ ጀግኖች ኢትዮጵያውያንን በጦር ሜዳ ተገኝቶ ረድቷል። ከአድዋ ድል ማግስት ጀምሮም የኢትጵያን አንድነትና ግዛት ለማስፋት የደቡብ መስመርን የተረከበው የራስ ወልደ ጊዮርጊስ ጦርን በመቀላቀል ወደ ከፋ ዘመተ። አማርኛን አቀላጥፎ የሚናገረው አሌክሳንደር ብላቶቪች ከፋን "ታላቁ የኢትዮጵያ ደቡባዊ ግዛት" ሲል ይጠረዋል። የከፋ ንጉሥና ሕዝብ "ለኢትዮጵያ ንጉሥ አንገብርም" በሚል እምቢ ባይነት ከራስ ወልደ ጊዮርጊስ ጦር ጋር ውጊያ ገጥሞ ያካሄደውን የጀግንነት ፍልሚያን አድንቆ በስፋት በመፅሐፉ ላይ አስፍሮታል። በዚህም ምክንያት ስለ ዘመቻው፤ ስለከፋ መልከዐ ምድራዊ አቀማመጡና የሕዝቡ አኗኗር ታሪክ እጅግ አስውቦ ባዘጋጀው የጉዞ ማስታወሻ ሳቢያ ሩሲያውያን "የከፋ መሐንዲስ" እያሉ ይጠሩታል።

የከፋው ንጉሥ ዋና መቀመጫን "አንደራቼ" የተባለውን ቦታ የተቆጣጠረው የራስ ወልደ ጊዮርጊስ ጦር ሕዝቡን ካረጋጋ በኋላ አሌክሳንደር ብላቶቪችን አስጠርተው "ክቡር ወዳጃችን ጦሩን ይዘን እስከ ሩዶልፍ ሐይቅ ብንዘምት ምን ይመስለሃል?፤ የመንገዱን ርቀት ሁኔታ የአየሩን ጠባይና የቦታውን አቀማመጥ መገመት አይቻልምን?" ብለው ይጠይቁታል። አሌክሳንደር ብላቶቪችም ጫካ በመመንጠር ምቹ መንገድ እንደቀየሰ ምላሽ ይሰጣል።

ጦሩም ወደ ሩዶልፍ ሐይቅ ተጉዞ ስድስት ወር የፈጀ ወታደራዊ ዘመቻውን በድል አጠናቋል። ድሉ አዲስ አበባ ሲሰማም ዐፄ ምኒልክ ደስታቸውን መድፍ በመተኮስና ክብረ በዐል በማዘጋጀት ገልፀዋል።

ኢትዮጵያን አንድ የማድረጉን ዘመቻ ደቡብ ላይ በድል ያጠናቀቀው የራስ ወልደ ጊዮርጊስ ጦር አዲስ አበባ ከተመለሰ በኋላ ሩሲያዊው የጦር መኮንን አሌክሳንደር ብላቶቪች በአድዋና በከፋ ላበረከተው ወታደራዊ አገልግሎት ዐፄ ምኒልክ የወርቅ ሜዳሊያ ሸልመውታል።

"ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ" በሚል ያሳተመውን ጽሑፍ ተከትሎ የሩሲያ ጂኦግራፊ ማኅበረሰብ የብር ሜዳሊያ ሸልሞታል። ከዚህ ባሻገር ከፕሮፌሰር ካሚል አራምቡርና ከዶክተር ሊውስ ሊኪ ጋራ በመሆን በምሥራቅ አፍሪካ ላይ ለአካሄደው ውጤታማ የጥናትና ምርምር የፈረንሳይ መንግሥትም የክብር ሜዳሊያ አበርክቶለታል።

በ1900 እ.ኤ.አ ወደ አገሩ ሩሲያ ከተመለሰ በኋላ ሁለት መጻሕፍት ለኅትመት ያበቃው አሌክሳንደር ብላቶቪች ከ122 ዓመት በላይ ዘመን ተሻጋሪ የሩሲያና የኢትዮጵያ የወዳጅነት ማሠሪያ ከሆኑ ሩሲያውያን አንዱ ሆኖ ለዘላለም ይኖራል። ግን 122 አመት ስንት ነው?







ግዮን
መጽሔት

12 3 6 9

ግዮን መጽሔት
በየ15 ቀን ቅዳሜ
ይጠብቁዋት!

ቀጣይ ዕትም
ቅዳሜ
መጋቢት 29
ይጠብቁን!

ጽርጅትዎንና
አገልግሎትዎን
ያስተዋውቁ!

በቀጣይ
ዕትማችን
የተመረጡ
አምዶቻችንን
ይዘን እንመጣለን

ፃፉልን፣
አስተያየት
ይስጡ ምልሻቹን
ፈጣን ነው




ስልክ : +251 912165606
+251 912165606
ኢ-ሜይል: gihonmeg@gmail.com
Facebook: gihon2010meg@gmail.com